17ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው [ወደ ኢየሱስ ቀርቦ በፊቱ ተንበረከከና[ማቴ]] እንዲህ አለው፤ [ጌታ ሆይ፣ እባክህ ልጄን ማርልኝ[ማቴ]] «መምህር ሆይ፣ ርኩስ መንፈስ አድሮበት ዲዳ የሆነውን ልጄን [ያለኝ ልጅ እርሱ ብቻ ስለሆነ[ሉቃ]] [በሚጥል በሽታ እየተሠቃየ ነው[ማቴ]] ወደ አንተ አምጥቼዋለሁ፤ 18በተነሣበት ጊዜ ሁሉ [በድንገት ይጮኻል[ሉቃ]] ይጥለዋል፤ [ያንፈራግጠዋል[ሉቃ]] አረፋ ይደፍቃል፤ ጥርሱንም ያፋጫል፤ ሰውነቱም ይደርቃል፤ [ጉዳት ካደረሰበት በኋላ በስንት መከራ ይተወዋል[ሉቃ]] ርኩስ መንፈሱን እንዲያስወጡት [ሊፈውሱት[ማቴ]] ደቀ መዛሙርትህን ጠየቅኋቸው፤ እነርሱ ግን አልቻሉም::

*ማር 9÷17-19 ከማቴ 17÷14-17፤ ሉቃ 9÷37-41 ጋር ያነ*

19ኢየሱስም መለሰ፣ «የማታምን [ጠማማ[ማቴ፣ሉቃ]] ትውልድ ሆይ፤ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ልጁን ወደ እኔ አምጡት!» አላቸው::

ይህ ልጅ በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ ነበር:: ማቴዎስ ሕመሙ የሚጥል በሽታ እንደ ነበር ይናገራል (ግሪክ - ሴሌኒያዞ - *Seleniazo*)::[77] ችግሩ ከአጋንንት ጋር የተያያዘ መሆኑ ግልጽ ይሆን ዘንድ ባለመድኃኒቱ ሉቃስ ምንም የሕክምና ቋንቋ አለመጠቀሙ የሚገርም ነው:: በአጋንንት ምክንያት የደረሰበት አካላዊ ችግር የሚከተሉትን ይጨምራል:-

1. መናገር አይችልም ነበር፤ አልፎ አልፎ በድንገት ከሚያሰማው ጩኸት በቀር::
2. የሚጥል በሽታ ነበረበት - መሬት፣ እሳትና ውሃ ላይ ይጥለው ነበር::
3. ከአፉ የሚወጣውን መቆጣጠር አይችልም ነበር - በአፉ አረፋ መድፈቅን፣ ጥርሶቹን ማፋጨትን ጨምሮ::
4. ሰውነቱ ይደርቅ ነበር [ዜራይኖ - *xeraino*] የሚለው ቃል፣ «መጠውለግን» ወይም፣ «ድርቀትን» ያመለክታል:: «መዛል»ን እንጂ፣ «ደረቅ መሆንን» ላያመለክት ይችላል (ማቴ 15÷28፤ 17÷16፣18፤ ማር 9÷18፤ በተጨማሪ ሉቃ 9÷42 ጋር ያነ)::

አጋንንት ብዙውን ጊዜ የሰውን አካል በበሽታ ያጠቁ ነበር::[78] ከዚህም የተነሣ መናፍስትን ማውጣት ፈውስ እንደሆነ ተመልክቷል (ከማቴ 15÷28፤ 17÷16፣18 ማር 9÷18 እና ሉቃ 9÷42 ጋር ያነ):: ኢየሱስ በፈወሳቸው ሕመሞች ዝርዝር በአጋንንት መያዝ የሚካተተው ምናልባት በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል (ማቴ 4÷24፤ 8÷16፤ 10÷8፤ ማር 1÷32-34፣39፤ ሉቃ 4÷41፤ 13÷32):: ይህ ማለት ሁሌም በሽታ በአጋንንት የሚመጣ ነው ወይም አንዳንድ አጋንንት ከተወሰኑ ዐይነት በሽታዎች ጋር የተያያዙ ናቸው ማለት አይደለም:: ወንጌሎቹ በበሽታና በአጋንንት መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ አስቀምጠዋል:: ይሁን እንጂ ከአጋንንት ባሕርይ አንዱ ጥፋት ነው (ለምሳሌ፣ የጌርጌሴናን ዐሣማዎች):: ስለሆነም ከተፈቀደላቸው አጋንንት ያደሩበትን አካል እንደሚያጠቁና እንደሚያጠፉ ግልጽ ነው::

ሐዋርያቱ ጋኔኑን ማስወጣት አቅቷቸው ነበር:: አሁን ግን ልበ ሙሉነት ሳይሰማቸው አልቀረም (ማር 3÷15፤ 6÷13):: «የማያምን ጠማማ ትውልድ ...» (ዘዳ 32÷5፣20 በሚያሳስብ መልኩ) በማለት

---

[77] «በጨረቃ የሚነሣባቸው» የሚለው አሳሳች ከመሆኑ ሌላ ትክክልም አይደለም:: ምንም እንኳ በሁለቱም ቃላት ጨረቃ የምታሳድረው ተፅዕኖ (Greek, *Selene*, Latin, *luna*) ቢታይም፣ ከዚያ ውጪ በመካከላቸው አንድም ግንኙነት የለም::

[78] ኢየሱስ አጋንንት ስለ ማውጣቱ ከተሰጡት ስድስት ገለጻዎች (§ 42፣61፣66፣68፣78፣87) ሦስት አካላዊ ሕመምን (ዐይነ ስውርነት፣ ደንቆሮነት/ዲዳነትና የሚጥል በሽታ)፣ አንድ ደግሞ በውል ያልታወቀ ሕመምን ያመለክታል (ማቴ 15÷22፤ ማር 7÷30):: ከርኩሳን መናፍስት ጋር ስላልተያያዙና በርኩሳን መናፍስት አማካይነት ስለሚመጡ ሕመሞች ሉቃ 13÷11ን በተጨማሪ ይመ::

መናገሩ ኢየሱስን በጣም ካሳዘነው ነገር አንዱ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው። ከመለወጥ ተራራ ከወረደ በኋላ ወዲያውኑ ከምቀኞቹ ጸሐፍት፣ ከጸበኞቹና አዳዲስ ነገር ናፋቂዎቹ ሕዝብና ዐቅመ ቢስነት ከተሰማቸው የቅርብ ወዳጆቹ ጋር ተገናኘ። አሁን ደግሞ ሐዋርያቱ እንኳ የማኅበረ ሰቡ እምነተ ቢስነት ተካፋይ ሆኑ (ከማቴ 11፥16፤ 12፥39 ጋር ያነ)። በአጭሩ፣ የተራራው ልምምዱ ኢየሱስ የመጣበትን እንዲናፍቅ፣ የሸለቆው ልምምዱ ደግሞ ገና ምን ያህል ርቀት መጓዝ እንዳለበት አሳይቶታል።

**ማር 9፥20-24**
**ከሉቃ 9፥42 ጋር**

20ሰዎቹም ወደ እርሱ አመጡት፤ ርኩስ
መንፈሱም [ጋኔኑም[ማቴ]] ኢየሱስን ባየው ጊዜ ልጁን
ወዲያው አንዘፈዘፈው መሬት ላይ ወድቆ
በመንፈራገጥም አረፋ ይደፍቅ ጀመር።
21ኢየሱስም የልጁን አባት፣ «ከያዘው ስንት ጊዜ ነው?» ብሎ ጠየቀው።
እርሱም እንዲህ አለው፤ «ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው፤
22ሊገድለው ፈልጐ ብዙ ጊዜ
እሳትም ውስጥ ውሃም ውስጥ ይጥለዋል፤ የሚቻልህ ከሆነ ራራልን፤ ርዳንም።»
23ኢየሱስም፣ «የሚቻልህ ከሆነ አልህ? ለሚያምን ሰው ሁሉም ነገር ይቻላል»
አለው።
24ወዲያውኑ የልጁ አባት፣ «አምናለሁ፤ አለማመኔን ርዳው!» በማለት ጮኸ።

ጋኔኑ ጥቂት ጊዜ ብቻ እንደ ቀረው ዐውቋል። ስለሆነም በቀረው የመጨረሻ ዕድሉ ለመጠቀም ያህል ልጁን ወደ መሬት ጣለው። ውሃ ውስጥ ሊያሰጥመውና እስኪሞት ድረስ እሳት ላይ ሊጥለው ብዙ ጊዜ ከዚህ የባሰ ነገር ያደርግ ነበር። ተስፋ መቁረጥ የተጫጫነው አባት ሁኔታ በእርግጥ አሳዛኝ ነበር። ምናልባትም ችግሩን ራሱ ላይ ከማድረግ ይልቅ ኢየሱስ ላይ ያደረገው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ተግባሩ እምነትን ቢያሳይም፣ «የሚቻልህ ከሆነ …» የሚለው አነጋገሩ ግን ተጠራጣሪነቱን ያመለክት ነበር።



ከአንደበት የሚወጡ ቃላት የመልእክቱን ትርጉም ከሚያመለክቱበት ምንባቦች አንዱ ይህ ነው። ኢየሱስ፣ «የሚቻልህ ከሆነ አልህ?» ሲል፣ «ችሎታዬን ተጠራጠርህ?» ማለቱ ነበር ወይስ፣ «የሚቻልህ ከሆነ!» ሲል፣ «አዎን ማድረግ እችላለሁ። ጥያቄው ግን መቀበል እንድትችል ማመን ያለማመንህ ነው!» ማለቱ ይሆን? ፈውስ ከጠያቂው እምነት ጋር ተያይዞ ከቀረበበት ጊዜ አንዱ ይህ ነው።[79] የዚህ ሰው ጩኸት በማንኛውም ክርስቲያን ልብ ውስጥ ሲያስተጋባ የሚኖር ነው። ይህ ዐይነት ስሜት ተሰምቶት የሚያውቅ ማነው? «አምናለሁ፤ አለማመኔን ግን ርዳው!» ወደ ኢየሱስ ለመምጣት የተወሰነ እምነት መጠን ሊኖረን ይገባል። ይሁን እንጂ እፊታችን ላለው ተግባር የማይበቃ ደካማና ዐቅመ ቢስ ነው። ኢየሱስ በልባችን ክፍ ሊል የጎደለንን እምነት ሊሰጠን ይገባል።

**ማር 9፥25-29**
**ከማቴ 17፥18፣20፤**
**ሉቃ 9፥42-43 ጋር**

25ኢየሱስ ሕዝቡ ወደዚያ እየተንጋጋ በሩጫ
መምጣቱን ባየ ጊዜ፣ «አንተ ደንቆሮና ዲዳ መንፈስ
ከእርሱ ውጣ! ከእንግዲህም ተመልሰህ እንዳትገባበት
አዝሃለሁ!» ብሎ ርኩሱን መንፈስ ገሠጸው።
26ርኩሱም መንፈስ እየጮኸ ክፉኛ ካንፈራገጠው በኋላ ከልጁ ወጣ፤ ብዙዎቹ
«ሞቶአል» እስኪሉ ድረስ ልጁ እንደ በድን ሆነ።
27ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው፤
ልጁም ተነሥቶ ቆመ። [ልጁም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነ[ማቴ]] [ለአባቱም መልሶ
ሰጠው። ሰዎቹም ሁሉ በእግዚአብሔር ታላቅነት ተገረሙ[ሉቃ]]።

[79] ፈውስን ወይም የጸሎትን መልስ ለመቀበል እምነት ምንጊዜም አስፈላጊ ነው (ማቴ 9፥22፤ 21፥22፤ ማር 6፥5-6፤ 10፥52፤ ሉቃ 7፥36-50፤ 17፥19፤ ሐሥ 14፥8-9፤ ያዕ 1፥6-8)። ሆኖም አንዳንዴ፣ ፈውስ የሚገኘው በጓደኛ ወይም ከቤተ ሰብ አባል በአንዱ እምነት ምክንያት ይሆናል (ማቴ 8፥5-13፤ 15፥28፤ ማር 2፥5፤ 9፥22-24፤ ሉቃ 8፥40-42፣49-56፤ ያዕ 5፥15)። አንዳንዴ የተፈዋሹን ሳይሆን የፈዋሹን እምነት መሠረት ያደረገ ሊሆን ይችላል (ሉቃ 7፥11-16፤ 8፥26-33፤ ዮሐ 5፥1-9፤ 11፤ ሐሥ 3፥1-8፤ 9፥36-43፤ 20፥1-12)።

28ኢየሱስ ወደ ቤት ከገባ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርት ለብቻቸው፣ «እኛ ልናስወጣው ያልቻልነው ለምንድን ነው?» ብለው ጠየቁት::

29እርሱም፣ [እምነታችሁ በማነሱ ምክንያት ነው፤ እላችኋለሁ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ፣ ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁም ነገር አይኖርም[ማ+]] «የዚህ ዐይነቱ ሲወጣ የሚችለው በጸሎትና በጾም ብቻ ነው» አላቸው::

በዚህ ጊዜ በኢየሱስ ዙሪያ ብዙ ሕዝብ ነበረ:: ሌሎች ብዙዎች ደግሞ ከየገበያውና ከየነበሩበት ቦታ እየመጡ ነበር:: የሰዎች ብዛት ሌሎችንም ይጠራል:: የሚሆነውን ለማየት የተሰበሰቡ ሰዎች ብዛት ይበልጥ እየጨመረ እያለ የበለጠ ኹካታ ከመፈጠሩ በፊት ነገሩ ቶሎ እንዲያበቃ ፈለገ:: ኢየሱስ በተግባሩ መንፈሱን ካወቀ በኋላ እንዲወጣ አዘዘው:: ጋኔኑ ከመታዘዝ ሌላ አማራጭ የለውም:: ሕዝቡ በእግዚአብሔር ኀይል ተደነቁ:: ጸሐፍት ያስነሡት ክርክር ማብቃቱ በግልጽ ይታይ ነበር:: አንድ አንድ እያሉ ከዚያ ቦታ ሳይሄዱ እንዳልቀረ ማሰብ ይቻላል::

በዚህ ቀን ተሸናፊዎቹ ጸሐፍት ብቻ አይደሉም:: ዘጠኙ ደቀ መዛሙርቱም ቢሆኑ ክፉኛ ተጐድተዋል:: ምናልባት ሦስቱ በመጠኑም ቢሆን ሊያጽናኑዋቸው እንደሚችሉ እናስብ ይሆናል:: ሆኖም እነርሱም ቢሆኑ፣ ከተራራው የወረዱት የተገሠጸ ሰው ዐይነት ስሜት ይዘው ነበር:: የኢየሱስን ሞትና ኤልያስን ለተመለከቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ካለመቻላቸውም በላይ፣ ከሰማይ በመጣው ድምፅ እንኳ ሳይቀር ተገሥጸዋል::[80]

80 ካርሰን፣ እንደሚለው (ገጽ 390) የደቀ መዛሙርቱ ውድቀት በዚህ ክፍል በተደጋጋሚ የሚታይ ዐቢይ ሐሳብ ነው (ማቴ 14÷16-21፣26-27፣28-31፤ 15÷16፣23፣33፤ 16÷5፣22፤ 17÷4፣10-11)::



ቤት ውስጥ ብቻቸውን በነበሩ ጊዜ (ከማቴ 13÷36፤ 15÷12 ጋር ያነ)፣ «ችግሩ ምንድንነው? እኛ ልናስወጣው ያልቻልነው ለምድንነው?» በማለት ሊጠይቁት በጣም ጓጉተዋል:: አንዳንድ ዘዴዎችን ባለመከተላቸው ነበር? ኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ የጋኔኑን ማንነት ማወቅ ስለ ነበረባቸው ይሆን? ምናልባት ይህ ጋኔን ተጨማሪ ትግል የሚጠይቅ የተለየ ዐይነት ስለሆነ ይሆን? ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ከኢየሱስ ስም ጋር የተያያዘ አንድ ዐይነት ቀመር ስለ ጐደለ ይሆን? በፍጹም! ችግሩ ዘዴን ወይም ስልትን ያለማሟላት አይደለም:: እምነታቸው ትንሽ ስለ ነበር ነው:: ምናልባት ኢየሱስ በቦታው ባለ መኖሩና በራሳቸው በመደገፋቸው የደቀ መዛሙርቱን እምነት አዳክሞአል በማለት እናስብ ይሆናል:: በጣም ትንሽ የተባለ እምነት እንኳ፣ (ትንሽነትን ለማመልከት፣ «የሰናፍጭ ዘር» እንኳ ምሳሌ ቀርቧል) ትልልቅ ችግሮችን (ለምሳሌ፣ «በተራራ» የተመሰለውን ያህል) ማሸነፍ ይችላል:: እዚህ ላይ ኢየሱስ በምሳሌያዊ ሁኔታ እየተናገረ ነበር:: ተራራን ማንቀሳቀስ ትልቅ ነገር ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም የሚያስገኘው ጥቅም የለም:: ስለሆነም፣ እግዚአብሔርን ጨምሮ ማንም ይህን አላደረገም:: ሆኖም በመለወጥ ተራራ ጥላ ሥር ሆኖ እንዲህ መናገሩ ነገሩን ጉልህ አድርጎ ለማሳየት ሳይጠቅም አልቀረም::

«የሚሳናችሁ አይኖርም» በማለት ኢየሱስ የሰጠው ተስፋ ፍጹማዊ አይደለም:: እንደ አላዲን ፋኖስ አስማታዊ ኀይል ያለው አይደለም፤ እንደ ዕቅዱና አስፈላጊነቱ ይወሰናል:: ይህ መወሰን ያለበት፣ (1) ኢየሱስ እንድናደርገው ሥልጣን በሰጠን ሁኔታ፣ እና (2) ተመሳሳይ ሐሳብ ባላቸው ሌሎች ምንባቦች ነው (ለምሳሌ 1ቆሮ 6÷12፤ ፊልጵ 4÷12-13)::

አጋንንት የማስወጣት ሥርዓት አካል በመሆኑ ሳይሆን፣ ለመንፈሳዊ ውጊያ በየዕለቱ ዝግጁ ሆኖ በመገኘት ረገድ ዘጠኙን ደቀ

መዛሙርት ሊረዳቸው የሚችል ጸሎት[81] ነበር:: በሌላ አነጋገር፣ በየዕለቱ ዝግጁ እንዲሆኑ እንጂ አጋንንትን ለማስወጣት እንዲጸልዩ ኢየሱስ መመሪያ አይሰጣቸውም ነበር:: ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ውጊያ የሚሸነፉት ለውጊያ የሚያስፈልገውን መሣሪያ ባለ ማወቃቸው ሳይሆን ምቾት ፈላጊዎች፣ ሰነፎችና ራስን በመግዛት ባለ መኖራቸው ነው::

**§ 88**
**ስለ ኢየሱስ መከራ ለሁለተኛ ጊዜ መነገሩ**
**(ማቴ 17፥22-23፤ ማር 9፥30-32፤ ሉቃ 9፥43-45)**
**[ከ§ 83 እና 86 ጋር ያነ]**

30ከዚያም ተነሥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤
ኢየሱስም ያሉበትን ስፍራ ማንም እንዲያውቅ አልፈለገም፤
31ለደቀ መዛሙርቱ፣ «የሰው ልጅ በሰዎች እጅ ዐልፎ
ይሰጣል፤ እነርሱም ይገድሉታል፤ ከሦስት ቀንም በኋላ
[በሦስተኛው ቀን[ማቴ]] ይነሣል» እያለ ያስተምራቸው ነበር::
32እነርሱ ግን የሚላቸው አልገባቸውም፤ [እንዳያስተውሉ
ነገሩ ተሰውሮባቸው ነበር[ሉቃ]] እንዳይጠይቁትም ፈሩ::
[ደቀ መዛሙርቱም እጅግ አዘኑ[ማቴ]]::

ጋኔን የነበረበትን ልጅ በአስደናቂ ሁኔታ መፈወሱ ካስከተለው ውጤት የተነሣ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን በግል ለማስተማር አዳጋች ሆኖበታል:: የጸሐፍት እዚያ መገኘት ደግሞ ነገሮችን አባብሶአል:: ሌላው ቢቀር በሩን እንካ ዘግተው መቀመጥ ወደሚችሉበት ወደ ቅፍርናሆም፣ ምናልባትም ወደ ጴጥሮስ ቤት ሄዱ:: ለሐዋርያቱ ይህ ከባድ ጊዜ ነበር:: ኢየሱስ ከዚያ በፊት አድርጐት በማያውቅ ሁኔታ ስለሚመጣው መከራውና ስለ ክብሩ ገልጾላቸዋል:: ዐሥራ ሁለቱ ይህን አዲስ መገለጽ አለመቀበላቸው ግልጽ ነበር፤ ሆኖም ግን የግድ መቀበል ነበረባቸው::

[81] «ጾም» የሚለው ምናልባትም በጸሐፊው የተጨመረ ሊሆን ይችላል:: በጥንቱ ቅጂ አልተገኘም:: እርሱ እስከሚሞት ድረስ ደቀ መዛሙርቱ መጾም እንደሌለባቸው ኢየሱስ ተናግሮ ነበር (ማቴ 9፥15):: የጥንት ክርስቲያናት ጾምን ማዘውተር እዚህ ላይ ጾምን ለማከል ምክንያተ ሆኖ ሊሆን ይችላል::



ስለሆነም ኢየሱስ ወደ መስቀሉ እየተቃረበ ባለበት በዚህ ወቅት ብቻቸውን ከእርሱ ጋር መሆናቸው አስፈላጊ ነበር::

ኢየሱስ ስለ ሞቱ በግልጽ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረ:: ምንም እንኳ በዚህ ምንባብ ይህን ያህል አዲስ ነገር ባይኖርም ጥቂት ነገሮችን ማየት ይቻላል:: በመጀመሪያ ባለፈው ጊዜ የተነገረውን ማቴዎስ፣ «በሦስተኛው ቀን» በማለት ሲያቀርበው፣ ሉቃስ ግን፣ «ከሦስት ቀንም በኋላ» ብሏል:: ሦስት ቀን ሲል ቁርጥ ያለ ጊዜ ለማመልከት ታስቦ ሳይሆን የተወሰነ ጊዜ ማለቱ እንደ ነበር ግልጽ ሆኗል::

ሁለተኛ፣ ይህን ምንባብ ቀደም ሲል ከተደረገው ተአምር ጋር የሚያያይዘው ሉቃስ ብቻ ነው (ሉቃ 9፥43):: ሉቃስ በሚያቀርበው መልኩ ለሁለተኛ ጊዜ የተነገረው ይህ ትንቢት ለሁሉም የተነገረ ነበር ማለት (ከማር 9፥30-31 ጋር ያነ) ምናልባት ትክክል ላይሆን ይችላል:: በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል ከነበረወ ሁኔታ ለይቶ ማቅረቡም ትክክል ላይሆን ይችላል:: የመጀመሪያው ትንቢት የጴጥሮስን ታላቅ ምስክርነት ተከትሎ፣ ስለ መሲሑ ተግባር ለነበራቸው የተሳሳተ አስተሳሰብ፣ «ማስተካከያ» እንዲሆን የተነገረ ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ ሁለተኛውም ትንቢት «ማስተካከያ» እንዲሆን የመለወጡንና ከአጋንንት ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጦ ማሸነፉን ተከትሎ የተነገረ ነበር::

በሦስተኛ ደረጃ፣ ሁለተኛው ትንቢት ኢየሱስ መከራ ከመቀበሉ በፊት ዐልፎ እንደሚሰጥ ይገልጻል:: ፓራዲዶሚ [Paradidomi] የሚለው ቃል አሻሚ ትርጉም ያለው ነው:: አዲሱ መደበኛ ትርጉም በኢየሱስ ሞት ይሁዳ የነበረውን ድርሻ በሚያመለክት መልኩ፣ «ዐልፎ ይሰጣል» ይላል:: ይሁን እንጂ፣ በኢየሱስ ሞት እግዚአብሔር ያለውን ድርሻ በሚያመለክት መልኩ፣ «ተሰጠ» ወይም፣ «አስረከበ» ማለት ሊሆን ይችላል:: ሁለቱም ወገኖች ስለ ነበራቸው ድርሻ ቢያመለክት ኖሮ አስገራሚ ሊሆን አይችልም (ከሐሥ 2፥23 ጋር ያነ):: አርጌነስ

እንደሚለው፣ «በሰዎች እጅ» የሚለው ሐረግ ከይሁዳ ይልቅ በበለጠ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ድርሻ የሚያመለክት ይመስላል::

በአራተኛ ደረጃ፣ ደቀ መዛሙርቱ አሁንም ቢሆን የኢየሱስን ትንቢት በሚገባ አልተረዱም:: ሉቃስ ግራ መጋባታቸውን የሚያመለክተው አጽንዖት በመስጠት ነው (9÷45):: ሙሉ በሙሉ የእነርሱ ጥፋት አለመሆኑንም ያመለክታል:: «እንዳያስተውሉ ነገሩ ተሰውሮባቸው ነበር» የሚለው ሐረግ ይህን በማድረግ ረገድ መለኮታዊ አሠራር የነበረውን ድርሻ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪም፣ ኢየሱስን እንዳይጠይቁ ፈርተዋል:: ሁለት ጊዜ ከገለጸላቸው በኋላ እንደገና ቢጠይቁት ማስተዋል ባለመቻላቸው ሊገሥጻቸው እንደሚችል አስበው ይሆናል:: ምናልባትም ነገሩ በትክክል የሚፈጸም መሆኑን አስረግጦ የሚያመለክት ገለጻ እንዳይሰሙ ፈርተው ይሆናል:: ሆኖም ከመጀመሪያ ጊዜ ይልቅ አሁን በመጠኑም ቢሆን መረዳት ችለዋል:: ማቴዎስ እጅግ ማዘናቸውን ይናገራል (17÷23):: ዝርዝር ነገሮችን ባያውቁም እንኳ አስቸጋሪ ሁኔታ እየመጣ መሆኑን ለመገንዘብ የሚያስችላቸውን ያህል ዐውቀዋል::

**§ 89**
**ጴጥሮስ የቤተ መቅደሱን ግብር መክፈሉ**
**(ማቴ 17÷24-27)**

[24]ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ቅፍርናሆም ከደረሱ በኋላ፣ የቤተ መቅደሱ ግብር ተቀባዮች ወደ ጴጥሮስ ቀርበው፣ «መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር አይከፍልምን?» አሉት::

ይህን ያልተለመደ ሁኔታ ያሰፈረው ብቸኛ ወንጌላዊ ቀረጥ ሰብሳቢው ሌዊ መሆኑ ይህን ያህል ሊያስገርመን አይገባም:: ለእንዲህ ዓይነቱ ያልተለመደ ግብር አሰባሰብ ዘዴ ትኩረት ከመስጠቱ ባሻገር፣ ታሪኩን ያሰፈረው ለምን ነበር? በዚህ ላይ የታሪኩን ፍሰት ማደናቀፍ ይመስላል:: ረጋ ብለን ስንመረምረው ግን፣ በፊልጶስ ቂሣርያ



የተጀመረው አዝማሚያ ቀጣይ መሆኑን እንረዳለን:: ይህም ሌሎች ኢየሱስን ከፍ ቢያደርጉትም እርሱ ግን ራሱን ዝቅ ማድረጉን ነው:: ይህን ታሪክ የሚያነብ ማንኛውም ሰው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ የቤተ መቅደስ ግብር ይከፍላል ብሎ አያስብም:: ሆኖም እንደዚያ አድርጓል:: ይህ በኢየሱስ ራስን ዝቅ ማድረግና፣ በሚቀጥለው ክፍለ እንደምንመለከተው፣ በደቀ መዛሙርት ራስን ከፍ ማድረግ መካከል ንጽጽር ያደርጋል::

ይህ የተለየ ግብር ሕጋዊው የሮማውያን ግብር አካል አልነበረም:: ይሁን እንጂ፣ ዕድሜው በሃያና በሃምሳ ዓመት መካከል ያለ ማንኛውም ወንድ ለቤተ መቅደሱ ርዳታ የሚሆን ሁለት ዲናር እንዲከፍል አይሁድ ይጠብቁ ነበር (CF. Josephus, *Ant.* 111. 8.2; XVIII, 9.1):: ይህ ዘፀአት 30÷11-16፤ 38÷25-26ን መሠረት ያደረገ ሲሆን የመገናኛውን ድንኳን እንዲረዱ እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ የምናገኘውም በነዚሁ ክፍሎች ነው:: መጠኑ የአንድ ሰው የሁለት ቀን ደመወዝ ያህል ነበር:: አሁን እንዲከፍል የተጠየቀው ለምን ነበር? ባለፈው ፋሲካ ባለ መክፈሉ፣ እንደ አንድ አይሁዳዊ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ መሆኑን በተመለከተ ጥያቄ ተነሥቶ ነበር:: ግብር ሰብሳቢዎቹ ጴጥሮስ ሌሎችን ወክሎ መናገር የሚችል መሆኑን እንዳወቁ ግልጽ ነው:: አጠያየቃቸው አዎንታዊ ምላሽ በመጠበቅ የቀረበ ነበር:: «መምህራችሁ የቤተ መቅደሱን ግብር ከፍሏል፤ አይደለም እንዴ?» በሚል መልኩ ተተርጉሞ ቢሆን ኖሮ የበለጠ ግልጽ ይሆን ነበር:: ሕጋዊ ዕውቅና ያላቸው መምህራን ከዚህ ግብር ነጻ መሆናቸው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው:: ኢየሱስ በትምህርት ቤታቸው የተማረ ስላልነበረ ይህን ጥቅም ማግኘት አይችልም::

25እርሱም፣ «ደከፈላል እንጂ» አላቸው፡፡ ማቴ 17፥25-27
ጴጥሮስ ወደ ቤት እንደ ገባ ኢየሱስ በቀድሚያ፣
«ስምዖን፤ የምድር ነገሥታት ግብር ወይም ቀረጥ
የሚቀበሉት ከራሳቸው ልጆች ወይስ ከሌሎች ደመሰልሃል?»
አለው፡፡
26ጴጥሮስም፣ «ከሌሎች ነው የሚቀበሉት» አለው፡፡
ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ «እንግዲያውስ ልጆች
ነጻ ናቸው፤ 27ሆኖም እንዳናስቀይማቸው ሄደህ
መንጠቆህን ወደ ባሕር ጣል፤ መጀመሪያ የምትይዘውን
ዓሣ አፉን ስትከፍት የምታገኘውን አንድ እስታቴር በእኔና
በአንተ ስም ክፈል፡፡

በእርግጠኝነት መናገር ባንችልም ጴጥሮስ መልስ የሰጠው ክርስቶስ የሚለውን ሳያማክር እንደ ነበር እንገምታለን፡፡ ከዚያ በፊት ኢየሱስ መክፈሉን ጴጥሮስ ያውቅ ይሆናል፡፡ ጴጥሮስ ወደ ቤት ሲገባ፣ መጀመሪያ የተናገረው ኢየሱስ ነበር፡፡ ምናልባት ማቴዎስ ኢየሱስ የጴጥሮስን ሐሳብ ማንበብ መቻሉን ሊያሳየን ፈልጐ ይሆናል፡፡ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት የቤተ መቅደሱን ግብር ለመክፈል ነጻ መሆኑን ለማመልከት ይህን አጭር ምሳሌ መሠረት በማድረግ ነበር ጴጥሮስን የጠየቀው፡፡ ይሁን እንጂ የአይሁድ ባለ ሥልጣኖችን ላለማስቀየም እንደሚከፍል ተናገረ፡፡ ነጻ የሆነው ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን፣ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር በመሆኑ ጴጥሮስም ነጻ ነበር፡፡ ሆኖም፣ እርሱም መክፈል ነበረበት፡፡ ጴጥሮስ የሚያገኘው ገንዘብ ለሁለቱም የሚበቃ እንደ ነበር ልብ በሉ፡፡

ትምህርቱ ግልጽ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ከእነርሱ ጋር በመስማማታችን፣ ወይም ግዴታ ስላለብን ሳይሆን፣ ሕግ እንዳንተላለፍ ለመንግሥት ባለ ሥልጣኖች መገዛት ይኖርብናል፡፡ እንዲህ ባለው ነገር



ጎድሎ መገኘት የቤተ ክርስቲያንን መልካም ስም ያጐድፋል፤ ከባለ ሥልጣናቱ ጋር አላስፈላጊ ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ይህ መርሕ በሮሜ 13 ድጋሚ ተነሥቷል፤ ሆኖም የተለየ ትኩረት የተሰጠው ሃይማኖታዊው ሳይሆን መንግሥታዊው ባለ ሥልጣን ነው (ማቴ 22፥15-22ን ይመ)፡፡ በቅርቡ የፌዴራሉ መንግሥት ገንዘቡን ለአንዳንድ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች ያውለዋል በማለት ጥቂት ክርስቲያኖች ተቃውመው ነበር፡፡ ስለዚህም በንጹሕ ሕሊና ግብራቸውን መክፈል ይችሉ እንደሆን አንዳንዶች ጥያቄ አንሥተው ነበር፡፡ ጳውሎስም ሆነ ኢየሱስ ለፖለቲካና የሃይማኖት ባለ ሥልጣኖች ግብር ከፍለዋል፡፡ የሃይማኖትና የሲቪል ባለ ሥልጣኖች የሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮችን አጥብቀው መቃወም ይችሉ ነበር፡፡ መሪዎች የአገርን ገንዘብ ለመጥፎ ተግባር ቢያውሉ ክርስቲያኖች ግብር መክፈላቸውን ማቆም ወይም መቀነስ ይገባቸዋል፣ የሚለው ክርክር የሚያዋጣ አይደለም፡፡

በተጨማሪም፣ የማያምኑ ሰዎች መጥፎ ተግባራቸውን እንዲያቆሙ ለማስገደድ ክርስቲያኖች ጣልቃ መግባት እንደሚገባቸው መጽሐፈ ቅዱሳዊ ድጋፍ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ ጳውሎስ የአረማውያንን አምልኮ በመቃወም አልተናገረም (ሐሥ 19፥37)፡፡ እንዲህ ያለው ጣልቃ ገብነት ከአንዳንድ ምክንያቶች የተነሣ አግባብ ያልሆነና ማስተዋል የጐደለው ይሆን ነበር፤ ለመጥቀስም፡- (ሀ) የአካባቢው ሰዎች ክርስትና ሕገ ወጥ ነው በማለት ሊከራከሩ ይችላሉ፤ (ለ) ለመቀበል የሚያስችል መሠረት በሌላቸው ላይ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን መጫን ይሆን ነበር፤ (ሐ) መንፈሳዊ ጠላትን ሥጋዊ ጠላት አድርጐ የማሰብ አዝማሚያ ይኖር ነበር፡፡

ቀጥሎ ይበልጥ ተገቢ የሚሆኑ ምላሾችን እንመለከታለን፡-

(1) በማኅበረ ሰቡ ያሉ ችግረኞችን መርዳት (ለምሳሌ ለወላጆች እንክብካቤ ማድረግን፣ ለረሃብተኞች ምግብ መስጠትን፣

የምክር አገልግሎትና ማይምነትን የማስወገድ ፕሮግራም ማቋቋምና ሌሎች)::

(2) በሚቻለው መንገድ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ማወጅ (ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማደል፣ በመጽሔቶችና በራሪ ጽሑፎችን በመሳሰሉ)::

(3) በተደራጀ መልክ የፖለቲካን ባለ ሥልጣኖችን ማናገር እንዲቻል የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ማድረግ (ደብዳቤ በመጻፍ፣ ለመራጮች ትምህርት መስጠትና አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ ክርስቲያኖችን በመቀስቀስ)::

(4) በሕጋዊ ሁኔታ ተቃውሞን ማቅረብና ቀና አማራጭን ማሳየት:: ዓለም ክርስቲያኖች የሚጠሉትን በሚገባ ያውቃል፤ ብዙ ጊዜ ግን የምንወደውን አያውቁም::

(5) ጸረ ክርስቲያን የሆኑ አስተሳሰቦችን በሚያደፋፍሩ ድርጅቶች ላይ የኤኮኖሚ አድማ ማድረግ::

ክርስቲያኖች ሕዝባዊ ዐድማ ማድረግ የሚኖርባቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በቀጥታ የሚጻረር ነገር እንዲያደርጉ የታዘዙ እንደሆነ ብቻ ነው (ዘፀ 1፥15፤ ዳን 3፥1፤ 6፥10፤ ሐሥ 4፥19፤ 5፥29)::

አሁን ወደ ዐውዱ እንመለስ:: ማቴዎስ ታሪኩን የሚያቆመው ጴጥሮስ ሄዶ ዐሣውን ማጥመዱ ላይ ነው:: እንደ ታዘዘው ሄዶ አፉ ውስጥ ሁለት ዲናር የያዘ ዓሣ ማጥመዱን መረዳት አለብን:: ብዙ ጊዜ ዓሣዎች ወደሚያብለጨልጭ ነገር ይሳባሉ:: በገሊላ ባሕር ሳንቲም የዋጠ ዓሣ ስለ መያዙ የሚታወቅ ታሪክ አለ:: ምናልባትም ኢየሱስ ጴጥሮስ ያንን ዓሣ ከማጥመዱና ሁለቱንም ይዞ ከመምጣቱ በፊት፣ «ዐይቶ» ሊሆን ይችላል::[82]

---

[82] ሁለተኛው አማራጭ፣ «ሄደህ ዓሣዎች አጥምድና ከሸጥህ በኋላ ገንዘቡን ለተጠየቅነው ግብር ክፈል» በማለት በፈሊጣዊ ቋንቋ ኢየሱስ ለጴጥሮስ መናገሩ ሊሆን ይችላል የሚል ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ትክክል አለመሆኑን



**§ 90**
**ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው በሚል የተደረገ ውይይት**

**ማቴ 18፥1-5**
**ማር 9፥33-37፤**
**ሉቃ 9፥46-48**

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከመለወጥ ተራራ ወደ ቅፍርናሆም እየተመለሱ ነው:: መንገድ ላይ ደቀ መዛሙርቱ ከመካከላቸው የሚበልጠው ማን እንደ ሆነ እየተከራከሩ ነበር:: ምንኛ አሳፋሪ ነው! የወደ ፊት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ክርስቲያናዊ ያልሆነ ነገር ማድረጋቸው ያስደነግጠናል:: ይሁን እንጂ እንዲህ ያለ ክርክር ያደረጉት ሦስት ሲሆን፣ ይህም የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አልነበረም (ከ§125ለ እና 144 ጋር ያነ):: ነገሩን አሳዛኝ የሚያደርገው ደግሞ በእያንዳንዱ ጊዜ ይህን ያደረጉት ኢየሱሰ ስለ መከራው የተናገረውን ትንቢት ተከትሎ መሆኑ ነው:: ስለዚህ፣ ኢየሱስ ሕይወቱን ስለ መስጠት ሲናገር እነርሱ ግን ለሕይወታቸው እያሰቡ ነበር ማለት ነው::

**ማር 9፥33-35**
**ማቴ 18፥1፤ ሉቃ 9፥47 ጋር**

[33]ከዚህ በኋላ ወደ ቅፍርናሆም መጡ:: ቤት
ከገባ በኋላም፣ [ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣
«በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?» ብለው
ጠየቁት[ማቴ]] «በመንገድ ላይ የምትከራከሩት ስለ ምን
ነበር?» ብሎ ጠየቃቸው:: [34]እነርሱ ግን በመንገድ ላይ
የተከራከሩት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው? በሚል ስለ ነበር
ዝም አሉ:: [35]ከተቀመጠ በኋላ [የልባቸውን ሐሳብ ተረድቶ[ሉቃ]] ዐሥራ ሁለቱን ጠርቶ፣
«መጀመሪያ ለመሆን የሚፈልግ ከሁሉ መጨረሻና የሁሉም አገልጋይ ይሁን» አላቸው::

---

የሚያሳየው ኢየሱስ ዓሣውን እንዲያጠምድ የነገረው በመረብ ሳይሆን በመንጠቆ መሆኑ ነው (አዲስ ኪዳን ውስጥ መንጠቆ የተጠቀሰው እዚህ ቦታ ብቻ ነው):: በአንድ ጊዜ ብዙ ዓሣዎችን የሚይዝ መረብ ያንን ያህል ዓሣ በቀላሉ መያዝ ይችላል (ከሉቃ 5፥1-11 ጋር ያነ):: መንጠቆ የሆነ እንደሆን ግን ቀኑን ሙሉ ቢደከምም ዓሣውን የመያዝ ዕድሉ በጣም ያነሰ ነው የሚሆነው::

ማቴዎስ ንግግሩን የጀመሩ ደቀ መዛሙርቱ መሆናቸውን ነው የሚነግረን። ማርቆስና ሉቃስ ግን ኢየሱስ መሆኑን ያመለክታሉ። ሁኔታውን በሚከተለው መልኩ መግለጽ ይቻላል፤ ሐሳባቸውን የተረዳው ኢየሱስ (ሉቃስ) መንገድ ላይ እየተነጋገሩ የነበረው ስለ ምን እንደ ነበር ጠየቃቸው። በከንቱ አስተሳሰባቸውና በአጉል ተፎካካሪነታቸው ያፈሩት ደቀ መዛሙርት መልስ አልሰጡትም (ማርቆስ)። ከዚያ በኋላ ከመካከላቸው አንዱ፣ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ የሚሆነው ማነው? የሚል ጥያቄ በማቅረብ ዝምታውን ሰበረ (ከማቴዎስ 5፥19፤ 11፥11 ጋር ያነ)። ኢየሱስ መንግሥቱን ወደ ማወጅ እየተቃረበ ባለበት ጊዜ ይህ ጥያቄ ለደቀ መዛሙርቱ ይበልጥ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል።

ይህ በሃይማኖት መምህራኑ መካከል የተለመደ ውይይት ነበር። ይሁን እንጂ ከዚህ በስተ ጀርባ ያለው ዝንባሌ ለአይሁድ ሃይማኖት በፍጹም እንግዳ ነገር አልነበረም። ራስን ማስቀደም ለአብዛኞቹ ሰዎች የተለመደ ጉዳይ ነው። ቀዳሚውን ቦታ፣ የሚመቸውን ስፍራና የተሻለውን እንጀራ እንድንፈልግ የሚያደርገን ይኸው ዝንባሌ ነው። እንዲህ ያለው ዝንባሌ እኛ ውስጥ ሲሆን፣ የተለመደና ተፈጥሮአዊ ይመስለናል፤ ሌሎች ውስጥ ስናየው ግን ያበሳጨናል። እንዲያውም ወላጆችና አስተማሪዎች እንኳ ሳይቀሩ እንዲህ ያለውን ሐሳብ ያበረታታሉ። ኢየሱስ ግን እንዲህ ያለውን ሽፍንፍን ዘልቆ ያያል። የጋጠ ወጥነት፣ የራስ ወዳድነት፣ የጦርነት፣ የስግብግብነት፣ የዐድማ፣ የምቀኝነትና ሌሎችም ምክንያት ይህ ሁሉን ለእኔ ባይነት ነው። እንዲያውም ራስን አዋርዶ የማየት ምክንያትም ነው። ራስን አዋርዶ የማየት ችግር ሰውየው ራሱን ዝቅ አድርጐ ማሰቡ ሳይሆን ስለ ራሱ የተጋነነ ሐሳብ ያለው መሆኑ ነው። ዐይኖቻችንን ወደ ላይ ስናነሣና ሌሎችን ስናገለግል ግን ለራሳችን በማዘንና ራሳችንን በማዋረድ ስሜት በፍጹም አንጠቃም።



ሁሉን ለእኔ ባይነት ለሔዋን ውድቀትም ምክንያት ነበር። የተታለለችው በፍሬው ማማር ወይም በምግብ ይዘቱ አልነበረም። የተታለለችው፣ «እንደ እግዚአብሔር» ትሆናላችሁ በሚለው ሐሳብ ነበር። እንደ እግዚአብሔር ከሆነች ከማንም በታች አትሆንም፣ ሁሉን መቆጣጠር፣ አስበችው ቦታ መድረስ፣ የራሷን ዕጣ ፈንታ መወሰን ትችላለች። አብዛኛው የዘመናችን ማስታወቂያም ወደዚሁ ዓይነት ከንቱነት ነው የሚጋብዘን። «ውድ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ይገባሃል»፣ «ዛሬ ማረፍ ይገባሃል»፣ «በራስህ መንገድ አድርገው!» ይሉናል። ራስን ማስቀደም ሁሉንም ኀጢአት የሚያስተሳስር ገመድ ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም፣ ራስን የማስቀደም መሠረታዊ ክፋት በባሕላችን ተቀባይነት ያለው በመሆኑና በሰዎች አስተሳሰብ ዘልቆ በመግባቱ ተሸፋፍኖ ኖሯል።

ኢየሱስ የመረጣቸው እነዚህ ዐሥራ ሁለት ሰዎች ይንቁት ከነበረው የሚንጫጫ ሕዝብ የተሻሉ አልነበሩም። ማን እንደሚበልጥ እየተከራከሩ ነበር። በኢየሱስ ቀኝና ግራ የሚቀመጥ ማነው? እርሱ የበለጠውን ቦታ እንደሚይዝ ጴጥሮስ በቂ ምክንያት ማቅረብ እንደሚችል አይጠረጠርም። እንዲያውም የመንግሥተ ሰማይ መክፈቻዎች የተሰጡት፤ በውሃ ላይ የተራመደ፤ «ጌታ ሆይ፣ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ» ያለ እርሱ ነበር። በአንጻሩ ደግሞ ሌሎቹ፣ «አዎን፣ ኢየሱስ 'ሰይጣን' በማለትም የጠራው አንተን ራስህን ነበር። አጉል በውሃ ላይ እራመዳለሁ ብለህ ከመስጠም ለጥቂት ያመለጥህ አንተ ነበርህ። በመለወጥ ተራራ ላይ ሦስት ዳሶች የመሥራትን ከንቱ ሐሳብ ያቀረብህ አንተ ነበርህ» ይሉታል። ዮሐንስና ያዕቆብም የበለጠውን ድርሻ መውሰድ እንዳለባቸው እንደ ተከራከሩ አይጠረጠርም። እንዲያውም ከዐሥራ ሁለቱ የበለጠ ስፍራ እንዲሰጣቸው እንድትረዳቸው በቅርቡ እናታቸውን ወደ ኢየሱስ ሊልኩ

ነው (ማቴ 20÷20-24):: «በምርጦቹ ሦስት» መካከል ከማንም የበለጠ የማኅበር ድርሻ የነበራቸው እነርሱ ነበሩ:: የአስቆሮቱ ይሁዳም የሁለት ሳንቲም መዋጮ እንዳደረገ ጥርጥር የለውም::

እዚህ ላይ ኢየሱስ ወደ ፊት ደጋግሞ የሚያነሣውን አዲስ ሥነ መለኮት ያስተዋውቃል:: ይህም፣ የትሕትና ሥነ መለኮት» ተብሎ ሊጠራ ይችላል:: «ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞች፣ ብዙ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ» (ማቴ 19÷30፤ 20÷8፣16፣27፤ ማር 9÷35፤ 10÷31፣44፤ ሉቃ 13÷30፤ 22÷26):: «ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ፣ አገልጋያችሁ ይሁን» (ማቴ 20÷26፤ 23÷11፤ ማር 10÷43፤ ሉቃ 9÷48፤ 22÷26-27፤ 1ጢሞ 3÷13):: «እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ» (ማቴ 23÷12፤ ሉቃ 14÷11፤ 18÷14፤ ያዕ 4÷10፤ 1ጴጥ 5÷5፣6)[83] በሚሉና በመሳሰሉት ሐረጐች ተደጋግሞ ተነሥቷል:: ኢየሱስ የሰው ልጆችን ከግምት በላይ የሆነ ታላቅ እሴት የሚያየው በዚህ ነገረ መለኮት ውስጥ ነው:: ታናናሾችና በኀጢአታቸው የጠፉትም፣ ማለትም አመንዝራዎች፣ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አካለ ስንኩላን፣ ለምጻሞች፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎች፣ ሳምራውያንና የባዕድ አገር ዜጐች ጭምር ሰዎች ሁሉ ለኢየሱስ የከበሩ ናቸው:: ይህ፣ «የትሕትና ነገረ መለኮት» መረዳት በማያስቸግር ሁኔታ ቀለል ባለ ቋንቋ ተገልጾአል:: ሆኖም ተግባር ላይ ማዋል ቀላል ቢመስልም በጣም አዳጋች ነው:: የእኛ በአእምሮ የመረዳታችን ደረጃ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም:: የትሕትናን ነገረ መለኮት በተጨባጭ ሁኔታ መረዳት ካልቻልን ዮሐንስ 3÷16 የመሳሰሉትን በጣም ቀላል ነገረ

---

[83] ይህ ነገረ መለኮት፣ ማቴ 11÷29፤ ሮሜ 12÷16፤ ኤፌ 4÷2፤ ፊልጵ 2÷3-11፤ ቈላ 3÷12 በመሳሰሉ ምንባቦችም ትምህርት ተሰጥቶበታል:: ይህን ትምህርት በብሉይ ኪዳንም መመልከት ይቻላል (መዝ 18÷27፤ 147÷6፤ ምሳ 16÷18-19፤ 18÷22፤ 29÷23፤ ኢሳ 2÷11-17፤ 53÷10-12፤ 57÷15፤ ሕዝ 17፡24፤ 21÷26)::



መለኮታዊ እውነቶች እንኳ ማስተዋል ሊያስቸግረን ይችላል:: ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ይወደናል የሚለውን እውነት መቀበል ይችላሉ:: ጠበኛ ጐረቤቶቻቸውን ግን እንደሚወድ ግን ለማሰብ እንኳ ያዳግታቸዋል:: የአንድ አገር ልጆች ብቻ የተሰበሰቡበት፣ የሳሳ ማኅበረ ሰባዊ ግንኙነት ያላቸውና በገንዘብ ጉዳይ ጠባብ አመለካከት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በትሕትና ነገረ መለኮት ያለንን አሳዛኝ አለመረዳት ያጋልጡብናል:: እንደ ዐሥራ ሁለቱ ሁሉ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ እንድንመጣ ያቀረበውን ጥሪ ለመረዳት ብዙ ርቀት መጓዝ ያስፈልገናል::

**ማቴ 18÷2-4**
**ማር 9÷36-37 ጋር**

[2]ኢየሱስ አንድ ሕፃን ጠርቶ በመካከላቸው አቆመና፣ [አምጥቶ[ማር]] እንዲህ አላቸው፤ [3]እውነት እላችኋለሁ፤ ካልተለወጣችሁ እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ፈጽሞ ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም:: [4]ስለዚህ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው::

**ሉቃ 9÷48**

[48]ይህን ሕፃን [ከእነዚህ ሕፃናት አንዱን[ማር]] በስሜ የሚቀበል ማንም ቢኖር እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል ደግሞ የላከኝን ይቀበላል፤ ከሁላችሁ የሚያንስ እርሱ ከሁሉ ይበልጣልና::

በአይናቸው እያዩ እንዲማሩ በማሰብ ኢየሱስ አንድ ሕፃን በመካከላቸው አቆመ:: ሕፃኑን ወደ ደረቱ አስጠግቶ አቀፈው በጭኑ ላይ ሳያስቀምጠው አይቀርም (ማር 10÷16):: ከዚያ በኋላ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት እንደ ሕፃን መሆን እንደሚገባ የገለጸበትን የተደነቀ ቃሉን ተናገረ:: ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ሕፃናት ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው ስለነበሩ ኢየሱስ እንዲህ መናገሩ የሚገርም ነው::

በአረማይክ ቋንቋ፣ «ሕፃናት» ለማለትና፣ «አገልጋይ» ለማለት የሚጠቀሙበት ቃል አንድ ነበር:: ለስለስ ያለው ንግግሩ የመልእክቱን ጠንካራነት ሊጋርድብን አይገባም:: ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን እያስጠነቀቀ ነበር:: አመለካከታቸው ካልተለወጠ፣ እነርሱም እንኳ ወደ መንግሥተ ሰማይ ላይገቡ ይችላሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ከመካከላቸው አንዱ ወደ መንግሥተ ሰማያት አልገባም!

ኢየሱስ እንደ ሕፃናት እንድንሆን እንጂ፣ ሕፃናት እንድንሆን አልጠራንም:: ብልኖች (ማቴ 10÷16)፣ እንዲያውም፣ «ልባሞች» (ሉቃ 16÷1-9) መሆን አለብን:: እየተመለከትን ያለነው ዐውድ ከዚህም የላቀ መልእክት አለው:: ምንም እንኳ ሕፃናት ራስ ወዳድና ተፎካካሪዎች ቢሆኑም (እንደ ደቀ መዛሙርቱ)፣ የክብር ቦታ ለመያዝ ይህን ያህል የሚያሳስባቸው አይደሉም (ከደቀ መዛሙርቱ በተለየ መልኩ):: በንፁሕ ወይም በአዳፋ ልብስ አለዚያም በቆዳ ቀለም አያገሉም:: በውጫዊ ሁኔታ የሚፈርዱ ባለ መሆናቸው፣ ባሕርይን በተመለከተ ትክክለኛ ዳኞች ናቸው:: በተጨማሪም በዋነኛነት ተቀባይነት ለማግኘት የሚፈልጉት ከወላጆቻቸው ዘንድ ነው:: ከሰማዩ አባታችን ብቻ ተቀባይነት ለማግኘት ተንቀሳቅሰን ቢሆን ኖሮ ቤታችንና አገልግሎታችን ምን ያህል ይለወጥ ነበር! እንዲህ ያለ ባሕርይ ቢኖረን ኖሮ ራሳችንን በመንግሥተ ሰማይ መሓል እናገኘው ነበር::


**§ 91ሀ**
**በመንግሥቱ ውስጥ የሌሎች ሠራተኞች እንቅፋት መሆን (ሉቃ 9÷49-50)**

«የታናናሾች አስፈላጊነት» እና እነርሱን የማሰናከል አደገኛነት በሚል የወል ርእስ ጉዳይ የተያያዘውን ክፍል 91 እዚህ ላይ በሦስት ክፍል ተከፍሏል:: ሦስቱ ተነፃፃሪ ወንጌሎች በዚህ ነጥብ ላይ የተለየ አጽንዖት ሰጥተዋል፤ እኛም እያንዳንዱን በራሱ ዓውድ



ማንበብ ይኖርብናል:: ይሁን እንጂ ከሌሎች በተለይ ደግሞ ታናናሽ ተደርገው በሚቆጠሩትና እየታገሉ ካሉት ጋር በሚኖረን ግንኙነት ትሕትና ሊኖረን እንደሚገባ ሦስቱም ታሪኮች አጽንዖት የሰጡበት ጉዳይ ነው:: ስለሆነም ክፍል 91 በሦስት ተጨባጭ መንገዶች የትሕትናን ነገረ መለኮታዊ ይዘት ያቀርባል::

**ማር 9÷38-41**
**ሉቃ 9÷49 ጋር**



[38]ዮሐንስም፦ «መምህር ሆይ፦ አንድ ሰው በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየን፤ ከእኛ ጋር ስለማይከተልህም ከለከልነው» አለው::

[39]ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ፤ «አትከልክሉት፤ ማንም በስሜ ታምር ሠርቶ ወዲያውኑ በእኔ ላይ ክፉ መናገር አይችልም፤ የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነውና፤ [41]እውነት እላችኋለሁ፦ የክርስቶስ በመሆናችሁ በስሜ አንድ ኩባያ ውሃ የሚሰጣችሁ ሁሉ ዋጋውን አያጣም»::

አጋንንት የሚያስወጡ ሰዎች በአይሁድ ዘንድ ያልተለመዱ አልነበሩም (ማቴ 12÷27፤ ሉቃ 11÷19፤ ሐሥ 19÷13-14):: አጋንንት ማስወጣት የሚረዳቸውን ኃይለኛ ድግምት ለመፈለግ ምንጊዜም ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጉ ነበር:: ብዙውን ጊዜ በአጋንንቱ ላይ ሥልጣን ይኖረዋል ብለው በማሰብ ኃይለኛ አስማተኛንና ተአምር ሠሪን ስም ይጠሩ ነበር:: አጋንንት ያስወጣ የነበረው አይሁዳዊ በኢየሱስ ስም መጠቀሙ የሚያስገርም አይደለም:: ይሁን እንጂ አስገራሚው ነገር የወሰደው እርምጃ ውጤት ማስገኘቱ ነበር (ሐሥ 19÷13-16 ጋር ያነ):: ምናልባትም ይህ የሚያሳየው እንደ አንድ ዐይነት ቀመር በኢየሱስ ስም መጠቀሙን ሳይሆን በእርግጥ በኢየሱስ ማመኑንና ደቀ መዝሙር በመሆን አዝማሚያ ላይ ሳይሆን እንደማይቀር ነው:: ስለዚህም ምንም እንኳ በግልጽ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ባይሆን እንኳ ሥራው ሊደናቀፍበት አይገባም::

የዚህ ምንባብ ዋነኛ ነጥብ የቤተ እምነት ጉዳይ ባይሆንም፣ ተግባራዊ ግንዛቤ ማድረግ ግን የማይቀር ነው። አንድ ሰው የእኔ ቤተ እምነት አባል አለመሆኑ ወይም እኔ የምቀበለውን አስተምህሮ አለማመኑ ብቻ ጠላቴ አያደርገውም። እንዲህ ሲባል ግን እንዲሁ ሁሉንም የእምነት ክፍሎች ያለ ግንዛቤ እንድንቀበል የቀረበ ጥሪም አይደለም። መቼም ቢሆን ለኢየሱስ መገዛት፣ ለኅብረት መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ኢየሱስን ለማወጅና የሰው ልጆችን ስቃይ ለማስወገድ በጋራ ዓላማ የመሰለፍ ኅብረት ነው። ብዙ ቤተ እምነቶች የማይተባበሩት፣ እዚህ ነጥብ ላይ ልክ ዮሐንስን በመምሰላቸው ነው። ትኩረታቸው ሁሉ ወደ ውስጥ እንጂ ወደ ውጭ አይደለም። ከምንም ነገር በፊት፣ «ከሁሉ የሚበልጠው ማነው?» ለሚለው ጥያቄ (ማር 9፥33-37) ትክክለኛውን ለማስረገጥ ጥረት ማድረግ ነው። «ከእነዚህ ሕፃናት አንዱን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበለኝ ሁሉ የሚቀበለው እኔን ሳይሆን የላከኝን ነው» (ማር 9፥37) በማለት ኢየሱስ ከተናገረው አንጻር እንደ ተሰጠ ስንገነዘብ የዮሐንስ ምላሽ ይበልጥ አሳዛኝ ይሆንብናል። የተለያዩ መታወቂያዎቻቸውን ከግምት ሳያስገቡ እውነተኛ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ ሁሉ በአንድነት ቢተባበሩ በዓለማችን ባለው ረሀብን የማስወገድ፣ ወንጌልን የማዳረስ፣ በፖለቲካ፣ የመገናኛ ብዙኀን፣ የሕክምና ወዘተ አገልግሎቶች ላይ ኃይለኛ በጎ ተፅዕኖ ማሳደር በቻሉ ነበር።

ዮሐንስ የዚያን ሰው ሥራ እንዳያሰናክል ኢየሱስ ነገረው። በመጀመሪያ፣ ታምራት ያደረገው በኢየሱስ ስም ከሆነ ወዲያውኑ ኢየሱስ ተቃዋሚ አይሆንም (ቁ 39)። ሁለተኛ፣ ኢየሱስን አይቃወምም። ስለሆነም አጋንንትን ማውጣቱ ኢየሱስን ይበልጥ እንዲታወቅ ያደርጋል (ቁ 40)። ሦስተኛ፣ አገልግሎቱ ለሰው ልጆች ስቃይ በኢየሱስ ስም መፍትሔ እየሰጠ ነው። ስለሆነም ከእግዚአብሔር ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል (ቁ 41፤ ማቴ 10፥42 ጋር ያነ)። ስለ፣



«ታናናሾቹ» እየተነገረ የነበረው ጉዳይ ከሕፃናት (ማቴ 18፥5፤ ማር 9፥37) ወደ ደቀ መዛሙርቱ (ማር 9፥41፤ ማቴ 18፥6) መለወጡን እንመለከታለን።

ቀደም ሲል ማቴዎስ 12፥30 ላይ ኢየሱስ፣ «ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል» ብሎ ነበር። ታዲያ ይህ በማርቆስ 9፥40 ከተገለጸው ጋር አይቃረንም? በፍጹም። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎች ናቸው። እዚህ ላይ የምንመለከተው ሰው ደቀ መዝሙር ወደ መሆን እያመራ ነበር። በትክክለኛው አቅጣጫ እየሄደ ነው። ስለሆነም የኢየሱስ ተቃዋሚ አይደለም። ስለዚህም፣ «ሥራውን አታሰናክሉ» አለ። በማቴዎስ 12፥30 ፈሪሳውያን ኢየሱስን እንዲከተሉ ጥሪ ቀርቦላቸው ነበር። እነርሱ ግን ገለልተኛ ለመሆንና ራሳቸውን ላለመስጠት በመፈለጋቸው ሊቀበሉት ፈቃደኛ አልነበሩም። ሆኖም ከኢየሱስ ጋር አንድ ጊዜ ፊት ለፊት ከተገናኛችሁ በኋላ ማቅማማት አይኖርም። ወይ በግልጽ ማመናችሁን ትናገራላችሁ አለዚያም በግልጽ ትቃወሙታላችሁ።

**§ 91ለ**
**ታናናሾችን ማሰናከል**
**(ማር 9፥42-50)**

[ማቴ 18] 6 ነገር ግን በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሰው፣ ከባድ የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል።

7 ይህች ዓለም የመሰናከል ምክንያት በመሆኗ ወዮላት! መሰናከል መምጣቱ አይቀርምና፤ ነገር ግን የመሰናከሉ ምክንያት ለሚሆን ሰው ወዮለት፤ 8 እጅህ ወይም እግርህ ለመሰናከል ምክንያት ቢሆንብህ፣ ቈርጠህ ጣለው ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል፣ አንካሳ ወይም ሽባ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል። እንዲሁም ዐይንህ ለመሰናከል ምክንያት ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ጣለው፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ [እሳቱ ወደማይጠፋ[ማር]] ወደ ገሃነም እሳት ከምትጣል፣ አንድ ዐይን ኖሮህ ወደ ሕይወት [ወደ እግዚአብሔር መንግሥት[ማር]] መግባት ይሻልሃል።

[ማር9]48በገሃነም ትሉ አይሞትም፤ እሳቱ አይጠፋምና
49ሰው ሁሉ በእሳት ይቀመማልና::
50ጨው መልካም ነው፤ ነገር ግን ጨው ጨውነቱን ቢያጣ እንዴት መልሳችሁ ጣዕም እንዲኖረው ታደርጉታላችሁ? ጨው በውስጣችሁ ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም ተስማሙ::

ማቴዎስ በቀጥታ በግዙፍ አካል ከሚታየው ሕፃን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ይሸጋራል:: እንዲህ በማድረጉ በእግዚአብሔር ፊት የከበሩ ስለ ሆኑትና በአንጻራዊ መልኩ ራሳቸውን መከላከል ስለማይችሉት ታናናሾች እንድናስብ ያደርገናል:: እንዲህ ያሉትን ግለ ሰቦች እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ይጠነቀቅላቸዋል:: ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ከባድ መከራ ይደርስበታል:: የኢየሱስ ቃል የፈጠረው የሃሳብ ሥዕል በጣም ጠንካራ ነው:: ይህ የወፍጮ ድንጋይ የተለመደው ዐይነት የእጅ ወፍጮ አይደለም:: በጣም በርካታ እህል መፍጨት እንዲችል በአህያ ጉልበት ከሚሽከረከሩት ትልልቅ ክብ ድንጋዮች አንዱ ነው:: በሌላ አነጋገር ከእነዚህ አንዱ አንገቱ ላይ የታሰረበት ሰው በፍጥነት ወደ ጥልቁ ባሕር ይሰጥማል::

ማርቆስ ይህን ታሪክ ዮሐንስ ይቃወመው ከነበረው ማንነቱ ካልታወቀው አጋንንት የሚያስወጣው ጋር ያያይዘዋል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ታናናሾቹን የማሰናከሉ ጉዳይ የሚነሣው ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መካከል መሆኑን እንረዳለን:: ቍጥር 7 መሰናክያ ከዓለም ሊመጣ እንደሚችል ያመለክታል:: በሌላ በኩል ሮሜ 5÷12 ኀጢአት ከራሱ ከግለሰቡ የሚመነጭ መሆኑን ያመለክታል:: ስለሆነም አንድ የተወሰነ ኀጢአትን በተመለከተ ተጠያቂ የሚሆኑ ሦስት ወገኖች አሉ ማለት ነው፤ (1) ዓለም፣ (2) የሚፈትነው፣ (3) የሚወድቀው ሰው:: በዚህ ዓለም ስንኖር ኀጢአትን ከማድረግ ፈተና ልንርቅ አንችልም:: ሌላውን ሰው እስካሰናከልን ድረስ በግል ተጠያቂዎች



ከመሆንም አናመልጥም:: «ሰይጣን አሳስቶኝ እንዲህ አደረግሁ» የሚል ሰበብ ማቅረብም አንችልም:: እያንዳንዳችን ስለ ኃጢአታችን ተጠያቂዎች ነን (ቍ 8-9፤ ማቴ 26÷24 ጋር ያነ)::

ሁለት ጉልህ ልዩነቶችን ከማሳየቱ በስተቀር በቍጥር 8-9 ያለው የተራራው ስብከትን (ማቴ 5÷29-30) ያስተጋባል:: በመጀመሪያ ማቴዎስ 5÷29-30 በሴሰኛነት መንፈስ ወደ አንዲት ሴት መመልከትን በተለየ ሁኔታ ያሳያል:: እዚህ ላይ ግን ማንኛውንም ዐይነት ኀጢአት ይመለከታል:: ሁለተኛ፣ እዚህ ላይ የቅጣቱ መግለጫ ይበልጥ ግልጽ ሆኖ ቀርቧል፣ «እሳቱ ወደማይጠፋ ገሃነም» (ማር 9÷43)፣ «በገሃነም ትሉ አይሞትምና፤ እሳቱ አይጠፋምና» (ማር 9÷48፤ ኢሳ 66÷24 ጋር ያነ):: የትንቢተ ኢሳይያስ ማጠቃለያ የሆነው ይህ ጥቅስ በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር የሚኖረውን ሐሴት ከአስፈሪው ዘላለማዊ ቅጣት በማነጻጸር ቅራኔውን ያመለክታል::

«ገሃነም» [*gehenna*] የሚለው ቃል ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ የነበረው ሸለቆ ስም ነው:: ሰዎችን መሥዋዕት ማድረግን ጨምሮ የጣዖት አምልኮ የሚካሄድበት ማዕከል ነበር (ኤር 7÷31፤ 19÷5-6፤ 32÷35):: በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን የነበረው ተሐድሶ ይህንን ስፍራ የሰው ልጆች አዳሪና የሞቱ እንስሳት አስከሬን ሳይቀር የሚጣልበትና የከተማው ቆሻሻ የሚቃጠልበት ቦታ ወደ መሆን ለወጠው (2ነገ 23÷10):: ከዚያ የሚወጣው ግማት በጣም አስከፊ ሊሆን እንደሚችል አይጠረጠርም:: እሳቱ ጠፍቶ አያውቅም፤ ምንጊዜም ትሎች በዚያ አይታጡም:: ከዚህ የተነሣ ያ ቦታ የእግዚአብሔርን ቅጣት በሥዕላዊ ሁኔታ የሚያመለክት ምሳሌ ሆነ::

ዋናው ነጥብ ቀላል ነው፤ ገሃነም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የቃጠሎ ቦታ ነው:: የተሟላ አካልን ጨምሮ በዚህ ዓለም ማንኛውም ነገር ማጣት ከዚያ ዓይነቱ መከራ ጋር ሊመጣጠን አይችልም:: ኢየሱስ

አካልን ስለ መቆራረጥ እየተናገረ አይደለም (የማቴ 5፥29-30 ማብራሪያ ይመልከቱ)፡፡ ይልቁንም ዐይኖቻችን፣ እጃችንና እግራችን መቁረጥ እስከሚያስፈልገን ድረስ ማሰብ እንዳለብን ማመልከቱ ነበር፡፡ በቀላል አነጋገር የምር ንስሐ እንድናደርግ የቀረበ ጥሪ ነው፡፡

ማርቆስ 9፥49 የኢየሱስ ከባድ ንግግር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ በርካታ ከዐሥራ ሁለት በላይ የተለያዩ ትርጓሜዎች እንዲቀርቡና አያሌ የቅጂ ልዩነቶችም እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለሆነም በትሕትናና ብዙም ጠልቀን ወደ ውስጥ ሳንገባ ይህን ሐሳብ እናቀርባለን፡፡ ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን አንድ ነገር በጨው ሲቀመም ላዩ ላይ ከመነስነስ ይልቅ ሙሉ በሙሉ በጨው እንዲሸፈን ይደረግ ነበር፡፡ ስለዚህ የቀረበው የሃሳብ ሥዕል ግልጽ የመከራ ምሳሌ በሆነው እሳት መሸፈንን ነው፡፡[84] እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ፣ «በእሳት የሚሸፈነው ማን ነው?» የሚል ነው፡፡ ማርቆስ 9፥48ን መለስ ብለን ስንመለከት ስለ ገሃነም ገለጻ ተደርጐ እንደነበረ እናስተውላለን፡፡ ስለዚህም ለታናናሾቹ መሰናከል ምክንያት የሚሆኑ መጥፎ ሰዎች ጨርሶ ይደመሰሳሉ ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ እንችላለን፡፡[85] በሌላ በኩል ማርቆስ 9፥50ን ስንመለከት ደግሞ በእሳት መቀመም ያለባቸው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሆናቸውን የሚያመለክት ይመስላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይህ የመከራ እሳት ከሚያነጻው እሳት ጋር የሚነጻጸር ነው (ማቴ 5፥10-12 ጋር ያነ)፡፡ እንዲያውም የእሳትና የጨው በአንድ ላይ መሆን

---

[84] አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከእሳት ጋር ይያያዛል፡፡ ስለሆነም አንዳንዶች፣ «በእሳት መቀመም» በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዐውዱ የሚያመለክተው መከራንና (ቍ 48) ሊታጣ የሚችል ተደማጭነትን ነው (ቍ 50)፡፡ ያ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚያም በላይ «ሁሉም» የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን አይቀበልም፡፡

[85] W.W. Fields, "Everyone Will Be Salted w th Fire," *GTJ* 6/2 (1985): 299-304 ላይ ማርቆስ 9፥49ን ወደ ዕብራይስጥ መልሶ በመተርጐም «በጨው መቀመም» የሚለው «ይጠፋል» ተብሎ ሊተረጐም እንደሚችል አመልክቷል፡፡



ሌዋውያን ለመንጻት ያቀርቡት የነበረውን መሥዋዕት ሊያመለክት ይችላል (ዘሌ 2፥13)፡፡ እንዲህ ያለው ሐሳብ የማርቆስን ወንጌል ለተቀበሉት ለሮም ክርስቲያኖች ታላቅ መጽናኛ ሊሆናቸው ይችላል፡፡ እንዲህ ከሆነ በቍ 48 እና 49 መካከል፣ ኢየሱስን በመከተላችሁ አሁን መከራ ትቀበላላችሁ፣ አለዚያም እሱን ካልተቀበላችሁ በኋላ መከራ ትቀበላላችሁ የሚል የተቃርኖ ንጽጽር ይኖራል፡፡

**ማቴ 18፥10**

[10]ከእነዚህ ከታናናሾች መካከል አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ እላችኋለሁና፤ በሰማይ ያሉት መላእክቶቻቸው በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ሁልጊዜ ያያሉ፡፡

ከዕብራውያን 1፥14 እና መዝሙር 91፥11 ጋር በአንድነት ሆኖ ይህ ጥቅስ አንዳንዶችን እያንዳንዱ ግለ ሰብ በእግዚአብሔር የተመደቡ የግል ጥበቃ የሚያደርጉለት «ጠባቂ መላእክት» አሉት ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡ አይሁድ እንዲህ ያለ ነገር ያምናሉ (*b. Sabb.* 119b)፡፡ ሆኖም ከዚህ ጥቅስ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ወይም የማያረጋግጥ ሐሳብ ማግኘት አይቻልም፡፡

ዌስል እነዚህ ጠባቂ መላእክት ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ በመሆናቸው ዘወትር ፊቱን ለማየት የታደሉ በሞት የተለዩ፣ የ«ታናናሾች» መንፈሶች ናቸው የሚል አሳማኝ ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ለነገሩማ እነዚህ መላእክት በአንድ ጊዜ በምድር የተመደበላቸውን ሰው መጠበቅና በእግዚአብሔር ፊት መሆን እንዴት ይቻላቸዋል?

**§ 91ሐ**
**የጠፋው በግ**
**(ማቴ 18፥12-14**
**ሉቃ 15፥3-7**
**ጋር ያነ)**

ይህ ምሳሌ ጭራሽ ልዩ በሆነ ዐውድ በሉቃስ 15፥3-7 በድጋሚ ቀርቧል፡፡ እዚህ ላይ የጠፋው በግ የሚወክለው፣ «የወደቀ» ደቀ መዝሙርን ነው፡፡ በሉቃስ ወንጌል የጠፋው በግ

የሚወክለው የጠፋውን ኃጢአተኛ ነው:: ከዚያም በግሪኩ ምንባብ አብዛኞቹ ዐበይት ቃላት የተለዩ ናቸው:: በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባሎች ምንጭ ላይ ጥናት ያደረጉ (Source Crities) እንደሚሉት ይህ ምሳሌ ማቴዎስና ሉቃስ ከሌላ ሦስተኛ ሰው የወሰዱት አይመስልም:: ይልቁንም፣ ኢየሱስ ተመሳሳይ ምሳሌን ሁለት የተለያዩ (የሚመሳሰሉ ቢሆኑም) ነጥቦችን ለማሳየት በሁለት የተለያየ ወቅት፣ በሁለት የተለያየ ዐውድ የተጠቀመ ይመስላል::

ማቴ 18÷12-14

12እስቲ ንገሩኝ፤ አንድ ሰው መቶ በጐች
ቢኖሩትና ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋበት ዘጠና ዘጠኙን
በተራራ ላይ ትቶ የጠፋውን ለመፈለግ አይሄድምን?
13እውነት እላችኋለሁ፤ የጠፋውን በግ ሲያገኝ፣ ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በዚያ
በተገኘው ደስ ይለዋል:: 14እንደዚሁም ከእነዚህ ከታናናሾቹ መካከል አንዱ እንኳ
እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም::

በምሳሌው የቀረበው ነጥብ ግልጽ ነው፤ እግዚአብሔር ሰዎችን፣ በተለይም የጠፉትንና ደካሞችን ይወዳል::[86] አንድ ኀጢአተኛ ሲድን እጅግ ደስ ይለዋል:: ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲመጡ እንጂ፣ ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም (2ጴጥ 3÷9)::

እረኛው ዘጠና ዘጠኙን ሜዳ ላይ እንደሚተው ምሳሌው ያመለክታል:: በእውኑ ዓለም እንደምንመለከተው ማንም እረኛ እንደዚያ አያደርግም:: የሚጠብቋቸው ሌሎች እረኞች ይኖራሉ:: እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር ዘጠና ዘጠኙን መጠበቅና የጠፋውን አንዱን በግ መፈለግ ይችላል:: ሆኖም፣ እዚህ ላይ ምሳሌው የሚለው ስለሌለ ይህን ጉዳይ (አላጐሪያዊ) አንድምታዊ ትርጉም መስጠት የለብንም::

86 መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ራሳቸውን የሚረዱትን እግዚብሔር ይረዳቸዋል» በማለት አያስተምርም:: ይልቁንም ይህ ምንባብ እግዚአብሔር እርዳታ ቢሶችን እንደሚረዳ የሚናገር ይመስላል::



ቁጥር 13 ላይ፣ «ሲያገኘው» የሚለው ቃል በረት ውስጥ ካሉት በጐች አንዱ መጥፋት የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ያሳያል:: የፓለስቲና እረኞች ብዙ ጊዜ የሚቅበዘበዙ በጐች ይጠፉባቸዋል:: ይህ ግን፣ እረኛው ችልተኛ ነው ማለት አይደለም:: ሌላው ቀርቶ ኢየሱስ እንኳ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ጠፍቶበታል (ዮሐ 17÷12፤ 18÷9):: ይህ በዮሐንስ 10÷27-28 ለተነገረው ሚዛናዊነትን የሚያስይዝ አስፈላጊ ጉዳይ ነው::

**§ 92ሀ**
**የሥነ ሥርዐት እርምጃና ይቅር ማለት (ማቴ 18÷15-22)**

ይህ አስቸጋሪ ምንባብ ነው፤ አስቸጋሪነቱ ግን ለመረዳት ከባድ በመሆኑ ሳይሆን የምንኖርበት ማኅበረ ሰብ ዓይን-ያወጣ ግለኝነትን የሚያበረታታ በመሆኑ ነው:: «ለራስህ አስብ፤ እኔ ራሴ እንደ ወደድኩት አደርጋለሁ» ለሚለው አባባል ከበሬታ እንሰጣለን:: «እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?» (ዘፍ 4÷9) የሚል ጥያቄ ቢቀርብልን ያለ ምንም ልዩነት የምንሰጠው መልስ፣ «አይደለሁም» የሚል ነው፣ ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚገባው ግን ለሌሎች መንፈሳዊ ደኅንነት ኀላፊነት አለብኝ» የሚል መሆን አለበት:: እርግጥ ነው፣ በመጀመሪያ ደረጃ በራሳችን ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ ማውጣት አለብን (ማቴ 7÷3-4) ይሁን እንጂ በወንድማችን ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ እንድናወጣ ኀላፊነትም ተሰጥቶናል (ማቴ 7÷5):: ፈራጅ ልንሆን በፍጹም የተገባን ባይሆንም፣ ሌሎች አማኞችን የመመዘን የመዳኘት ኀላፊነት ተሰጥቶናል (1ቆሮ 6÷4-5):: አዎን፣ በግብዝነት ወንድሞችን በኀሊና ወይም በአመለካከት ጉዳይ መዳኘት የለብንም (ሮሜ 2÷1):: ያም ሆኖ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመወሰንና ሥርዐት የማስያዝ ኀላፊነት አለብን::

ማቴ 18÷15-17

15ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ
ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው:: ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደገና
የራስህ ታደርገዋለህ:: 16ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት
ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው::
17እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛብና
እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው::

ፊት ለፊት ሰዎችን በምንወቅስበት ጊዜ የመጀመሪያው ችግር፣ ተወቃሹ ወገን የሚኖረው አመለካከት ነው:: ፊት ለፊት የሚወቀሰውም ሰው አመለካከት የዚያኑ ያህል አስቸጋሪ ነው:: በተለይም በሌሉበት ወቅት የሌሎችን ኀጢአት መጠቈም በአንጻራዊ መልኩ ቀላል ነው:: ዕርቅ ማድረግን ዓላማ በማድረግ (ሉቃ 17÷3-4፤ ያዕ 5÷19-20) በፍቅር፣ (ዘሌ 19÷17-18)፣ በትሕትና (ገላ 6÷1)፣ መንፈስ ማድረጉ ደግሞ የበለጠ ከባድ ነው::

በዚህ ሂደት ውስጥ ሦስት ርምጃዎች አሉ:: የመጀመሪያው፣ አንድ ላንድ መገናኘት ነው:: እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሲሆን ግለ ሰቡ ራሱን ነጻ ለማውጣት የሚያደርገውን ሙግት ከመቀነሱም በላይ፣ ሐሜት ከመጀመሩ በፊት ስፍራ እንዳይኖረው ይረዳል:: ብዙውን ጊዜ የመጀመሪያው ርምጃ ዕርቅን ግብ ባደረገ በፍቅርና በትሕትና መንገድ ከተወሰደ፣ የተቀረው ይህን ያህል አያስቸግርም:: አብዛኛውን ጊዜ ችግር የሚፈጠረው የመጀመሪያውን ርምጃ ከአግባብ ውጪ ከተወሰደ፣ ወይም ጨርሶ ርምጃው ሳይወሰድ የቀረ እንደሆነ ነው::[87]

[87] ጳውሎስ ጴጥሮስን ፊት ለፊት መገሠጹ (ገላ 2÷11-14) ሊስተዋል የሚገባው የተለየ ጉዳይ ሲሆን የጴጥሮስም በደል እንዲሁ የተለየ ነው:: በጳውሎስና በጴጥሮስ መካከል የሆነው የግል ጉዳይ አልነበረም:: ጴጥሮስ ታዋቂ ሰው ነበር:: ተግባሩ ብዙዎች ግብዝነቱን እንዲከተሉ አድርጓቸዋል:: እንዲህ ያለው ይፋ የወጣና ሌሎችን ማሳሳት የሚችልን በደል ጳውሎስ ፊት ለፊት መውቀሱ ተገቢ ነበር::



ሁለተኛው ርምጃ፣ የሁለት ወይም የሦስት ምስክሮችን መኖር ይጠይቃል (ዘዳ 19÷15 ጋር ያነ):: ይህ ግን፣ ፊት ለፊት መገናኘታችንን፣ በሕጋዊ ምስክሮች ፊት ማድረግ እንጂ «በበደለኛው» ወገን ላይ «አድማ» መምታት አይደለም:: እንዲህ ማድረጉ ቢያንስ ሁለት ዓላማዎችን ለማሟላት ያግዛል:: በመጀመሪያ፣ ጉዳዩ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመራ ከሆነ ሁለቱም ወገኖች የሚያቀርቡትን ታሪክ እውነተኛነት ለማረጋገጥ ይረዳል:: ሁለተኛ፣ ጉዳዩን «ሥርዓት» ለማስያዝና የሁለቱም ወገኖች ጉዳይ መሰማቱን ያረጋግጣል:: ከዚህም በበለጠ በአይሁድ ሸንጐ ደንብ መሠረት ከሁለቱ ምስክሮች አንዱ፣ «ለበደለኛው» የሚወግን ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ምስክሮች በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሥራ ላይ ያሉ (ለምሳሌ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናትና መጋቢዎች) መሆናቸውን የሚያመለክት ነገር የለም:: ሆኖም፣ በሳል፣ መንፈሳዊና ከአድልዎ የፀዱ መሆናቸው ከሚዛናዊነት አንፃር ተፈላጊ ነው::

ሦስተኛው ርምጃ፣ «የሥነ ሥርዓት ርምጃ» በመባል የሚታወቀውን የሚመለከት ነው:: ምንም እንኳ እዚህ ላይ ኢየሱስ የሰጠው ትእዛዝ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደምታደርገው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የተከተለ ጉዳይ ባይሆንም፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛውን ጊዜ የዘነጉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድንጋጌ ነው (2ተሰ 3÷14-15 ጋር ያነ):: በደል የፈጸመው ወንድም እርሱ ለመናገር በግል የተደረገለትንና ጥቂት ምስክሮች ባሉበት የተደረገውን ወቀሳ የማይቀበል ከሆነ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መወሰድ ይኖርበታል:: የማቴዎስን ወንጌል ያነቡ ለነበሩ አይሁድ አንድን ሰው እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ወይም እንደ ኀጢአተኛ መቍጠር ከአምልኮና ከማኅበራዊ ተሳትፎ ማገድ ማለት ነበር (ለምሳሌ ዘፍ 17÷14፤ ዘፀ 12÷15፣19):: በሌላ አነጋገር ከኅብረቱ ውጪ ይሆናሉ:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምናልባት ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑን የሚችሉ 1ቆሮንቶስ 5÷1-5 እና 2ቆሮ

2÷5-11 ብቻ ናቸው:: ማገድን (1ቆሮ 5)፣ እንዲሁም የዚያ ውጤት የሆነውን ዕርቅ (2ቆሮ 2) ሁለቱንም ይገልጻል::

ፊት ለፊት የመውቀስን ሂደት አስመልክቶ ሁለት ተጨማሪ ችግሮችም ይኖራሉ:: በመጀመሪያ፣ ተገቢ መመሪያና ጉዳዩን በሰነድ ዘግቦ የማስቀመጥ ሥርዓት የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኀላፊነታቸውን ተግባር ላይ ቢያውሉት በሕግ ሊጠየቁ ይችላሉ:: ይህን ሂደት በሥርዓት በተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቸልታ ልናየው አይገባም::[88] የኢየሱስን ትምህርት ችላ ማለትም የለብንም:: እንደ እባብ ልባሞች፣ እንደ ርግብ የዋሆች መሆን የሚገባን ከሆነ ልንሆን የሚያስፈልገን በእንዲህ ያለው ሁኔታ ነው (ማቴ 10÷16):: በመጨረሻም፣ በየአቅጣጫው አብያተ ክርስቲያናት በተከፈቱበትና ከፍ ያለ የአባላት ቊጥር የተሳካ አገልግሎት መለኪያ ሆኖ በሚቈጠርበት ሁኔታ አብያተ ክርስቲያናት በሥነ ሥርዓት ርምጃ አወሳሰድ ላይ እንዲተባበሩ ማድረግ አዳጋች ነው:: ባንዱ ቤተ እምነት ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት ደግሞ የበለጠ ከባድ ነው::

[18]እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ያሰራችሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል::

ማቴ 18÷18-20

[19]ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለ ምንም ነገር በመስማማት ብትጠይቁ በሰማይ ያለው አባቴ ያደርግላችኋል፤ [20]ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛለሁና::

[88] ጠቃሚ መመሪያ ለማግኘት የMarlin Jeschke, *Disciplineg in the Church* (Scottdale, PA: Herald Press, 1988) ወይም፣ John White and Ken Blue, *Healing the Wounded: The Costloy Love of Church Discipline* (Downers Grove, IL: InterVarsity, 1985) ይመልከቱ::



ቊጥር 18 ማቴዎስ 16÷19 ላይ ኢየሱስ ለጴጥሮስ የሰጠውን ተስፋ ቃል በቃል በድጋሚ ያቀርባል (ማብራሪያውን ይመ):: እዚህ ላይ ለሁሉም ሁኔታ ባይሆንም ይህ ተስፋ ለሁሉም ደቀ መዛሙርት የቀረበ ይመስላል:: ሁለት ነገሮችን በአእምሮአችን መያዝ አለብን፤ (1) እዚህ ላይ ዐውዱ በመካከላቸው አለመግባባት የተፈጠረ ሁለት ወንድማማቾችን ይመለከታል:: ስምምነት ያደረጉት ሁለቱ፣ በደል በፈጸመው ወንድም ላይ የሚመሰክሩበትና፣ በዚህም ሳቢያ መለኮታዊ ውሳኔን የሚያሳልፉ ሊሆኑ ይችላሉ:: አለዚያም ሁለቱ አለመግባባት ውስጥ የነበሩና አሁን ግን በሦስተኛ ወገን አደራዳሪነት ዕርቅ ያወረዱ ሁለቱ ወንድማማቾች ሊሆኑ ይችላሉ:: (2) ሁለቱ የሚያደርጉት ስምምነት በሰማይ እውቅና የሚኖረው የኢየሱስ መገኘት ውሳኔውን ስለሚያጸናው ነው:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በኩል የኢየሱስ በአካለ ሥጋ መገለጥ ይቀጥላል:: የእርሱ መገኘት አካሉ ለሚያሳልፈው ሕጋዊ ውሳኔ ሥልጣን ያለው ያደርገዋል::

ቊጥር 19 ላይ ያለው ጸሎት የእኛን እቅድ ወይም ፍላጐት የሚመለከት «ምንም ነገር» ሳይሆን ዳኝነትን የሚፈልግ ጉዳይ ነው:: ብዙውን ጊዜ ፕራግማ (*pragma*) የሚለው ቃል የሚያመለክተው ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ወይም ሕግ ነክ ውሳኔዎችን ነው (1ቆሮ 6÷1 ጋር ያነ):: ቊጥር 20 ላይ፣ «ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ቢሰበሰቡ» የሚለው ለአምልኮ ስለ መሰብሰብ የሚናገር አይደለም:: (የእግዚአብሔር በሁሉም ቦታ መገኘትና በውስጡ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አንድ ክርስቲያን ብቻውን ቢሆን እንኳ የክርስቶስ ሕልዎት ከእርሱ ጋር ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው):: «ቢሰበሰቡ» [*Synegmenoi*] የሚለው ቃል፣ «መሰብሰብ» ብቻ ሳይሆን «ኅብረት»ም ማለት ነው:: ስለሆነም ይህ ጥቅስ የሚሰጠው ተስፋ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረገው የፍርድ ውሳኔ አባሎቹ ሲስማሙ እግዚአብሔር የድጋፍ ማኅተሙን የሚያሳርፍ

መሆኑን ነው (መዝ 82፥1 ጋር ያነ)። በዚህ ሁኔታ «ሰላም አድራጊዎች መለኮታዊ ተግባር ይፈጽማሉ።»[89]

ማቴ 18፥21-22

[21]በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ «ጌታ ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን? አለው። [22]ኢየሱስም «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አይደለም» አለው።

በአይሁድ መምህራን ሕግ መሠረት ጴጥሮስ ከለጋስነት ያለፈ ነገር አድርጐ ነበር። በወቅቱ ይቅርታ ለማድረግ የሚጠበቀው ከፍተኛው መጠን ሦስት ጊዜ ብቻ ነበር (*b. Yoma* 86b, 87a)። ኢየሱስ ግን፣ «ለጋስ» የተባለው የእርሱን ሰባት በዐሥራ አንድ በማባዛት ጴጥሮስን አስደነጠው።[90] ሆን ብሎ፣ «ቃየንን የሚገድል ሰባ ጊዜ ቅጣት ካገኘው፤ የላሜሕ ገዳይማ ሰባ ሰባት ጊዜ ቅጣት ያገኝዋል» ከሚለው በዘፍጥረት 4፥24 ሳይ ካለው ጋር ያለውን ተቃርኖ ሊያሳይ የፈለገ ይመስላል። በሁለቱም ምንባቦች ዋናው ነጥብ ቍጥሩ ሳይሆን፣ የቍጥሩ ግነት ነው። በሌላ አነጋገር ኢየሱስ፣ «ሰባ ስምንት ጊዜ ከበደሏችሁ ይቅር አትበሉ» ማለቱ ሳይሆን፣ «ሁሌም ይቅር በሉ» ማለቱ ነበር።

**§ 92ለ**
**ይቅር ማለት ያልፈለገው አገልጋይ ምሳሌ**
**(ማቴ 18፥23-35)**

ኢየሱስ ለጴጥሮስ ሰባት ጊዜ ሳይሆን አስፈላጊ የሆነውን ያህል ጊዜ ይቅር እንዲልነገረው። አሁን ደግሞ፣ ጉዳዩን በምሳሌ ያብራራለታል። በመሠረቱ ይህ፣ ጌታ ለሐዋርያት ባስተማረው ጸሎት ከተገለጸው አቋም ጋር ተመሳሳይ ነው (ማቴ 6፥12-15 እና ሉቃ 17፥3-5)። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ይቅርታ ሌሎችን ይቅር በማለታችን ላይ የተመሠረተ ነው። እርሱ እኛን ይቅር ያለን በነጻ በመሆኑ፣ እኛም በነጻ ይቅር እንድንል እግዚአብሔር ይጠብቅብናል (ሉቃ 23፥34፤ 1ዮሐ 1፥9)። ጳውሎስ፣ «እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር ተባባሉ» በማለት ገልጾታል (ኤፌ 4፥32፤ ቈላ 3፥13)።

[23]ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ፣ በአገልጋዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ ለመተሳሰብ የፈለገን ንጉሥ ትመስላለች። ሂሳቡን ማጣራት እንደ ጀመረም ዐሥር ሺህ ታላንት ዕዳ ያለበትን አንድ አገልጋይ አቀረቡለት። [25]አገልጋዩም ያለበትን ዕዳ መክፈል ስላቃተው እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆቹና ንብረቱ ሁሉ ተሸጠው ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።

[26]በዚህ ጊዜ አገልጋዩ እግሩ ሳይ ወድቆ፣ «ታገሰኝ፣ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልሃለሁ» ሲል ለመነው። [27]ጌታውም አዘነለትና ማረው፤ ዕዳውንም ትቶለት አሰናበተው። [28]ያ አገልጋይ ከጌታው ፊት እንደ ወጣ አንድ መቶ ዲናር የእርሱ ዕዳ ያለበትን አገልጋይ ባልንጀራውን አግኝቶ አንቀ አድርጐ በመያዝ፣ 'ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ!' አለው። [29]ባልንጀራው አገልጋይም ከፊቱ ወድቆ፣ 'ታገሠኝ እከፍልሃለሁ' ብሎ ለመነው።

[30]ነገር ግን ሊታገሠው ፈቃደኛ ስላልነበረ፣ ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ ወህኒ ቤት አስገባው። [31]የሆነውን ነገር ያዩ ሌሎች አገልጋዮችም በጣም አዘኑ፤ ሄደውም ሁኔታውን በሙሉ ለጌታቸው ነገሩት።

[32]በዚህ ጊዜ ጌታው አገልጋዩን አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ 'አንተ ክፉ አገልጋይ፤ ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ፤ [33]እኔ እንደ ማርሁህ አንተም ባልጀራህን ልትምረው አይገባህም ነበርን?' [34]በቁጣም ያለበትን ዕዳ ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ ለአሳሪዎች አሳልፎ ሰጠው።

[35]ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ ያደርግባችኋል።

[89] Cf. J.D.M. Derrett, "'Where Two or Three Are Convened in My Name ...': A Sad Misunderestanding," *ExpT* 91 (1979-80): 83-86.

[90] «ሰባ ሰባት» ከማለት ይልቅ፣ «ሰባ ጊዜ ሰባት» ብሎ በማቅረቡ ምናልባት ትርጉሙ ትክክል ሳይሆን አይቀርም።

ይህ ይቅር ማለት ያልፈለገ አገልጋይ፣ ምናልባትም አንድ ባለሥልጣን የዐሥር ሺህ ታለንት ዕዳ ተከምሮበት ነበር:: ያ፣ በጣም ብዙ ነው! ለሮማውያን ዐሥር ሺህ በቋንቋቸው ያላቸው በጣም ከፍተኛው ቍጥር ነበር:: ታለንት ከፍተኛ ተመን ያለው ገንዘብ ነበር:: በዚህ ዘመን ምንዛሪ ዐሥር ሺህ ታለንት ከበርካታ ሚሊዮኖች እስከ ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚደርስ ሊሆን ይችላል (ይህን የሚወስነው እየተነጋገርን ያለው ከወርቅ፣ ከብር ወይም ከሌላ ርካሽ ነገር የተሠራ መሆን አለመሆኑ ነው):: ይህ ግን ከጉዳያችን ውጪ ነው:: ይህ ሰው ማንኛውም በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት ይኖር የነበረ ሰው ማሰብ ከሚችለው በላይ ዕዳ ነበረበት::

ንጉሡ ገንዘቡ እንዲመለስለት ፈልጓል:: ስለዚህም ሰውዬውንና ቤተ ሰቡን ለባርነት እንደሚሸጥ ዝቷል:: ያም የተለመደ የአይሁዶች ሕጋዊ አሠራር ነበር (ዘሌ 25÷39፤ 2ነገ 4÷1):: ሆኖም የአንድ ባርያ ዋጋ ግፋ ቢል የአምስት መቶ ቀን ደመወዝ ብቻ ነበር የሚያወጣው (Carson, p. 407):: ስለዚህም ንብረቱንና ቤተ ሰቡን ለባርነት መሸጥ ዕዳውን ምንም ያህል አይቀርፍለትም:: ዋናው ነጥብ ቅጣት መቅጣት እንጂ ዕዳው መከፈሉ አይደለም:: አገልጋዩ ዕዳውን እንደሚከፍል መናገሩ፣ እንዲሁ ጊዜ ለማራዘም ያህል ነበር:: ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ገንዘቡን ለመክፈል ምንም አቅም አልነበረውም:: ንጉሡም ይህንን ስለሚያውቅ ይቅስስለስ ለነበረው ባለ ዕዳ አዘነለት:: ዕዳው ተደመሰሰለት::

አገልጋዩ ወጥቶ ብዙም ሳይቆይ ያበደረውን ጥቂት ገንዘብ ለመሰብሰብ እርምጃ ወሰደ:: ምናልባት ዕዳውን ለመክፈል በጐ ፈቃድ ያለው መሆኑን ለንጉሡ ለማሳየት ጥቂት የዕዳ ክፍያ ማድረግ ፈልጐ ይሆናል:: አንድ መቶ ዲናር ዕዳ የነበረበትን አገልጋይ ጓደኛውን ጉሮሮውን አንቆ ያዘው:: ዲናር የአንድ የቀን ሠራተኛ ደመወዝ ነበር:: ይህ ደግሞ የሚወክለው ከአምስት ወር ያነሰ ደመወዝን ነበር:: እርግጥ



ነው፣ ገንዘቡ ብዙ ነው፤ ሆኖም ባለ ሥልጣኑ ከነበረበት ዕዳ ጋር ሲነጻጸር ግን እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም:: አንድ ታላንት ከስድሳ እስከ ዐሥር ሺህ ዲናር ሊመነዘር እንደሚችል ይገመት ነበር (Blomberg, p. 284):: ስለሆነም በሁለቱ ዕዳዎች መካከል የነበረው ልዩነት በአንድ ሚሊዮንና በአንድ ያለው ልዩነት ያህል ነበር::

ሌሎቹ አገልጋዮች በግብዝነቱ በመደንገጣቸው የሆነውን ለንጉሡ ነገሩት:: ንጉሡ በጣም ተቈጣ:: ባለ ሥልጣኑ አገልጋይ ጓደኛው ላይ እንደሚያደርግ የዛተበትን ንጉሡ በባለ ሥልጣኑ ላይ አደረገ:: ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ እንዲታሰርና እንዲያሰቃዩት ወህኒ ቤት እንዲጣል አደረገ:: ሐቁ ግን፣ ከወህኒ ቤት የሚያተርፈው ገንዘብ አለመኖሩ ነው:: ስለሆነም የዕድሜ ልክ ፍርድ ነበር ማለት ነው::

በቍጥር 35 ላይ ኢየሱስ ያቀረበው ማጠቃለያ ሃሳብ ቀላል ሆኖም አስገራሚ ነበር:: ሌሎች አገልጋዮች እኛ ላይ ያደረሱትን ቀላል በደል ይቅር የማንል ከሆነ፣ እግዚአብሔር ደግሞ እኛ በእርሱ ላይ የፈጸምነውን በጣም የበዛ በደላችንን ይቅር አይለንም:: የእግዚአብሔር ርምጃ ከባድና ተገቢም ነው:: በወንድሞቻቸው ወይም በትዳር ጓደኞቻቸው ወይም ወላጆቻቸው ላይ ቂም የቋጠሩ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎች ይህን ትምህርት ልብ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ሌሎችን ይቅር ማለት ለራሳችን ድነት አስፈላጊ ነው (ማቴ 6÷14-15፤ 18÷21-35፤ ማር 11÷25፤ ሉቃ 6÷37)::

**§ 93**
**(ከ§ 101 በኋላ ይመልከቱ)**

በልግስና በሚምርና፣ በጭካኔ በሚቀጣ ሰማያዊ አባት ተግባር ኢየሱስ ምንም የሚጣረስ ነገር አላየም፤ እኛም እንዲሁ ማየት አለብን:: ምሕረትና ርኅራኄ የሌላቸውን የራሱ አድርጐ የማይቀበልበት ትክክለኛው ምክንያት እርሱ ራሱ የምሕረትና የርኅራኄ አምሳል በመሆኑ ነው (Carson, p. 407)::

§ 94
የኢየሱስ ወንድሞች
የዳስ በዓል
ወደሚከበትበር ቦታ
እንዲሄድ ጠየቁት
(ዮሐ 7÷2-9)

በዚህ ጊዜ ጥቅምት ወር 32 ዓ.ም. ነበር፡፡[91] ባለፉት ስድስት ወራት ኢየሱስ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ የሰጠውን አገልግሎት ዮሐንስ፣ «ከዚህ በኋላ ኢየሱስ፣ በዚያ የነበሩት አይሁድ ሊገድሉት ስለ ፈለጉ፣ በይሁዳ አውራጃ መዘዋወር ትቶ፣ በገሊላ ተዘዋወረ» በሚል አንድ ቍጥር (7÷1) ብቻ ነው ያቀረበው፡፡ ወደ ጢሮስና ሲዶና አካባቢ፣ ወደ ዐሥሩ ከተሞች፣ ወደ ፊልጶስ ቂሣርያና ገሊላ ያደርገውን ጕዞ ያካተተና ዐሥራ ሁለቱን ለማሰልጠን ሰፋ ያለ ወቅት ያገኘበት ጊዜ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፣ ቀጣዮቹ ስድስት ወሮች ኢየሱስ በዓላማ ወደ መስቀሉ የሚያቀናባቸው ወቅቶች ይሆናሉ፡፡ ከአንዳንድ ምክንያቶች የተነሣ የዚህ ወቅት ቅደም ተከተላዊ ይዘት ምናልባት በወንጌሎች ውስጥ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡፡ (1) ማቴዎስና ማርቆስ ስለዚህ ወቅት የሚነግሩን በጣም በጥቂቱ ነው፡፡ (2) በሉቃስ ላይ የቀረበው ሰፋ ያለ ትረካ (9÷51-19፣44) እዚህ ላይ የተለመደው ቅደም ተከተል የመጠቀም ልማዱን አልተከተለም፡፡ (3) ዮሐንስ ስለ ሦስት በዓሎች ቢናገርም፣ ሁለቱ ግን በሦስቱ ተወራራሽ ወንጌሎች በፍጹም አልተጠቀሱም፡፡

ዮሐ 7÷2-5

[2]የአይሁድ የዳስ በዓል በተቃረበ ጊዜ ግን፣
[3]የኢየሱስ ወንድሞች እንዲህ አሉት፤ «ደቀ
መዛሙርትህም ደግሞ የምታደርገውን ታምራት እንዲያዩ፣
ከዚህ ወደ ይሁዳ ሂድ፤ [4]ራሱን ሊገለጥ እየፈለገ በስውር

[91] የዳስ በዓል በሰባተኛው ወር ዐሥራ አምስተኛ ቀን ይውላል (ዘሌ 23÷34) ይህም በጥቅምት ሁለተኛ ሳምንት መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ስቅለቱ የዋለው በ30 ዓ.ም. እንደ ሆነ ጠንካራ መከራከሪያ ቀርቧል፤ እንዲህ ከሆነ ይህ ሁኔታ የዋለው ጥቅምት 29 ዓ.ም. ነበር ማለት ነው፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ፣ ስቅለቱ ስድስት ወር በፊት ነበር፡፡



የሚሠራ ማንም የለምና፡፡ አንተም እነዚህን ነገሮች የምታደርግ ከሆነ፣ ራስህን ለዓለም
ግለጥ፡፡ [5]የገዛ ወንድሞቹ እንኳ አላመኑበትም ነበር፡፡

እንደ ፋሲካና እንደ በዓለ ሃምሳ ሁሉ የዳስ በዓልም ማንኛውም አይሁዊ ወንድ እንዲገኝ የሚጠበቅበት በዓል ነበር (ዘዳ 16÷16)፡፡ የዳስ በዓል ለስምንት ቀን የሚቈይ አስደሳች በዓል ሲሆን፣ (ዘዳ 16÷13-17) በዚሁ በዓል ሁለት ነገሮች ይከበራሉ፤ የመከር መሰብሰብና ከግብፅ ባርነት ነፃ መውጣት፡፡ ለመሥዋዕት ከሚቀርቡት ሰባ በሬዎችና በየዕለቱ ይነፋ ከነበረው መለከት በተጨማሪ በምድረ በዳ መንከራተታቸውን ለአይሁድ የሚያሳስቡ የተለያዩ ትእምርቶችን ይካተቱ ነበር፡፡ ለምድረ በዳ መንከራተታቸው መታሰቢያ እንዲሆኑ በመላ ከተማው በተተከሉት ዳሶች ቤተ ሰቦች ይመገባሉ፤ መኝታቸውንም እዚያ ውስጥ ያደርጋሉ (ዘሌ 23÷43)፡፡ ቅዱሱ ባለ ሰባት ቅርንጫፍ መቅረዝና መደዳውን የሚነዱት ችቦዎች በሌሊት ይመራቸው የነበረውን የእሳት ዐምድ ያስታውሳቸዋል (ዘኍ 14÷14፤ ዮሐ 8÷12)፡፡ ከሰሊሆም ምንጭ የሚወጣው ውሃ በመሪባ እግዚአብሔር ከዐለት ውሃ እንደ ሰጣቸው ያሳስባቸዋል (ዘፀ 17÷1-7፤ ዮሐ 7÷37 ጋር ያነ)፡፡ ኢየሱስ በዚህ በዓል መገኘት ብቻ ሳይሆን እነዚህን ትእምርቶች የስብከቱ መነሻ ያደርጋቸዋል (ዮሐ 7÷37፤ 8÷12)፡፡

ወደ ኢየሩሳሌም ጕዞ የሚጀምሩበት ጊዜ ነበር፡፡ የኢየሱስ ወንድሞች ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ይሁዳና ስምዖን (ማቴ 13÷55) አፋጠውት ነበር፡፡ መሲሕ መሆኑን ለማረጋገጥ ኢየሱስ ወደ በዓሉ መሄድ እንደሚገባው ሃሳብ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም፣ እነርሱ በእርሱ አላመኑም ነበር፡፡ ጠብ እንዲገጥማቸው እየጋበዙት ነበር፡፡ ባለፉት ስድስት ወሮች ኢየሱስ በአይሁድ ድንበሮች ዳር ዳሩን እየሄደ በመደበቅ ላይ ነበር፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ ባለፈው ፋሲካ በዓሉ ላይ አልተገኘም ነበር፡፡ ስለዚህ ባለፉት ዐሥራ ስምንት ወሮች ወደ ኢየሩሳሌም አልሄደም ማለት ነው፡፡

ማንኛውም፣ «ጥሩ» አይሁዳዊ በተቀደሰው ከተማ ተገኝቶ ሃይማኖታዊ ተግባሩን የማሟላት ኀላፊነት ይሰማዋል:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ እዚያ በነበረበት ባለፈው ጊዜ የአለቆች ሸንጐ አባላት ሊገድሉት ወስነው ነበር (ዮሐ 5÷18):: ለኢየሱስ አደገኛ ቦታ ነበር:: አሁን ደግሞ ወንደሞቹ፣ በመሠረቱ «ራስህን ግለጥ ወይም ዝም በል! በኢየሩሳሌም ልታደርገው ካልቻልህ፣ እንግዲያው ሐሰተኛ ነህ::» እያሉት ነው::

> 6 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «ለእኔ ትክክለኛው
> ጊዜ ገና አልደረሰም፤ ለእናንተ ግን ማንኛውም ጊዜ ምቹ
> ነው:: 7 ዓለም እናንተን ሊጠላ አይችልም፤ እኔ ግን፣
> አድራጐቱ ክፉ መሆኑን ስለምመሰክርበት ይጠላኛል::
> 8 እናንተ ወደ በዓሉ ሂዱ፤ ለእኔ ትክክለኛው ጊዜ
> ስላልደረሰ ወደ በዓሉ አልሄድም:: ይህን ብሎአቸው
> በገሊላ ቈየ::
>
> ዮሐ 7÷6-9

ኢየሱስና ወንድሞቹ በማኅበራዊና ባሕላዊ አመለካከታቸው በእጅጉ ይስማማሉ:: በመንፈሳዊ አስተሳሰባቸው ግን በጣም የተራራቁ ነበሩ:: እዚህ ላይ ኢየሱስ ሁለት ልዩነቶችን በጉልህ አቅርቧል:: በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ መለኮታዊውን የጊዜ ሰሌዳ ይጠብቃል:: ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ይሞታል፤ ሆኖም ጊዜው ገና አልደረሰም:: ሌላው ቀርቶ ወደ በዓሉ ቦታ ሄዶ ከሕዝቡና ከመሪዎቻቸው ጋር ፊት ለፊት ይገናኛል፤ ሆኖም ጊዜው ገና ነበር:: የኢየሱስ ወንድሞች ግን ይህን መሳዩን መለኮታዊ የጊዜ ቅደም ተከተል የሚከተሉ አልነበሩም:: እንደ ፈለጉት ይገባሉ፤ ይወጣሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሱስ እንደዚያ ማድረግ አይችልም:: መላው ሕይወቱ በእግዚአብሔር ምሪት መሠረት የተቃኘና የማይዛነፍ የጊዜ ሰሌዳን የተከተለ ነበር (ዮሐ 2÷4 ጋር ያነ)::

ሁለተኛው ዓቢይ ልዩነት ኢየሱስ ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት ነው:: ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ይሁዳና ስምዖን ጠላቶች አልነበራቸውም ማለቱ



ሳይሆን፣ የዚህ ዓለም ሥርዓት፣ በተለይም ከአይሁድ ባሕል ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል መሆናቸውን ማመልከቱ ነበር:: የግለሰቦችን ስሜት ይነካኩ ይሆናል፤ በማኅበራዊ ዕይታ ላይ ግን ተፅዕኖ ማምጣት አይችሉም:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢየሱስ የዚህ ዓለም አመለካከት፣ ነገር መለኮትና ባሕል ተቃራኒ ነበር (ዮሐ 2÷14-16፤ 3÷19-20፤ 5÷30-47 ጋር ያነ):: ከዓለም ወገን ስላልነበር፣ ኢየሱስ የዚህን ዓለም ሥልጣን ለያዙት ከባድ ስጋት ነበር:: ስለሆነም ዓለም ኢየሱስን ይጠላል (ዮሐ 5÷18፣19፤ 17÷14)::

**§ 95**
**በሰማርያ በኩል ማለፉ**
**(ሉቃ 9÷51-56፤ ዮሐ 7÷10)[92]**

ይህ ምንባብ ሉቃስ በጥንቃቄ ያቀረበውን ማዕከላዊ ክፍል ይከፍታል (ሉቃ 9÷51-19÷44)[93] በዚህ የመጽሐፉ ክፍል አንዳንድ ነገሮችን ሲያደርግ እንመለከታለን:: በመጀመሪያ ማቴዎስ በጽሑፍ ያሰፈራቸውን ኢየሱስ በገሊላ አገልግሎቱ ወቅት የተናገራቸውንና ያደረጋቸውን ነገሮች ይወስድና በይሁዳና በፔሪያ ጉዞ ኢየሱስ ካደረጋቸው ነገሮች ጋር ያካትታቸዋል:: ይህንንም በማድረጉ ሉቃስ ኢየሱስ በገሊላ ያደረገውና የተናገረውን ሁሉ በፖለስቲና ደቡባዊ ክፍል በድጋሚ ማድረጉን ያሳያል:: በሁለተኛ ደረጃ፣ የሉቃስ ማዕከላዊ ክፍል የኢየሱስንና የተቃዋሚዎቹን ንጽረተ ዓለማዊ ግጭት በጉልህ ያቀርባል::[94] ይህም መስቀሉን በተመለከተ ለሚከሰተው ታላቁ ግጭት ያዘጋጀናል::

---

[92] See notes on J.M. Dawsey, "Jesus' Pilgrimage to Jerusalem," *PRS* 14 (1987): 217-232 (esp. nn. 1 and 2, p. 217)

[93] H.K. Farrell, "The Structure and Theology of Luke's Central Section," *TrinJ* 7 ns (1986): 33-54.

[94] J.L. Resseguie, "Point of View in the Central Section of Luke (9:51-19:44)" *JETS* 25/1 (1982): 41-47.

ዮሐ 7÷10

10ደሁን እንጂ፣ ወንድሞቹ ወደ በዓሉ ከሄዱ
በኋላ፣ እርሱም በግልጥ ሳይሆን በስውር ወደ በዓሉ
ሄደ::

ሉቃ 9÷51

51ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሚያርግበት ጊዜ
በመቃረቡ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቁርጦ ተነሣ::

የበዓሉ አጋማሽ ላይ መድረስ እንዲችል ኢየሱስ ዘግይቶ ወጣ (ዮሐ 7÷14):: ከገሊላ ወደ ይሁዳ ለመሄድ ሰማርያን መሐል ለመሐል ቆርጦ ነበር የሄደው:: በአይሁድና በሳምራውያን መካከል የነበረው አለመግባባት በጣም የተካረረና በሚገባ ተዘግቦ የተያዘ ነበር (የ§ 35ሀ ማብራሪያ ይመ):: ለማንኛውም፣ ጊዜውን በሚገባ ለመጠቀምና ማንም ሳያውቀው ለመጓዝ እንዲችል ኢየሱስ ይህን መንገድ መርጧል::

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ለበቀል ነበር («ቁርጦ ተነሣ» (ቍ 51) የሚለው የግሪኩ ፈሊጣዊ አነጋገር የሚያመለክተው ቆራጥ ውሳኔ ማድረጉን ነው):: ከዚያም በላይ ሉቃስ የሚናገረው ስለዚህ ጉዞ ብቻ አልነበረም:: ሉቃስ 9÷51 ኢየሱስ ወደ መስቀሉ ለመሄድ ውሳኔ ማድረጉን የሚያመለክተውን አዲስ ክፍል (ሉቃ 9÷51፤ 10÷35፤ 13÷22፣32፣33፤ 17÷11፤ 18÷31፣35፤ 19÷1፣28-29) ይከፍታል (ሉቃ 9÷51-19÷44):: ዮሐንስን ያሰፈረውን ሦስት የኢየሩሳሌም ጉዞ አንድ እንቅስቃሴ አድርጐ እጥር ባለ አቀራረብ ያካትታል (ዮሐ 7÷10፤ 10÷22፤ 12÷12):: ባለፈው ክፍል ዮሐንስ እንዳደረገው ሁሉ፣ ሉቃስም በዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔርን ዕቅዳዊ አሠራር ይገነዘባል:: «በመቃረቡ» (Sympleroo, ቍ 51) የሚለው አገላለጹ የግብ ግንዛቤ ማለትም፣ መለኮታዊ ቀጠሮ እንዳለው መረዳቱን ያመለክታል (ሉቃ 1÷1፤ 4÷21፤ 9÷31፤ 22÷16፤ 24÷44 ጋር ያነ):: ወደ መስቀሉ



ለመድረስ ገና ስድስት ወር የቀረው ቢሆንም፣ የኢየሱስ አገልግሎት ጊዜ ወደ መደምደሚያው እየተቃረበ ነበር::

«ወደ ሰማይ» (ቍ 51) የሚለው ሐረግ በግሪኩ አዲስ ኪዳን ውስጥ አይገኝም፤ ሆኖም አ.መ.ት፣ ሐረጉን «የሚያርግበት ጊዜ» በሚለው ላይ መጨመሩ ትክክል ነው:: ይህንኑ «ዐረገ» ከሚለው ቃል ጋር የሚዛመደውን *analempseos* የተሰኘውን ቃል በሐዋርያት ሥራ 1÷2 እና 11 የምናገኘው ሲሆን፣ በቀጥታ የሚያመለክተው ዕርገትን ነው:: ምንም እንኳ *analempseos* በቀጥታ ስቅለትን ባያመለክትም ሞቱን፣ መቀበሩንና የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ማክተሚያ የሆነውን እርገቱን የሚጨምረውን ትንሣኤውን የሚያካትት ይመስላል::

ሉቃ 9÷52-56

52አስቀድሞም መልእክተኞችን ወደዚያ ላከ::
እነርሱም ሁኔታዎችን አስቀድመው ሊያመቻቹለት ወደ
አንድ የሳምራውያን መንደር ገቡ:: 53ሕዝቡ ግን ወደ
ኢየሩሳሌም እያመራ መሆኑን ስላወቁ አልተቀበሉትም:: 54ደቀ መዛሙርቱም ያዕቆብና
ዮሐንስ ይህን ሲያዩ፣ «ጌታ ሆይ፣ ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ እሳት ከሰማይ ወርዶ
እንዲያጠፋቸው እንድናዝ ትፈቅዳለህን?» አሉት 55ኢየሱስ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና፣
«እናንተ ከምን ዐይነት መንፈስ እንሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የመጣው የሰውን
ሕይወት ለማዳን ነው እንጂ ለማጥፋት አይደለምና አላቸው፤ ወደ ሌላ መንደርም
ሄዱ::

ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰማርያ ሲያልፍ፣ እንደ መሲሕ፣ እንዲያውም እንደ፣ «የዓለም አዳኝ» ተቀብለውት ነበር (ዮሐ 4÷39-42):: ታዲያ፣ አሁን ከ21 ወሮች በኋላ ችላ ያሉት ለምንድነው? ምናልባትም፣ ችላ ያሉት ወደረኛ የአምልኮ መቅደስ (ዮሐ 4÷20-24) ወደ ነበረበት ወደ ኢየሩሳሌም እያመራ የነበረውን የአይሁድ ቡድን እንጂ ኢየሱስ ራሱን ላይሆን ይችላል::

«የነጐድጓድ ልጆች» (ማር 3÷17) (*Boanerges*) በመባል የሚታወቁት ያዕቆብና ዮሐንስ ቅጽል ስማቸውን በተግባር ለመግለጽ ሁኔታውን ለማስተካከል በትሕትና ለኢየሱስ ሐሳብ አቀረቡ:: ችኩልነታቸውና ትዕቢታቸው በጣም አስደንጋጭ ነበር:: በመጀመሪያ፣ እንደዚያ ያለውን ኀይል ከየት እንቀበላለን ብለው አስበው ነው? እርግጥ ነው ብዙ ተአምራት አድርገዋል፤ አጋንንት አስወጥተዋል፤ ምናልባት፣ የሞቱ ሰዎች እንኳ አስነሥተው ይሆናል (ማቴ 10÷1፣8):: የተፈጥሮን ኀይል ማዘዝ ግን ሌላ ነገር ነው:: KJV የተሰኘው የእንግሊዘኛ ትርጉም እንዳስቀመጠው ራሳቸውን ከኤልያስ ጋር አወዳድረው ነበር (2ነገ 1÷9-12 ጋር ያነ):: ምናልባትም የመጥምቁ ዮሐንስ ምትክ እንደሆኑና፣ ለኢየሱስ፣ «መንገድ መጥረግ» እንዳለባቸው አስበው ይሆናል:: ይህ ግን በምኞት እንደ መወጠር ነው:: ሦስተኛ፣ ከኢየሱስ ጋር አብረው መቆም ያለባቸው ለምን እንደሆነ ያስቡ ይሆን? ተቃዋሚ በሆነ ማኅበረ ሰብ ውስጥ ለእግዚአብሔር መከራከር እንዳለባቸው እንደሚያስቡ ሰባኪዎች ሁሉ ነገሮችን በራሳቸው መንገድ ለመቈጣጠር በመፈለግ ያዕቆብና ዮሐንስ ከገደብ አልፈዋል:: ከዚህ ሁሉ የሚብሰው ስለ ትሕትናና ይቅር ባይነት ባለፈው ጊዜ ኢየሱስ ያስተማራቸው ሁለት ትምህርቶች ዘንግተዋል (§ 90-92)::

ጌታ እንደገና ለትሕትናና ለሰላማዊ ሕይወት የሚሆነንን አርአያነቱን አቀረበ:: ተቃዋሚዎቹ ሳምራውያንን ከመገሠጽ ይልቅ፣ የተሻለ ማወቅ የነበረባቸውን ደቀ መዛሙርቱን ገሠጸ:: እንዲያውም አንድ አስደናቂ አማራጭ ትርጉም ቍ 55ን፣ «ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም» በማለት አስቀምጦታል:: ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ጓዙን አንሥቶ በርጋታ ጕዞውን ቀጠለ::



# ምድብ ስምንት
# የክርስቶስ የመጨረሻው የይሁዳ አገልግሎት

**§ 96ሀ**
**ኢየሱስ የዳስ በዓል ወደሚከበርበት ቦታ መድረሱ**
**(ዮሐ 7÷11-31)**

ዮሐንስ 7 ከዐሥራ ስምንት ወሮች በፊት ዮሐንስ 5 ወደቆመበት ሁኔታ ይወስደናል:: ሁለቱም የተፈጸሙት በኢየሩሳሌም በነበረው በዓል ነበር:: በሁለቱም ምዕራፎች የአይሁድ መማክርተ ኢየሱስን ለመግደል ወስነዋል (5÷18፤ 7÷1፣19-20፣25፣30፣32፣44-45 በተጨማሪም ከ8÷59፤ 9÷22፤ 10÷31፣39፤ 11÷8፣53 ጋር ያነ):: በሁለቱም ምዕራፎች ኢየሱስ ስለ ራሱና መሪዎቹን በመቃወም መስክሯል:: በሁለቱም ምዕራፎች ሰንበትንና (5÷1-17፤ 7÷21-24)፣ የኢየሱስን ሥልጣን አስመልክቶ ጭቅጭቅ ተፈጥሮአል (5÷30-49፤ 7÷18-19):: ይህ ሁሉ የአንድ መዝሙርን አዝማች የማለት ያህል ነበር::

**ዮሐ 7÷11-13**

[11]በበዓሉም ላይ አይሁድ፣ «ያ ሰው የት አለ?»
እያሉ ይፈልጉት ነበር::
[12]ስለ እርሱ በሕዝቡ መካከል ብዙ ጉምጉምታ ነበር:: አንዳንዶች፣ «ደግ ሰው
ነው» አሉ:: ሌሎች ግን፣ «የለም፤ ሕዝቡን የሚያስት ነው» አሉ:: [13]ይሁን እንጂ
አይሁድን ከመፍራት የተነሣ ስለ እርሱ በግልጽ የተናገረ ማንም አልነበረም::

በዳስ በዓል ምክንያት ብዙ የሮማውያን ግዛት ሰዎች መጥተዋል:: እነዚህ ከተለያዩ አገሮች የመጡ የእምነት ተጓዦች (ቍ 20፣31-32)፣ የአይሁድ መማክርት (ቍ 15፣32፣35) እና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች (ቍ 25) በዚህ በዓል የተገኙ ሦስት የተለያዩ ቡድኖች ነበሩ:: በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ኢየሱስን በተመለከተ የተለያየ አመለካከት

ነበር፤ በአመዛኙ በጣም የሚጠሉት ግን የሃይማኖት መሪዎቹ ነበሩ:: ከሌሎች አገሮች የመጡት ሲወዱት፣ የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ግን ተጠራጣሪዎች ነበሩ (ምንም እንኳ ስለ የሕይወት እንጀራ የሰበከው፣ ብዙ የኢየሱስ ደጋፊዎችን አስቆጥቷል)::

ዮሐንስ፣ «አይሁድ» የሚላቸው የሃይማኖት ባለ ሥልጣናት ኢየሱስን እየፈለጉ ነበር:: ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት መገደል እንዳለበት ወስነው ነበር (ዮሐ 5÷18፤ 7÷1):: በነበረው ታዋቂነት ምክንያት ግን ሊነኩት አልደፈሩም:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማነኛውንም እንቅስቃሴውን የሚከታተሉ ሰላዮችን ከኢየሩሳሌም ይልኩ ነበር (ማር 7÷1፤ 8÷15፤ 9÷14፤ ማቴ 16÷1፣6፤ 17÷24):: ከስድስት ወራት በፊት መልካም ወሬ አምጥተውላቸው ነበር:: ስለ የሕይወት እንጀራ ከሰበከ በኋላ (16÷41፣52) በቅፍርናሆም ብዙዎች ከኢየሱስ ተለይተው ነበር:: ከዚያን ጊዜ ወዲህ የኢየሱስ ተቀባይነት ዝቅ እያለ ነበር:: አሁን ግን የበለጠ ዕድል አግኝተዋል:: ለማሤርና ለመዶለት ሰፊ ጊዜ ነበራቸው:: እርሱን በተመለከተም ሕዝቡ ተከፋፍለው ነበር:: ኢየሱስ በራሳቸው ክልል ውስጥ ነበር:: ይህ በዓል የሚፈልጉትን ሰው የሚያገኙበት ነበር:: ችግሩ፣ ኢየሱስ ገና አለመምጣቱ ነበር::

እንደ አይሁድ መሪዎች ሁሉ ሕዝቡም ኢየሱስን ለማየት ጓጉተዋል:: አንዳንዶች ደጋፊዎቹ፣ ሌሎች ደግሞ ተቃዋሚዎቹ ነበሩ:: ይሁን እንጂ፣ በዚህ አንድ ነገር ይስማማሉ፤ ኢየሱስ ሲመጣ፣ የሚያጓጓ ነገር የሚታይበት ጊዜ ይሆናል:: መማክርቱ በኢየሱስ ደጋፊዎች ላይ የሚያደርጉትን በመፍራት ሕዝቡ በሹክሹክታ እየተከራከሩ ነበር:: ኢየሱስን ለመግደል ማሴራቸው ይፋ ባይወጣም (ዮሐ 7÷20)፣ ሐሳባቸው ግን በኢየሩሳሌም ለሚኖር ሁሉ ግልጽ ነበር (ከዮሐ 7÷25):: መማክርቱ ለኢየሱስ የነበራቸው ጥላቻ በጣም ግልጽ ስለ ነበር እርሱን በመደገፍ እንዳይናገሩ አድርጓቸዋል:: ሰዎችን ከምኩራብ ለማግለል



ሥልጣን ነበራቸው (ዮሐ 9÷22፣34፤ 12÷42 ጋር ያነ):: ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሕይወታቸው ምኩራብ ውስጥ ካለው ኅብረት ጋር ለተቈራኙ ሰዎች ይህ አስፈሪ ቅጣት ነበር::

ዮሐ 7÷14-18

[14]በበዓሉም አጋማሽ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ
ወጥቶ ያስተምር ጀመር:: [15]አይሁድም በመደነቅ፣ «ይህ
ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?» አሉ::
[16]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣
«የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፣ ከላከኝ የመጣ
ነው:: [17]ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ
ቢፈልግ፣ የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል፤
[18]ከራሱ የሚናገር፣ ያን የሚያደርገው ለራሱ ክብርን ለማግኘት ነው፤ ለላከው ክብር
የሚሠራ ግን እርሱ እውነተኛ ነው፤ ሐሰትም አይገኝበትም::

በበዓሉ ሦስተኛ ወይም አራተኛ ቀን ኢየሱስ በቦታው ደረሰ:: መምጣቱ መሪዎቹን በጣም አስገርሟቸዋል:: ከዚያ በላይ የገረማቸው ደግሞ የኢየሱስ እንግዳ ትምህርት ነበር (ማቴ 7÷28-29፤ማር 1÷22፤ ሉቃ 2÷46-47):: ሌላው በጣም አስገራሚ ነገር በቂ የትምህርት ማስረጃ ያልነበረው መሆኑ ነው::[1] የንግግራቸው ሰወር ያለ አንደምታ፣ ከእውነተኛው አስተምህሮ እንዳይስት የሚመራው ስለ ሌለ፣ ራሱን በራሱ ባስተማረ ሰው መተማመን አትችሉም የሚል ይሆናል:: ኢየሱስ ግን ለዚህ የሰጠው መልስ፣ «እኔ ራሴን በራሴ ያስተማርሁ አይደለሁም:: መሪዬ እግዚአብሔር ነው!» የሚል ነበር:: በእግዚአብሔርና በሰው ትምህርት መካከል ምንም ዓይነት ንጽጽር ሊኖር አይችልም::

---

[1] ቃል በቃል፣ «ይህ ሰው መልእክቶችን እንዴት ያውቃል» [grammata] በቀጥታ ደብዳቤዎችን (ገላ 6÷11)፣ መልእክቶችን (ሐሥ 28÷21)፣ ወይም ቅዱሳት መጻሕፍትን ጭምር ከማለቱ ባሻገር (2ጢሞ 3÷15)፣ ጠቅላላውን ሥርዐተ ትምህርት ይመለከታል::

ቊጥር 17 ለእግዚአብሔር የሚታዘዙ እውነቱን እንደሚረዱ ይናገራል:: ኢየሱስ ይህን ሲል፣ «ትምህርቴን መርምሩ:: በሕይወታችሁ የማይሠራ እንደ ሆነም ዐይታችሁ ፍረዱ!» የማለት ያህል ነበር:: «ደስ የማይል» የሚባለው የኢየሱስን ትምህርት (ሌላውን ጉንጭ መስጠትን፣ ወይም የመጨረሻ መሆን መምረጥን) ስንሞክረው የሚሠራ መሆኑን በማየት ደስ ይለናል:: ብዙ እጀታዎች ባሉት ቴሌስኮፕ ለማየት የመሞከር ያህል ነው:: መጨረሻ ላይ ትክክለኛውን ስታገኙ ማንም ትክክለኛነቱን አይነግራችሁም:: ሁሉም ቦታ ቦታውን ሲይዝ ታውቃላችሁ:: የኢየሱስን ትምህርት መከተልም እንዲሁ ነው::

መሪዎቹ ኢየሱስ ራሱን ያስተማረ እንደ ነበር አስበዋል:: ከታዋቂ የአይሁድ መምህራን ሳይጠቅስ፣ በገዛ ራሱ ሥልጣን ነበር የሚናገረው (ማቴ 7÷28-29):: ሕዝቡን በማሳሳት የተከሰሰው በዚህ ምክንያት ነበር:: ቊጥር 18 ላይ ኢየሱስ ይህን ክስ ሲያስተባብል እንመለከታለን:: ወደ ዮሐንስ 5÷30-47 ተመልሰን ኢየሱስ ያቀረባቸው ምስክሮችን ዝርዝር (እግዚአብሔር፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ የገዛ ራሱን ሥራ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትና ሙሴ) እንመለከታለን:: ኢየሱስ እነዚህን ሁሉ ባይዘረዝርም፣ ዮሐንስ 5 ላይ ያሉ የመጀመሪያና መጨረሻ ምስክሮች፣ እግዚአብሔርና ሙሴን አቅርቧል:: አንድምታው ግን ተመሳሳይ ነበር፤ እናንተ ሰዎች እግዚአብሔርን ወክሎ እንደ መሆኑ መጠን፣ እርሱን አለመቀበል እግዚአብሔርን አለመቀበል ነው (ዮሐ 5÷23-24፣30፤ ማቴ 10÷40)::

ዮሐ 7÷19-24

[19]«ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ነገር ግን
እንዳችሁም ሕጉን አልጠበቃችሁም:: ስምን ልትገድሉኝ
ትፈልጋላችሁ?»
[20]ሕዝቡም፣ «አንተ ጋኔን ያደረብህ! ደግሞ አንተን ማን ሊገድል ይፈልጋል?»
አሉት::



[21]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «አንድ ሥራ ብሠራ፣ ሁላችሁም
ተገረማችሁ:: [22]ግዝረት የመጣው ከአባቶች እንጂ ከሙሴ አይደለም፤ ሆኖም ሙሴ
ግዝረትን ስለ ሰጣችሁ በሰንበት እንኳ ሕፃን ትገርዛላችሁ:: [23]የሙሴ ሕግ እንዳይሻር
ሕፃን በሰንበት የሚገረዝ ከሆነ፣ የሰውን ሁለንተና በሰንበት ስለ ፈወስሁ ስምን በእኔ
ላይ ትቈጣላችሁ? [24]የሰውን ፊት በማየት መፍረድ ትታችሁ ቀን ፍርድ ፍረዱ::

የኢየሱስ መልስ ግልጽና ጠንከር ያለ ነበር:: ለአንድ የሃይማኖት መሪ የሙሴን ሕግ አልጠበቅህም ማለት ፀብ መጋበዝ ነው:: ግን እውነት ነበር:: ምንም ሕጋዊ መሠረት ሳይኖራቸው፣ ተገቢውን ፍርድ በማዛባት መማክርቱ ኢየሱስን ለመግደል እያሴሩ ነበር:: የመግደል ፍላጐትን አስመልክቶ ኢየሱስ ካስተማረው አንጻር ይህ ክስ በጣም ጠንከር ያለ ነበር (ማቴ 5÷21-22):: ሕዝቡ ይህን ባለማወቃቸው ኢየሱስን እንደ ዕብድ (ጋኔን እንዳለበት ሰው) ቈጠሩት::[2] ምናልባትም ሕዝቡ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ መማክርቱ ሳይሆን ስለ እነርሱ እንደ ነበር ገምተው ይሆናል:: ያም ሆኖ ግን በስድስት ወሮች ውስጥ አብዛኞቹ በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ከመማክርቱ ጋር፣ «ስቀለው!» የሚሉበት ጊዜ እየመጣ ነበር::

ኢየሱስ ለሕዝቡ ጥያቄ መልስ ለመስጠት (ቊ 20) በፋሲካ የተፈጸመውን ነገር ያስታውሳቸዋል (ዮሐ 5):: «አንድ ሥራ» ሲል፣ አንካሳውን በሰንበት መፈወሱን ማመልከቱ ነበር:: ሌሎች ብዙዎችን ማቅረብ ይችል ነበር (2÷23፤ 3÷2)፣ ይህኛው ግን የግድያ ሐሳባቸውን ያንጸባርቃል (5÷18):: የተረበሹት በተአምሩ አልነበረም:: ያስቈጣቸው በሰንበት ቀን መፈወሱ ነበር:: በወጋቸው መሠረት በሰንበት መፈወስ አጥብቆ የተከለከለ ነበር (የ§ 51 ማብራሪያ ይመ):: አሁን ደግሞ ኢየሱስ የእነዚህ ሰው ሠራሽ ሕጎችን ከንቱነት ሊያሳይ ነው (§ 50 ጋር ያነ)::

---

[2] በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በጋኔን ስለ መያዝ የሚናገረው ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ከሆነ፣ የሚያመለክተው እብደትን ነው (ከ8÷48-52፤ 10÷20-21 ጋር ያነ)::

ግርዛት ለአይሁድ ከምንም ነገር ይልቅ የተቀደሰ ነበር:: የአንድ ወንድ አይሁዳዊ መለያ ግርዘት ነበር:: (ኢየሱስ ባመለከተው መሠረት የአብርሃምን ዘመን ይዞ ከአይሁዳዊነት በፊት የነበረ ሥርዓት ቢሆንም፣ ዘፍ 17÷9-14):: በጣም የተቀደሰ ከመሆኑ የተነሣ በደንቡ መሠረት በስምንተኛው ቀን ግርዘት ለመፈጸም ሌላው ቀርቶ ሰንበት እንኳ ይሻር ነበር:: መልእክቱ ግልጽ ነው:: በእግዚአብሔር ፊት ከሥርዓት ይልቅ ሰዎች ይበልጣሉ:: የሙሴ ሥርዓት ሕግ እንዳይሻር፣ ሰንበት ራሱ መሻር ነበረበት:: ታዲያ፣ ሰዎችን ለመርዳት ሲባል፣ ሰንበት ቢሻር ምናለበት! ቊጥር 24 ላይ ያለው ተግሣጽ ለመማክርቱ የነበረውን ያህል ለቤተ ክርስቲያንም ጠንከር ያለ መልእክት አለው (ከ1ሳሙ 16÷7 ጋር ያነ):: ከሰው ፍላጐት ይልቅ ሃይማታዊ ሥርዓት የሚቀድም ከሆነ ለእግዚአብሔር ተገቢው ክብር አልተሰጠም ማለት ነው:: ጉዳዩ መፋታትን፣ ኤድስን፣ ጦርነትን፣ ቤት ማጣትን፣ ትምህርትን ወይም የዘር ግጭትን የሚመለከት ቢሆንም እንኳ ለእግዚአብሔር ከሃይማኖታዊ ሥርዐት ይልቅ የሰዎች ፍላጐት ይበልጣል::

ዮሐ 7÷25-31

25በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩ አንዳንድ ሰዎች
እንዲህ አሉ፤ «ሊገድሉት የሚፈልጉት ሰው ይህ
አይደለምን? 26ይኸው እርሱ በአደባባይ ይናገራል፤ አንድም
ቃል አይናገሩትም፤ ክርስቶስ ነው ብለው ባለ ሥልጣኖቹም ተቀብለውት ይሆን? 27ይህ
ሰው ግን ከየት እንደ ሆነ እኛ እናውቃለን፤ ክርስቶስ ሲመጣ እኮ ከየት እንደ ሆነ
ማንም አያውቅም::»

28ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አደባባይ ሲያስተምር
ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤ «እኔን፣ እኔን
ታውቁኛላችሁ፤ ከየት እንደ ሆንሁም ታውቃላችሁ:: እኔ
እዚህ ያለሁት በገዛ ራሴ አይደለም፤ ነገር ግን የላከኝ እርሱ እውነተኛ ነው:: እናንተ
አታውቁትም፤ 29እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ስለ ሆንሁ፣ እርሱም ስለ ላከኝ ዐውቀዋለሁ::»



30ስለዚህ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን
አላሳረፈበትም፤ 31ሆኖም ከሕዝቡ ብዙዎች በእርሱ አምነው፣ «ታዲያ፣ ክርስቶስ ሲመጣ
ይህ ሰው ከሚሠራቸው ታምራዊ ምልክቶች የበለጠ ያደርጋል?» አሉ::

ምንም እንኳ ከሌላ አገር የመጡት የእምነት ተጓገሮች ስለ አይሁድ አድማ የሚያውቁት ባይኖርም፣ የአገሬው ሰዎች ግን ነገሩን ያውቁ ነበር:: የአይሁድ መማክርት አባሎች ሲያጉረመርሙ ሰምተዋል:: ኢየሱስ በእንዲህ ያለ ድፍረት በግልፅ መናገሩ አስደንግጧቸዋል [*parresia*] (ከዕብ 4÷16 ጋር ያነ):: ሌላው ቀርቶ «ክርስቶስ ነው ብለው ባለ ሥልጣኖቹም ተቀብለውት ይሆን?» በማለት የጠየቁት እንኳ አሉታዊ መልስ በመጠበቅ ነበር:: ግን፣ ባለ ሥልጣኖቹ ምን ያደርጉ ይሆን? ኢየሱስ ላይ አድማ እያደረጉ መሆኑን ከሌላ አገር የመጡት ካወቁ በእነርሱ ላይ ይነሡባቸዋል:: እንዲህ ከሆነ ኢየሱስ ትክክል እንደ ነበር የሚያረጋግጥ ይሆናል (ቊ 19):: በየጊዜው አቋማቸውን የሚለዋውጡ ሕዝብ፣ ተጠቂውን ሰው ሊደግፉ ይችላሉ::

አብዛኛዎቹ የኢየሩሴም ነዋሪዎች ግን ኢየሱስ መሲሕ እንዳልሆነ ድምዳሜ ላይ ደርሰው ነበር:: ለዚህ የሚያቀርቡት ምክንያት የተጣመመና የተሳሳተ ነበር:: አስተሳሰባቸው የተጣመመ እንደ ሆነ የተገለጠው መሲሕ ያለ ምንም ሥጋዊ ወላጆች በተአምር ከሰማይ ይወርዳል በማለታቸው ነበር:: የተሳሳቱ ነበሩ የተባለውም ኢየሱስ ከገሊላ የመጣ ነው ብለው በማሰባቸው ነበር (ቊ 41፤ ከ6÷42 ጋር ያነ)::

የኢየሱስን ምላሽ ስላቅ ብለን መተርጐም የምንችለው ዐይነት ነበር::[3] «እናንተ ሰዎች ከየት እንደ መጣሁ የምታውቁ ይመስላችኋል!

---

[3] አባባሉ ስላቅ ነበር የምንልበት ምክንያት የሚከተሉት ናቸው፤ (1) ይህንኑ ተከትሎ መማክርቱ ሊይዙት መሞከራቸው (ቊ 30):: (2) በትክክለኛው መንገድ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ ከየት እንደ መጣ የእነርሱን ስሕተት

ሆኖም የላከኝን እስካላወቃችሁ ድረስ እኔ ከየት እንደ ሆንሁ በፍጹም አታውቁም! ካደመጣችሁኝ ስለ እርሱ ማንነት እነግራችኋለሁ» (ከዮሐ 8÷42-43፣55-59)። በዚህ አባባሉ ኢየሱስ ሕዝቡ አንዱን እንዲመርጡ ምርጫ አቀረበላቸው። ግልጽ የወጣ ጥላቻና ተቀባይነት ማግኘት ይኖራል። ሕዝቡ ኢየሱስ ማድረግ የሚችለውን አይተዋል። ይህ ትኩረታቸውን ስቧል። አሁን ደግሞ ለአይሁድ መሪዎች እየተናገረ ያለውን እየሰሙ ነው። የአስተሳሰቡ ግልጽነት፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ጥርት ያሉ መሆናቸው፣ ድፍረቱ፣ በማንም ሥልጣን አለመደገፉና ጥልቅ ስብከቱ ወደ እርሱ ስቧቸዋል። ምንም እንኳ መሲሕ ባይሆንም፣ ያደረጋቸው ተአምራት ሁነኛ ስፍራ እንደሚያሰጡት ግልጽ ነበር። ስለሆነም ከጌታ ጋር ወገኑ።

**§ 96ለ**
**ኢየሱስን ለመያዝ የተደረገው ሙከራ አለመሳካት**
**(ዮሐ 7÷32-52)**

32ፈሪሳውያን፣ ሕዝቡ ስለ እርሱ በጉምጉምታ
የሚነጋገሩትን ነገር ሰሙ፤ የካህናት አለቆችና
ፈሪሳውያንም እንዲይዙት የቤተ መቅደስ ጠባቂዎችን
ላኳቸው።
33ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ «ከእናንተ ጋር
የምቆየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ 34ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን
አታገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ አትችሉም።»
35አይሁድም እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባባሉ፤ «ይህ ሰው፣ ልናገኘው
የማንችለው ወዴት ለመሄድ ቢያስብ ነው? በግሪኮች መካከል ተበታትነው ወደሚኖሩ
ወገኖቻችን ሄዶ ግሪኮችን ሊያስተምር ፈልጎ ይሆን? 36'ትፈልጉኛላችሁ ግን አታገኙ
ኝም'፤ ደግሞም፣ 'እኔ ወዳለሁበት ልትመጡ አትችሉም' ሲል ምን ማለቱ ይሆን?»

---

አያረጋግጥም ነበር። (3) ኢየሱስ ሰዎች ባለማወቅ በተቃውሞ ሲነሡበት በሰላቅ አነጋገር ይጠቀም ነበር።



ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ብዙውን ጊዜ አይስማሙም (ሐሥ 23÷6-8 ጋር ያነ)። አሁን ግን የጋራ ጠላት አግኝተዋል። ኢየሱስን እንዲይዙ ጠባቂዎቻቸውን ላኩ። ሆኖም፣ ከትምህርቱ ኀይል ማምለጥ አልቻሉም።

ስለ እርገት እያስተማረ በነበረው ተማርከዋል (ቍ 33-34)። እንደ ክርስቲያኖች ይህን ለመረዳት የሚያስችል ማጣቀሻ አልነበራቸውም። እነርሱ ማሰብ የቻሉት ኢየሱስ ግሪኮች በበዙበት አካባቢ ተበትነው ወዳሉ አይሁድ ለመሄድ መፈለጉን ብቻ ነበር። ኢየሱስ ራቅ ብሎ ወደ አሕዛብ ክልል ከሄደ ከአይሁድ መማክርት ጥቃት ነጻ ይሆናል። ይሁን እንጂ ተበትነው ያሉት ወገኖች ከኢየሩሌም በጣም የመራቃቸውን ያህል፣ ኢየሱስ ምን ማለቱ እንደ ነበር ከመረዳትም የራቁ ይሆናሉ። ያም ሆኖ ግን የኢየሱስ የስላቅ አነጋገር የእግዚአብሔር መንግሥት በድል እንደምትስፋፋ የሚያመለክት ትንቢት ነበር።

ኢየሱስ ለእነርሱ ፌዝ መልሱን ሰጠ። አንድ ቀን ይፈልጉታል፤ ሆኖም ሊያገኙት አይችሉም (ቍ 34)። አሞጽ 8÷11-12 ተመሳሳይ ዐይነት ሐሳብ ያስቀምጣል፤

> «በምድር ላይ ረሐብን የምሰድበት ዘመን ይመጣል፤ ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል የመስማት ረሐብ እንጂ፣ እንጀራን የመራብ ወይም ውሃን የመጠማት አይደለም። ሰዎች እግዚአብሔርን ለመሻት፣ ከባሕር ወደ ባሕር፣ ከሰሜን ወደ ምሥራቅ ይንከራተታሉ፤ ነገር ግን አያገኙትም።

**ዮሐ 7÷37-39**

37የበዓሉ መጨረሻ በሆነው በታላቁ ቀን፣
ኢየሱስ ቆሞ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አለ፤ «ማንም
የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ 38በእኔ
የሚያምን፣ ጽሑፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል። 39ይህን ያለው
በእርሱ የሚያምኑ ስለሚቀበሉት መንፈስ ነበር፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ገና ስላልከበረ
መንፈስ አልተሰጠም ነበር።

የበዓሉ መጨረሻ ቀን፣ በዓሉ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያበቃበት ሰባተኛ ቀን ወይም ደግሞ ለትምህርት የሚያደምጡበት ስምንተኛው ቀን ሊሆን ይችላል::[4] ይሁን እንጂ ስምንተኛው ቀን የበዓሉ መደበኛ አካል ስላልነበረ፣ «የበዓሉ ታላቁ ቀን» ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ እዚህ ላይ ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ስለ ሰባተኛው ቀን እንደ ነበር መገመት እንችላለን::[5]

ላለፉት ሰባት ቀኖች ካህኑ ወደ ሰሊሆም ምንጭ በመሄድ ወርቃማ እንስራውን በውሃ ይሞላ ነበር:: ውሃውን ይዞ ወደ መቅደስ ሲመለስ፣ ሕዝቡ ይከተሉት ነበር:: ይህን መሥዋዕት ወደ መሰዊያው ሥር ሰርጐ እንዲገባ ጉድጓዳ ሳህን ላይ ሲያፈሰው ይመለከቱ ነበር:: ወይን ጠጅም እንዲሁ ተመሳሳይ ዐይነት ሳህን ውስጥ እንዲፈስና የመሰዊያውን ሌላ ወገን እንዲሞላ ይደረግ ነበር:: ይህን ሲያደረጉ፣ ኢሳይያስ 12÷3 ላይ ያለውን፣ «ከድነቴ ምንጮች ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ» የሚለውን በቃላቸው ያነበንቡ ነበር:: ይህ ሥርዓት እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለሕዝቡ በተአምር ውሃ መስጠቱን

4 ዘሌ 23÷34-36፣ «እስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው፣ ሰባተኛውም ወር በገባ በዐሥራ አምስተኛው ቀን የእግዚአብሔር የዳስ በዓል ይጀምራል፤ እስከ ሰባት ቀንም ይቆያል:: የመጀመሪያው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ ነውና የተለመደ ተግባራችሁን አታከናውኑበት:: ሰባት ቀን መሥዋዕቱን በእሳት ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ በስምንተኛው ቀን የተቀደሰ ጉባኤ አድርጉ፤ መሥዋዕትን በእሳት ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ የተለመደ ተግባራችሁንም አታከናውኑበት::

5 ከአምስት መቶ ዓመት በፊት በዚሁ ቀን፣ ከዚሁ ቦታ ብዙም ባልራቀ ስፍራ ሆኖ ነበር ሐጌ የሚከተለውን ትንቢት የተናገረው፣ «ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ 'በቅርቡ ጊዜ እንደ ገና ሰማያትንና ምድርን፣ ባሕሩንና የብሱን አንድ ጊዜ አናውጣለሁ:: ሕዝቦችን ሁሉ አናውጣለሁ፤ የሕዝቦችም ሀብት ሁሉ ወደዚህ ይመጣል፣ ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ' ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር:: 'ብሩ የእኔ ነው ወርቁም የእኔ ነው' ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብብሔር ጸባኦት፤ የዚህ የአሁኑ ቤት ክብር ከቀድሞው ቤት ክብር ይበልጣል ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት፤ በዚህም ቦታ ሰላምን እሰጣለሁ ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ጸባኦት (ሐጌ 2÷6-9)::



የሚያሳስብ ነበር:: ድራማ መሰል በሆነ ሁኔታ ይህን ሲያደርጉ ኢየሱስ ቆመና ጮክ ብሎ ስለ የሕይወት ውሃ ተናገረ:: እርሱ ተአምራዊ ውሃ የመነጨበት ዓለት መሆኑን እያመለከተ ነበር (1ቆሮ 10÷4)::

ቅንፍ ውስጥ ባለ ማስታወሻ[6] ኢየሱስ እንዲህ ሲል ምን እያሰበ እንደነበር ዮሐንስ ያመለክታል:: ከእርገቱ በኋላ መንፈስ ቅዱስ የክርስቲያን የሁልጊዜ አጋር እንደሚሆን ኢየሱስ ተስፋ እየሰጠ ነበር (ዮሐ 14÷16-19፤ 16÷5-7)::[7] ከብዙ ጊዜ አስቀድሞ ብሉይ ኪዳን በውሃ ምሳሌነት እንደሚመጣ ሲያመለክት ነበር (መዝ 46÷4-5፤ ኢሳ 32÷15፤ 44÷3፤ 55÷1፤ 58÷11፤ ሕዝ 39÷29፤ ኢዮ 2÷28):: ቍጥር 38 ላይ ኢየሱስ በአእምሮው ይዞ የነበረው የትኛውን ክፍል ነበር? ይህን በተመለከተ ጥቂት የማይባሉ ሐሳቦች ቀርበዋል (ለምሳሌ ዘፀ 17÷5-6፤ ዘኍ 20÷7-11፤ መዝ 78÷15-16፤ ምሳ 5÷15፤ 18÷4፤ ኢሳ 12÷3፤ 58÷11፤ ዘካ 13÷1 እና ሌሎችም):: እንደ ዶድ ከሆነ ኢሳይያስ 12÷3፤ ሕዝቅኤል 47÷1-10 እና ዘካርያስ 14÷8 በሙሉ የዳስ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ለሕዝቡ ይነበቡ ነበር::[8] በተለይ ደግሞ ሕዝቅኤል 47÷1-10 አግባብነት ያለው ይመስላል:: በሺህ ዓመቱ ዘመን ከቤተ መቅደስ ስለሚመነጭ ውሃ ነው የሚገልጸው:: ይህ ክርስቲያንን አስመልክቶ የተቀመጠ ግሩም መገለጫ ነው፤ ምክንያቱም በውስጡ ከሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የተነሣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመሆኑ ነው (1ቆሮ 6÷19-20)::[9]

6 ዮሐንስ በቅንፍ ያሰፈራቸው ሌሎች ማስታወሻዎችን ከ2÷21፤ 6÷6፣71፤ 11÷51፤ 12÷6፣33፤ 21÷19ን ይመ::

7 ሌላው አማራጭ፣ «ውሃ» የሚመነጨው ከክርስቲያኑ ሳይሆን ከኢየሱስ ነው የሚል ነው:: ሆኖም ይህ የሚያስኬድ አይመስልም:: G. Fee, "Once More - Jn 7:37-39," *ExpT* 89 (1978): 116-118.

8 C.H. Dodd, *The Interpretation of the Fourth Gospel* (Cambridge: University Press, 1953), p. 349.

9 Z.C. Hodges, "Rivers of Living Water," *BibSac* 136 (1979): 239-248.

ውሃ ጠቃሚ ትእምርት ነው::[10] በፓለስቲና አካባቢ እንደ አርኪ ብቻ ሳይሆን እንደ ሕይወትም ይታሰባል:: በተመሳሳይ መልኩ መንፈስ ቅዱስ አብሮን የሚኖር ብቻ አይደለም:: ሕይወት ይሰጠናል፤ በሮሜ 8÷10-11 መሠረት ለሥጋችን እንኳ ሕይወት ይሰጣል (ከሕዝ 47÷9 ጋር ያነ):: በኤደን በተጀመረው ኀጢአት ምክንያት መንፈሳችን ያንቀላፋ (ለምሳሌ የሞተ) ያህል ነው:: ሆኖም ክርስቶስ በሞቱ የኀጢአትን ቅጣት ከከፈለ በኋላ ግን፣ የኤደን መርገም ተወግዶ በውስጣችን በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ (ከራእ 22÷17 ጋር ያነ) እንደገና ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስ እንጀምራለን (ዘፍ 3÷8)::

ዮሐ 7÷40-44

40ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ቃሉን ሰምተው፣ «ይህ
ሰው በእርግጥ ነቢዩ ነው» አሉ::
41ሌሎችም፣ «እርሱ ክርስቶስ ነው» አሉ::
ሌሎች ደግሞ እንዲህ አሉ፤ «ክርስቶስ ከገሊላ እንዴት ሊመጣ ይችላል?
42መጽሐፍ፣ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር፣ ዳዊትም ከኖረበት ከቤተልሔም እንደሚመጣ
ይናገር የለምን?» 43ስለዚህም በኢየሱስ ምክንያት በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ፤
44አንዳንዶቹም ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ማንም እጁን አላሳረፈበትም::

ይህ ከባድ ትምህርት የሕዝቡን አስተሳሰብ ለሦስት ከፈለ:: አንዳንቾቹ፣ «ነቢይ» ነው በማለት አሰቡ:: ይህ ኢየሱስ መሲሑ ነው ከማለት የራቀ አይደለም:: ምናልባትም ይህን ያሉት ዘዳግም 16÷15-18ን እያሰቡ ሊሆን ይችላል (ከዮሐ 1÷20-21 ጋር ያነ):: አንዳንዶች ደግሞ፣ «መሲሑ ነው» በማለት በተለየ ሁኔታ ጥንቃቄን በተከተለ መንገድ እምነታቸውን ገልጸዋል:: ሦስተኞቹ ወገኖች የመጣው ከቤተ ልሔም ሳይሆን ከገሊላ በመሆኑ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን አልተቀበሉም:: ምንም እንኳ የብሉይ ኪዳን ግንዛቤያቸው ቍ. 27 ላይ ካሉት የተሻለ ቢሆንም (ከሚክ 5÷2፤ ማቴ 2÷5-6 ጋር ያነ) የኢየሱስን ታሪክ በተመለከተ እነርሱም ቢሆኑ ያልተረዱት ነገር ነበር:: ኢየሱስ በቤተልሔም መወለዱን ለምን እንዳልነገራቸው መገረማችን አይቀርም:: ምናልባትም ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ነው የሚለው የተሳሳተ ክስ እንዳይነሣ ስለ ፈለገ ይሆናል:: ምናልባትም ቢነግራቸውም ከዝሕቡ ጩኸት የተነሣ አልተሰማ ይሆናል:: ይህንኑ ንግግሩን የጀመረው ከፍ ባለ ድምፅ ነበር (ቍ. 37)::

የሕዝቡ መከፋፈል ተራ ዐይነት አለመግባባት አልነበረም:: በአንዳንድ ወገኖች የሚደገፉ ጠባቂዎች ኢየሱስን ለመያዝ ተዘጋጅተው ነበር:: ሌላው ወገን ደግሞ ኢየሱስን በመደገፍ ቆሟል:: ብዙዎች በተለይም ከሌሎች አገሮች የመጡት በዚህ መንፈሳዊነት በሌለው ሁኔታ ተደናግጠው ገለልተኛ ሆነው መቆማቸውን ማሰብ ይቻላል:: ምናልባትም የመካከለኛው ምሥራቅ ሰዎችን ጭቅጭቅ በተመለከተ እዚህ ላይ የራሳችንን ግምት ብንሰጥ ብዙም አንርቅም:: ሆኖም በእግዚአብሔር ቅደም ተከተላዊ አሠራር መሠረት ኢየሱስ ከሰዎች መከፋፈል በላይ ነበር (ዮሐ 2÷4፤ 7÷30፤ 7÷44)::

ዮሐ 7÷45-52

45በመጨረሻም የቤተ መቅደስ ጠባቂዎቹ፣ ወደ
ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን ተመልሰው ሄዱ፤
እነርሱም ጠባቂዎቹን፣ «ለምን አላመጣችሁትም?»
አሏቸው:: 46ጠባቂዎቹም፣ «እንደዚህ ሰው፣ ከቶ ማንም
ተናግሮ አያውቅም» ሲሉ መለሱ::
47ፈሪሳውያንም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ «እናንተም ተታለላችኋል ማለት ነው?
48ለመሆኑ ከባለ ሥልጣኖችና ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለ? 49ሕጉን የማያውቅ ይህ
ሕዝብ ግን የተረገመ ነው::»

---

[10] S.H. Hooke, "The Spirit Was Not Yet," *NTS* 9 (1962-63): 372-380 እንደሚያመለክተው አብዛኛው በዮሐንስ ወንጌል ስለ ውሃ የሚናገረው ክፍል በምሳሌያዊ አነጋገር መወሰድ ያለበት ነው (ከዮሐ 2÷9፤ 3÷5፤ 4÷10-15፤ 5÷7፤ 6÷35፤ 7÷37-38፤ 19÷34 ጋር ያነ)::

[50]ከዚህ ቀደም ወደ ኢየሱስ ሄዶ የነበረውና ከእነርሱ አንዱ የሆነው
ኒቆዲሞስ እንዲህ አላቸው፤ [51]«ሕጋችን፣ አስቀድሞ አንድን ሰው ሳይሰማና ምን
እንዳደረገ ሳይረዳ ይፈርድበታልን?» [52]እነርሱም፣ «አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ
ከገሊላ እንደማይነሣ መርምር፤ ትደርስበታለህ» ብለው መለሱለት።

ጠባቂዎቹ ባዶ እጃቸውን በመመለሳቸው ፈሪሳውያኑና የካህናት አለቆቹ ተቆጡዋቸው። በየአደባባዩ የሚሳፍራቸውን ይህን ዋነኛ ጠላት እጃቸው ማስገባት አልሆነላቸውም። የቱንም ያህል ጥረት ቢያደርጉም ይህን ከገሊላ የመጣ ገጠሬ መያዝ አልቻሉም! በጊዜው እጅግ ከመቁሰላቸው የተነሣ በየትኛውም ጊዜ ጥቃት ሊሰነዝሩ ይችላሉ። ጠባቂዎቹ፣ በአነጋገሩ መማረካቸውን ነገሯቸው። መሪዎቹ የጠባቂዎቹን አነጋገር የደገፉ ይመስላል፤ እነርሱ ራሳቸውም ቢሆኑ። ይሁን እንጂ «ሰው» [anthropos] የሚለው ቃል ዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ አጽንዖት ባለው ሁኔታ ነው የተቀመጠው። ይህ ደግሞ ኢየሱስ ከሰው የበለጠ መሆኑን ጠባቂዎቹ ሳያምኑ እንዳልቀረ ሊያመለክት ይችላል።

ፈሪሳውያን የአነጋገር ጥበብ ያላቸው ነበሩ። እዚህ ላይ ችሎታቸውን ጠባቂዎቹን ለማጥቃት ተጠቅመውበታል። የአባባላቸው አንኳር ሐሳብ፣ «ሕዝቡ የማይማን ጥርቅም ናቸው። በቀላሉ ይስታሉ። እናንተም፣ እንደነዚያ መደዴዎች እየሆናችሁ ነው። እነርሱ ዐላዋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ርጉማንም ናቸው!» የማለት ያህል ነበር። ፈሪሳውያኑ ያሰቡት ሳይሳካ ሲቀር ትክክለኛ ማንነታቸውን አሳዩ። ሥልጣናቸውና የያዙትን አስተሳሰብ ለማይደግፉ ሁሉ ትዕቢተኞችና ክፉዎች ነበሩ።

ምንም እንኳ አንድም ፈሪሳዊ በኢየሱስ አለመማመኑ ቢናገሩም፣ ኒቆዲሞስ ካመኑት ወገን ነበር። በኢየሱስ ማመን ብቻም ሳይሆን፣ ሌሎችም መኖራቸውን በግልጽ አመልክቷል (ዮሐ 3፥1-2)። ኒቆዲሞስ እንደ ሥልጡን ሰው ምክንያታዊ ሆኖ ነበር የሚናገረው። የመጣለትን ሐሳብ ሁሉ አይዘረግፍም። ይልቁንም በጥያቄ ይፈትነዋል። ማንኛውም ከወገናዊነት የጠራ ሰው እርሱ ባነሣው የፍትሕ ነክ ጥያቄ ይስማማል (ዘዳ 1፥16-17)። መማክርቱ በፍርድ ሂደቱ አንድ ዐይነት ውሳኔ ለማሳለፍ ተዘጋጅተው ነበር። ኒቆዲሞስና አብረውት የነበሩ ግን የሞት ፍርድን አይቀበሉም። እንደ ባልደረቦቻቸው ሁሉ ጠባቂዎቹንም መልስ አሳጥተዋል። ያቀረቡት ክስ ኒቆዲሞስ ላቀረበው ጥያቄ የሚመጥን አልነበረም።

ነቢይ ከገሊላ እንደማይመጣ ተናግረዋል። ይህ ግን ሐሰት ነው። ዮናስ የመጣው ከገሊላ ነበር (2ነገ 14፡25)፤ ምናልባት ሆሴዕና ናሆምም እንዲሁ። ይሁን እንጂ እነርሱ ላነሡት ጥርጥር አንድ ተጨማሪ ነጥብ እንጨምራለን (ከአንድ ጥንታዊ ቅጂ መመልከት እንደሚቻለው?)። «ነቢዩ» ከገሊላ አይመጣም። ይህም፣ «መሲሑ» ከገሊላ አይመጣም ማለት ነው። ከፍተኛ የብሉይ ኪዳን ዕውቀት ያላቸው ከመሆናቸው አንጻር ይህ ይበልጥ አሳማኝ ነው።

### § 97 በምንዝር የተያዘች ሴት (ዮሐ 7፥53-8፥11)

ይህን ክፍል ከማንበባችን በፊት አዲሱ መደበኛ ትርጉም በቅንፍ እንዳሰፈረው እንመለከታለን። የግርጌ ማስታወሻቸው፣ «የጥንት ቅጆች ዮሐንስ 7፥53-8፥11 የላቸውም» የሚል አስፍረዋል። ይህ እውነት ነው። እንዲያውም፣ ከስድስተኛው መቶ ዓመት በፊት በነበሩ ቅጂዎች ውስጥ አይገኝም። ይህን የጻፈው ዮሐንስ ሳይሆን፣ በኋላ የመጣ ሌላ ጸሐፊ ነበር ብለን እንድንጠራጠር የሚያደርጉን ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም ይኖራሉ። (1) ቢካተት እንኳ ታሪኩ የተፈጸመበትን ስፍራ ጨምሮ አንዳንድ የሐሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ። አንዳንድ ቅጂዎች ከ7፡36 በኋላ አስቀምጠውታል፤ አንዳንዶች ዮሐንስ መጨረሻ ላይ፣ ሌሎች ከሉቃስ 21፥38 በኋላ አስቀምጠውታል። የተወሰኑት እዚህ ላይ ቢያስፍሩትም፣ አጠራጣሪ ነገር መኖሩንም አመልክተዋል። «ጥንታውያን ጸሐፊዎች

አላካተቱትም፤ ከአርዮስ በፊት ከነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ እንኳ አልጠቀሱትም ... ያሉት ጥቃቅን ልዩነቶች መብዛታቸው ታሪካዊ ፋይዳው አጠራጣሪ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል» (Tenney p. 91):: (2) መካተቱ በ7÷52 እና 8÷12[11] መካከል ያለውን የሐሳብ ፍሰት ያሰናክላል:: በተጨማሪም 7÷53 ስለ መማክርቱ ስብሰባ እየተናገረ እያለ ስለ ሕዝቡ ወደየቤታቸው መሄድ የሚነግረን ቅደም ተከተሉን ሳይጠብቅ በድንገት ነው:: (3) ትክክል እንደሆነ ከተቀበልን ዮሐንስ ስለ ጸሐፍት የተናገረውና ኢየሱስ ሲጽፍ የምንመለከተው እዚህ ቦታ ብቻ ይሆናል:: (4) ታሪኩ ውስጥ አንዳንድ ለመግለጽ የሚያስቸግሩ ነገሮች አሉ፤ የመፍረድ ሥልጣን ለኢየሱስ የተሰጠው ለምንድን ነው? ሴትዮዋን ወደ ኢየሱስ ሲያመጡ፣ ከእርሷ ጋር ያመነዘረውን ሰው ያላመጡት ለምድን ነው? እነዚህ ሁሉ ምናልባት ዮሐንስ 7÷53-8÷11 የመጀመሪያው የዮሐንስ ወንጌል ቅጂ አካል እንዳልነበረ ያመለክታሉ::[12]

ይህ ክፍል ትክክለኛ አይደለም ማለት የታሪክ ድጋፍ የለውም ማለት አይደለም:: በሌላ አነጋገር ምናልባት የመጀመሪያው የዮሐንስ ወንጌል አካል አልነበረም:: ሆኖም የኢየሱስን ሕይወት ታሪክ አስመልክቶ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የነበረ ትውፊትን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይችላል:: የዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረው ፓፒያስ ይህን ታሪክ እንደሚያውቅ ግልጽ ነው:: አውሳቤዎስ ደግሞ፣ «ፓፒያስ በብዙ

[11] የዳስ በዓል ሁነኛ ትዕምርት ስለ ሆኑት ውሃ (ዮሐ 7÷38-39)፣ እና ብርሃን (8÷12) የተነገረው በበዓሉ የመጨረሻ ቀን ነው (ዮሐ 7÷37):: በምንዝር የተያዘችው ሴት ታሪኩን ወደ ዮሐ 8÷12 በመግፋት በዓሉ ካለቀ በኋላ ሁለተኛው ቀን ላይ ያደርገዋል:: በተጨማሪም ዮሐ 8÷12፤ ኢሳ 9÷1-2ን በማመልከት ዮሐ 7÷52 ላይ ለተነሳው ጥያቄ መልስ ይሰጣል (cf. P. Comfort, "The Pericope of the Adulteress," *BT* 40/1 (1989): 145-147).

[12] ሰፋ ላለ ዝርዝር G.M.Burge, "A Specific Problem in the N.T. Text and Canon: The Woman Caught in Adultery (Jn 7:53-8:11)" *JETS* 27/2 (1984): 141-148 ይመ:: ይሁን እንጂ ትክክለኛ መሆኑን ከመደገፍ አንጻር Z. Hodges "The Woman Taken in Adultery (Jn 7:53-8:11): The Text," *BibSac* 137 (1979): 318-332 ይመ::



ኃጢአቶች ተከሳ ጌታ ፊት ስለ ቀረበች ሌላ ሴት ታሪክ ጽፎአል፣ ይህንንም የዕብራውያን ወንጌል አስፍሮታል» በማለት ይገልጻል (*Ecclesiastical History* III, 39.17):: አውግስጢኖስ ደግሞ፣ (*De adulterinis Conjugiis* II, 7) ይህ ታሪክ ከሌሎች ቅጂዎች እንዲወጣ የተደረገው፣ አመንዝራዎችን እንዳያደፋፍር ነበር:: ራስን የመጨቆን ሁኔታ እየተስፋፋ በነበረበት ጊዜ እንዲህ መደረጉ ለምን ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን:: ስለዚህ ይህን ክፍል እንደ አንድ የኢየሱስ ሕይወት ገጽታ እንመለከተዋለን:: ሆኖም የዮሐንስ ወንጌል ክፍል መሆኑ አጠራጣሪ ከመሆኑ አንጻር ቀለል አድርገን ነው የምንወስደው::

ዮሐ 7÷53-8÷5

[53]ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደየቤታቸው ሄዱ::
[1]ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ::
[2]በማለዳም በቤተ መቅደስ አደባባይ እንደ ገና ታየ፤
ሕዝቡም በዙሪያው ተሰበሰበ፤ ሲያስተምራቸውም ተቀመጠ:: [3]የኦሪት ሕግ መምህራንና
ፈሪሳውያን በምንዝር የተያዘች ሴት አመጡ፤ በሕዝቡም ፊት አቁመዋት፣ [4]ኢየሱስን
እንዲህ አሉት፤ «መምህር ሆይ፣ ይህች ሴት ስታመነዝር ተያዘች፤ [5]ሙሴም፣ እንደዚች
ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ በሕጉ አዞናል፤ አንተስ ምን ትላለህ?»

ከቀኑ ከባድ ክርክር በኋላ ሌሊቱን ለማሳለፍ እያንዳንዱ ወደ ቤቱ ሄደ:: በዚህ ጊዜ በዓሉ አብቅቶ ስለ ነበር፣ «ድንኳኖቻቸውን» አፍርሰው እንደ ገና በዐልጋ ለመተኛት ሄደዋል:: ኢየሱስ ግን ሁሌም በሚያዘወትረው ደብረ ዘይት አዳሩን አደረገ:: በሚቀጥለው ጠዋት ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ በጉጉት ከሚጠብቀው ሕዝብ ጋር ተገናኘ:: ይህ የተቀደሰ ጉባኤ የሚባለው የበዓሉ ስምንተኛው ቀን ነው የሚሆነው::

የተማሩት የሃይማኖት መሪዎች (ፈሪሳውያንና ጸሐፍትን የመሳሰሉት) ኢየሱስን አጣብቂኝ ውስጥ የሚከት ጥያቄ አቀረቡ:: አንድ

ነገር ስታደርግ የተያዘች ሴት ቀርባለች:: በእነዚያ ነፍሰ ገዳዮች መካከል ስትቆም ልቧ በሐይል ይመታ ነበር፣ መዳፎቿ በላቧ ረጥበዋል:: ከዚያ ሁኔታ በሕይወት እተርፋለሁ ብላ አላሰበችም:: ሁሉም የሆነው ድንገት ነበር::

ምናልባት ባለፈው ሰባት ቀን በደስታ ሲከበር የነበረው በአልና የወይን ጠጅ ለኀጢአት አነሣሥቶአት ይሆናል:: አሁን ግን በኀጢአቷ ተጋልጣ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ተገኝታለች:: የዚያ ቅዱስ ቦታ እያንዳንዱ ድንጋይ በመካከላቸው ያለውን ኀጢአት እየኮነነ ይመስላል:: የነበረው ሁኔታ ድንገት በመቋረጡ ሕዝቡ ቢናደዱም የሚሆነውን ለማየት አሰፍስፈዋል:: ሴትዮዋ ሕዝብ ፊት ተዋርዳለች፤ የወዳጇን ርዳታ እንኳ አጥታ ብቻዋን ቆማለች:: ሰውየው ግን የታል? ሲያመነዝሩ የተያዙ ከሆነ እርሱም በድንጋይ በመደብደብ ቅጣቱን ለመቀበል ለምን ሳይመጣ ቀረ? (ዘሌ 20÷10):: ግብዝነታቸው ግልጽ ነበር:: የሰውየው አለመምጣት ብቻ ሳይሆን፣ አመንዝራነቱ በተፈጸመበት ቦታ ፈሪሳዊ መገኘቱ ራሱም በፍጹም ከሐቁ ጋር የማይጣጣም ነበር:: አስቀድሞ የተዘጋጀ ወጥመድ ካልነበረ ሴትየዋ እንዴት በማመንዘር ላይ እያለች ልትያዝ ቻለች? እነርሱ ግን ለኀጢአትም ሆነ ለሴትየዋ ደንታ አልነበራቸውም:: ሴትየዋ፣ ኢየሱስን ለማጥመድ ከመሣሪያነት ያለፈ አይደለችም::

ኢየሱስን አጣብቂኝ ውስጥ ከተቱት:: «አንተስ ምን ትላለህ?» በማለት አጠንክረው ነበር የጠየቁት:: ሴትየዋ ላይ ቢፈርድ፣ የሞትን ቅጣት በመፈጸም የሮምን ተቃውሞ መቀስቀሱ ነው:: በከፊልም ቢሆን ርኅራኄውን በማየት በተከተሉትም ፊት እምነት ሲያጣ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ለሴትዮዋ ምሕረት ቢያደርግ፣ ያመነዘረ በድንጋይ ተደብድቦ ይገደል የሚለውን የሙሴን ሕግ በማፍረስ ሊወነጀል ነው (ዘዳ 22÷22-24):: ኢየሱስ ግን በወጥመዱ አይያዝላቸውም (ከማቴ 22÷15-40



ጋር ያነ):: እንዲህ ያለው ግብዝነት እንደ ተሸፋፈነ እንዲቀር አይፈቅድም::

6ይህን ጥያቄ ያቀረቡለት፣ እርሱን የሚከሱበት ምክንያት ለማግኘት ሲፈትኑት ነው:: **ዮሐ 8÷6-11**

ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ይጽፍ ጀመር:: 7በጥያቄ
ሲወተውቱት ቀና ብሎ፣ «ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ
ይወርውርባት» አላቸው:: 8እንደ ገናም ጐንበስ ብሎ በምድር ላይ ጻፈ::
9ይህን እንደ ሰሙ፣ ከሽማግሌዎች ጀምሮ አንድ በአንድ ወጡ፤ ሴትዮዋም
እዚያው ፊቱ እንደ ቆመች ኢየሱስ ብቻውን ቀረ:: 10ኢየሱስም ቀና ብሎ፣ «አንቺ
ሴት፣ ሰዎቹ የት ሄዱ? የፈረደብሽ የለምን?» አላት::
11እርሷም፣ «ጌታ ሆይ፣ አንድም የለም» አለች::
ኢየሱስም፣ «እኔም አልፈርድብሽም፤ በይ ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት
አትሥሪ» አላት::

ኢየሱስ ለጥያቄው ትኩረት ያልሰጠ በሚመስል ሁኔታ ጐንበስ ብሎ በጣቱ መሬት ላይ ይጽፍ ጀመር:: የጻፈው ምን እንደ ነበር ብዙ የግምት ሐሳቦች ቀርበዋል:: አንዱ ይበልጥ አሳማኝ የሚመስለው ሐሳብ የጻፈው የመማክርቱን የተለያዩ ክሶች እንደ ነበር ይገልጻል:: ሌላው ደግሞ የስሞችን ዝርዝር ነበር የጻፈው ይላል:: ሌላውም ለሁኔታው ትኩረት አለመስጠቱን ለማሳየት ያደረገው ነው ይላል:: የጻፈው ምን እንደ ነበር ለማየት እንጓጓለን:: ሆኖም፣ ይህን ማወቁ ያን ያህል አስፈላጊ አይደለም:: ዋናው ነገር መጻፉ እንጂ፣ የተጻፈው ምን መሆኑ አይደለም:: ኢየሱስ መሬት ላይ እየጻፈ እያለ፣ መልስ እንዲሰጣቸው ይወተውቱት ነበር:: ከጠበቁት በላይ የሆነ ግን ምላሽ አገኙ::

ኢየሱስ ቀና አለ፤ መልሱ ኀይል ያለበት ነበር:: ሙሴንም ሆነ ያቺን ክቡር ፍጡር በማያናንቅ ሁኔታ፣ «ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት» አለ:: ኢየሱስ ከሳሾቿ ምንም

ኀጢአት የሌለባቸው መሆን አለባቸው ማለቱ አልነበረም:: ይህ ሕጋዊ አሠራርን ይጻረራል:: ብቁ ምስክር መሆን እንዳለባቸው መናገሩ ነበር::[13] በዘዳግም 19፥16-19 መሠረት (ከዘፀ 23፥1-3፣6-8 ጋር ያነ) መሰሪና አሳሳች መሆን የለባቸውም::

ኢየሱስ ሴራቸውን አጋለጠ:: ማጥቃት የፈለጉት ኢየሱስን እንጂ፣ ሴትዮዋን አልነበረም:: አሁን፣ ከሴትዮዋ ጋር እነርሱም በክፉ ተግባር ተይዘዋል:: በተጨማሪም በአይሁድ ሕግ መሠረት የመጀመሪያውን ድንጋይ መወርወር የነበረባቸው፣ የወንጀሉ ምስክሮች መሆን ነበረባቸው:: ሰዎቹ በወጥመድ የተያዘ ያህል ሆነዋል:: የተለፈገውም ይኸው ነበር! በአንድ ዐረፍት ነገር ኢየሱስ አጋለጣቸው፤ ነቀፋቸው፤ መሰሪ ሥራቸውንም አፈረሰ:: ከዚያ በኋላ ጐንበስ ብሎ መሬት ላይ ይጽፍ ጀመር::

መጀመሪያ ላይ ሽማግሌዎቹ ሄዱ፤ በጊዜ ሂደት ያካበቱት ጥበብና ቁጥብነት አብሯቸው ነበር:: ሌሎቹ እያመነቱ ተከተሉ:: እነዚያ ከሳሾች አንድ አንድ እያሉ ሴትዮዋን ከኢየሱስ ጋር መሐል ላይ [ግሪክ = *en meso ousa*] ትተው ተበተኑ:: በምን መካከል ላይ ነበር ትተዋት የሄዱት? በእነዚህ ሰዎች ጣልቃ መግባት ተቋርጦ የነበረው የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ስብስብ መካከል ነበር::

የሴትዮዋ ከሳሾች ሁሉ ሄዱ:: ኢየሱስ ብቻ ቀረ:: ይሁን እንጂ፣ አንድ ምስክር ብቻ የሞት ቅጣት እንዲፈጸም በቂ አይሆንም::[14] ኢየሱስም ቢሆን ሊፈርድባት አልፈለገ (ሮሜ 8፥31-34):: በጨዋነትና

[13] C.P. Baylis, "The Woman Caught in Adultery: A Test of Jesus as the Greater Prophet," *BibSac* 146 (1989): 171-184.

[14] S.A. James, "The Adulteress and the Death Penalty" *JETS* 22/1 (1979): 45-53 እንደምንመለከተው ምንባቡ የሞት ቅጣት እንዳይኖር ምክንያት ሊሆን አይችልም የሚል ተገቢ ድምድሜ አቅርቧል:: በአይሁድ ፍርድ አፈጻጸም መሠረት ፈሪሳውያን ሕጋዊነት የሌላቸው ምስክሮች ናቸው:: ኢየሱስም ብቸኛ ምስክር እንደ መሆኑ መጠን የሞት ቅጣት ለማስፈጸም አይበቃም::



በአክብሮት ነበር ያነጋገራት (ከዮሐ 2፥4፤ 20፥13 ጋር ያነ):: ይቅር ተብላለች፤ ነጻ ሆናለች:: የክርስቶስ ይቅር ባይነት በነጻ የሚገኝ ቢሆንም፣ ርካሽ ነው ማለት አይደለም:: ከጸጋ ጋር እግዚአብሔርን የመምሰል ኀላፊነት ተኳቷል:: ኢየሱስ ከእንግዲህ በንጽሕና እንድትኖር በማሳሰብ አሰናበታት:: ይህ ታሪክ እውነት እንዳልሆነ ቢታሰብም እንኳ፣ ቢያንስ ለተሰበሩ ሰዎች ጌታ ያለውን ባሕርይና ውበት የተላበሰ ፍቅር ያንጸባርቃል::

**§ 98**
**እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ**
**(ዮሐ 8፥12-20)**

በዮሐንስ 8 ኢየሱስ እየሰበከ በመቅደስ ሲመላለስ እንመለከታለን:: መልእክቱ የምዕራፍ 7 ንግግሩ ቀጣይ ነበር:: መጀመሪያ፣ ዐሥራ ሦስት የመለኮት ቅርጽ ያላቸው ሳህኖች መደዳውን ግድግዳ ላይ ባለቡት የሴቶች አደባባይ እንደ ነበር እናያለን:: ከግድግዳው ወዲያ ደግሞ የመማክርቱ መሰብሰቢያ ክፍል ነበር:: ይህ አደባባይ ለፈሪሳውያን የተያዘ ነበር:: ደቀ መዛሙርቶቻቸውን የሚስተምሩት እዚህ ነበር:: ኢየሱስ የእነርሱን ቦታ ያዘ:: ሆኖም መማክርቱ በአካባቢው ቢኖሩም ማንም አልከለከለውም:: እንደዚያ ማድረግ ፈልገዋል፤ ሆኖም ጊዜው ገና አልደረሰም (ከዮሐ 2፥4፤ 7፥6፣30፤ 12፥23፣27፤ 17፥1 ጋር ያነ):: ኢየሱስ ከዚያ በመነሣት ወደ ቤተ መቅደሱ በረንዳ ሄደ:: ከመቅደሱ ውጪ ሰዎች ጥያቄ ለማቅረብና ውይይት ለማድረግ ነጻ ይሆናሉ:: ይሁን እንጂ፣ የነገራቸውን ብዙ አልወደዱለትም:: እንዲያውም ከግንባታው ቦታ ድንጋዮች አንሥተው ሊገድሉት ፈለጉ (ዮሐ 8፥59)::

**ዮሐ 8፥12-20**

[12]ኢየሱስ እንደ ገና ለሰዎቹ፣ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም» አላቸው::

13ፈሪሳውያንም፣ «አንተ ስለ ራስህ ስለምትመሰክር ምስክርነትህ ተቀባይነት
የለውም» አሉት፡፡
14ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ከየት እንደ
መጣሁና ወዴት እንደምሄድ ስለማውቅ ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከየት
እንደ መጣሁ ወይም ወዴት እንደምሄድ የምታውቁት ነገር የለም፡፡ 15እናንተ እንደ
ሰው አስተሳሰብ ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በማንም አልፈርድም፤ 16ብፈርድም፣ ከላከኝ ከአብ
ጋር እንጂ ብቻዬን ስላልሆንሁ ፍርዴ ትክክል ነው፡፡
17የሁለት ሰዎች ምስክርነት ተቀባይነት እንዳለው በሕጋችሁ ተጽፎአል፡፡ 18ስለ
ራሴ የምመሰክር አንዱ እኔ ነኝ፤ ሌላውም ምስክሬ የላከኝ አብ ነው፡፡
19ከዚያም፣ «አባትህ የት ነው?» አሉት፡፡
ኢየሱስም፣ «አባቴንም እኔንም አታውቁም፤ እኔን
ብታውቁኝ ኖሮ፣ አባቴንም ባወቃችሁ ነበር» ሲል
መለሰላቸው፡፡ ኢየሱስ ይህን የተናገረው በቤተ መቅደሱ
ግቢ፣ በግምጃ ቤት አጠገብ ሲያስተምር ነበር፤ ይሁን
እንጂ ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም አልያዘውም፡፡

ይህ ሁለተኛው የኢየሱስ፣ «እኔ ነኝ» ዐረፍተ ነገር ነው (ከዮሐ 6÷35፤ 8÷12፤ 10÷7፣9፣11፣14፤ 11÷25፤ 14÷6፤ 15÷1፣5 ጋር ያነ)፡፡ ምናልባትም ይበልጥ ጥልቀት ያለው ነው፡፡ ብርሃን ማንኛውንም ነገር ስለሚገልጥ እውነትን፣ ከባሕርዩ የተነሣ ደግሞ ንጽሕናን ይወክላል፡፡ በአዲስ ኪዳን እነዚህ ሁለት የብርሃን ባሕርያት በሚከተሉት አማካይነት በሰውኛ ቀርበዋል፤ (1) እግዚአብሔርን (1ጢሞ 6÷16፤ 1ዮሐ 1÷5)፡፡ (2) የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነው ኢየሱስን፣ (ማቴ 4÷16፤ [ኢሳ 9÷1-2]፤ ሉቃ 2÷32፤ ዮሐ 1÷4-5፣9፤ 3÷19፤ 8÷12፤ 9÷5፤ 12÷36፣46-47)፡፡ (3) የኢየሱስ መልእክተኞች የሆኑ ክርስቲያኖችን፣ (ማቴ 5÷14፤ ሉቃ 16÷8፤ ዮሐ 12÷36፤ 1ተሰ 5÷5)፡፡ (4) ክርስቲያኖች የሚያውጁት ወንጌልን፣ (ሐሥ 26÷23፤ 2ቆሮ 4÷4፤ ቲቶ 1÷3፤ 2ጴጥ



1÷19)፡፡ በብርሃንና በጨለማ መካከል ከባድ ውጊያ አለ (ዮሐ 1÷5፤ 3÷19-21፤ 12÷35፤ ሐሥ 26÷18፤ ሮሜ 13÷12፤ 2ቆሮ 6÷14፤ ኤፌ 5÷8፤ 1ተሰ 5÷5፤ 1ጴጥ 2÷9፤ 1ዮሐ 2÷9)፡፡ ስለሚገልጠውና በዚህም ምክንያት በክፉ ሥራው ስለሚፈርድበት ጨለማ ብርሃንን ይጠላል (ዮሐ 3÷19-21፤ 1ቆሮ 3÷13፤ 4÷5፤ ኤፌ 5÷13-14)፡፡ በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለው ይህ ትንንቅ (ለምሳሌ፣ በእግዚአብሔርና በሰይጣን) መንግሥቱ ሲገለጥ ያከትማል (ቈላ 1÷12፤ 1ዮሐ 2÷8)፡፡ በመጨረሻው፣ ስለ «ብርሃን» የሚያወሳው ነገረ መለኮት ጌታ ኢየሱስ ብርሃን በሚሆንላት በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም በአካል ይገለጣል (ራእ 21÷23-24፤ 22÷5)፡፡

ሻማዎቹ የሚበሩበት መቅረዝ በዳስ በዓል አከባበር ሁነኛ ስፍራ አለው፡፡ ብርሃኑ ኢየሱስ እያስተማረ ወደ ነበረበት የሴቶች አደባባይ ያበራ ነበር፡፡ ምናልባትም ይህ ንግግሩ በዳሱ ውስጥ ከነበረው የእግዚአብሔር ብርሃን ጋር የተያያዘ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ «በብርሃን» ምሳሌነት ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር መሲሐዊ አንድምታ እንደ ነበረው ከፈሪሳውያን የተሰወረ አልነበረም፡፡ በዚህ የድፍረት ንግግሩም ፊት ለፊት ተቃውመውታል፡፡ እንደ ገና በዚያ ቦታ ስለ ራሱ የሚናገር ፊር የለቀቀ ሰው እንደሆነ ከሰሱት፡፡ ምስክር መሆንን በተመለከተ የሙሴ ሕግ ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ምስክሮች ሊኖሩ እንደሚገባ ያዛል፡፡ ምስክሩ ማን እንደ ሆነ ኢየሱስ ሁለቴ ተናግሮ ነበር (ዮሐ 5÷30-47፤ 7÷16-19)፡፡ እዚህ ላይ ያንን ማንሣት አላስፈለገውም፡፡

ቍጥር 14 ላይ ኢየሱስ ራሱን እየተቃረነ ይመስላል (ከዮሐ 5÷31 እና ማስታወሻው ጋር ያነ)፡፡ ይሁን እንጂ ፈሪሳውያን ኢየሱስ ያቀረበው ምስክሮችን ችላ እስካሉ ወይም መቀበል እስካልፈገሉ ድረስ የራሱን ምስክርነት ከማረጋገጥ ሌላ ምን ማድረግ ይችላል? በእግርጥም፣ ስለ ሰማያዊ መገኛው (ቍ 14)፣ ከአብ ጋር ስላለው ኅብረት (ቍ 15-16)

እና እርሱ በሚለውና እግዚአብሔር በሚለው መካከል ያለውን መጣጣም በተመለከተ መመስከር የሚችል እርሱ ብቻ ነው (ቊ 17-18)። ኢየሱስ የተናገረውን እውነት ማረጋገጥ የሚችል ወደ ሰማይ ሄዶ የተመለሰ ማንም የለም። ዮሐንስና ሙሴ ኢየሱስን በተመለከተ መለኮታዊ መገለጥ ተቀብለዋል፤ ፈሪሳውያን ግን ምስክርነታቸውን መቀበል አልፈለጉም። ተአምራቱ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኀይልን ያመለክታሉ፤ ፈሪሳውያን ግን ከአጋንንታዊ አሠራር ጋር አመሳስለዋቸዋል። የቀሩ ምስክሮች ኢየሱስና እግዚአብሔር አብ ብቻ ናቸው። ፈሪሳውያን ኢየሱስን ላለመስማት ጽኑ ውሳኔ አድርገዋል። እግዚአብሔርን ስለማያውቁ ምስክርነቱንም መቀበል የሚችሉበት መንገድ አልነበራቸውም። የሚያሳዝነው፣ ወደ አብ የሚያደርስ መንገድ ኢየሱስ ብቻ ቢሆንም፣ እርሱንም ቢሆን መቀበል አለመፈለጋቸው። በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ሆነው ከዚያ የሚያወጣቸውን ድልድይ ቆርጠዋል።

የቀረላቸው ነገር ቢኖር ፍርድና ሞት ብቻ ነበር። ኢየሱስ የመጣው ዓለምን ለማዳን እንጂ፣ በዓለም ላይ ለመፍረድ አልነበረም (ዮሐ 3÷16-17)። ይሁን እንጂ፣ የድነትን ወንጌል ሲሰብክ፣ እነማን እንደሚድኑና እነማን እንደማይድኑ መስፈርት አስቀምጧል (ዮሐ 5÷24)። ትስጉት በምንለው በዚህ አጭር የጊዜ ቅጽበት፣ የሚፈርደው የሰው ልጅ ሳይሆን የተናገራቸው ቃላት ናቸው። ወደ ፊት ግን ኢየሱስ በዚህ ዓለምና የእግዚአብሔርን መልእክተኛ መቀበል ባልፈለጉ ክፉ ሰዎች ሁሉ ላይ ይፈርዳል (ዮሐ 5÷26-30)።

**§ 99ሀ**
**ወደ አባቴ እመለሳለሁ**
**(ዮሐ 8÷21-30)**

21ኢየሱስም እንደ ገና፣ «እኔ እሄዳለሁ፤ እናንተም
ትፈልጉኛላችሁ፤ በኀጢአታችሁም ትሞታላችሁ፤ እኔ
ወደምሄድበት ግን ልትመጡ አትችሉም» አላቸው።
22አይሁድም፣ «'እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ
አትችሉም' ያለው ራሱን ሊገድል ይሆን?» አሉ። 23እርሱ
ግን እንዲህ አላቸው፤ «እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም
ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም። 24በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአችኋለሁ፤
እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ፣ እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ
ትሞታላችሁና።»
25እነርሱም፣ «ለመሆኑ፣ አንተ ማን ነህ?»
አሉት። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እስካሁን
የነገርኋችሁ እኔ እርሱ ነኝ፤ 26በእናንተ ላይ ብዙ
የምናገረውና ብዙ የምፈርደው ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን
የላከኝ ታማኝ ነው፤ ከእርሱም የሰማሁትን ለዓለም
እናገራለሁ።»

ቀደም ባለው ጊዜ ኢየሱስ እንደሚሄድ ሲናገር፣ አይሁድ ወደ ተበተኑት ወገኖቻቸው እንደሚሄድ አስበው ነበር (7÷33-36)። አሁን ግን በስላቃዊ መልኩ ምናልባት ራሱን ይገድል እንደ ሆነ አሰቡ። እርግጥ ነው፣ ኢየሱስን ወደ ሞት አይከተሉትም። ኢየሱስ፣ «በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁ» ሲላቸው፣ «አይደለም፣ ይልቁንም አንተ ራስህን ልትገድል ነው!» የሚል መልስ ሰጡት። በሚገርም ሁኔታ ከእውነቱ ብዙም አልራቁም። ኢየሱስ በገዛ ራሱ ፈቃድ ሕይወቱን ለኀጢአታችን ቤዛ ሊሰጥ ነው (ዮሐ 10÷18፤ ማቴ 20÷28)።

ኢየሱስን ቢፈልጉት እንኳ የማያገኙት እንዴት ሊሆን ይችላል? የተለያዩ ግምቶች ይኖራሉ። ሔንድሪክሰን ሊሞቱ በተቃረቡበት ሰዓት ላይ ኢየሱስን ቢፈልጉትም፣ ጊዜው ስለሚያልፍ በኀጢአታቸው ይሞታሉ በማለት ያስባል። ምናልባት በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጣውን ፍርድ (በ70 ዓ.ም.) ያመለክት ይሆናል። ከተማዋን እንዲታደግ (ማቴ 24÷4-5፣ 23-26) መሲሓቸውን ይፈልጋሉ፤ ሆኖም በዚያ ጊዜ እርሱ መጥቶ ሄዶአልና አያገኙትም። ምናልባትም ራሳቸው የሳሉትን መሲሕ ይፈልጋሉ፤ ሆኖም እውነተኛው መሲሕ ኢየሱስ ተንቆ ተሠውቷልና

አያገኙትም:: ምናልባትም ሌላው አስፈሪ አማራጭ፣ በንስሐ ለመመለስ የነበራቸው ዕድል አምልጧቸዋል ማለት ይሆናል:: አሕዛብ ወንጌልን ለመቀበል የተሟላ ዕድል እስኪያገኙ ድረስ፣ እንደ ሕዝብ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልብ አደንድኗል (ሮሜ 11÷25):: ስለሆነም፣ አሁን ኢየሱስን ያልተቀበሉ የመቀበሉ ዕድል ያመልጣቸዋል (ከዮሐ 8÷43፤ ማቴ 13÷13-15፤ ሐሥ 28÷25-28፤ ዕብ 6÷6፤ ኢሳ 55÷6 ጋር ያነ)::

ኢየሱስን የማያገኙት ራሱን ስለሚያጠፋ እንደ ሆነ ሕዝቡ ተናግረዋል:: ኢየሱስ ግን፣ «ራስን ማጥፋት ከዚህ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም:: በሁለት የተለያዩ ዓለሞች ውስጥ ስለሆንን አታገኙኝም» አላቸው:: ምንም እንኳ ኢየሱስ ከራሱ ዓለም ወዳለንበት ዓለም፣ ያም ወደ ምድር ቢመጣም አይሁድ ግን ሐሳባቸውን ወደ እግዚአብሔር ሐሳብ ከፍ ከማድረግ ይልቅ በምድራዊ አእምሮ በማሰባቸው ዋናውን ነገር ስተዋል:: በኢየሱስ በአካል ወደዚህ ምድር መምጣት በኩል ካልሆነ በቀር እግዚአብሔርን አናውቅም ነበር:: አስተሳሰባችን ሰማያዊ ነገሮች ላይ ካልሆነ በቀር እግዚአብሔርን ማወቅ አንችልም:: መለኮታዊ አስተሳሰብ እንዲኖር የአምላክ በሰው አካል መገለጥና የሰው አእምሮ መታደስን ይጠይቃል::

የቃላት ስንጠቃ ጊዜ አልፏል:: ኢየሱስ የሚቻለውን ያህል ግልጽ ሆኗል፤ «መሲሕ መሆኑን አመኑ፤ አለበለዚያ ወደ ገሃነም ትሄዳላችሁ» (ከ3:36 ጋር ያነ):: እነርሱም ጠንከር አድርገው፣ «ለመሆኑ አንተ ማን ነህ?» [*su tis ei*] በማለት ጠየቁ:: ምናልባም እንደ ወፊፌ ቴፐረውት ይሆናል፤ ምናልባት በእነዚያ ጠንካራ ቃላት ቀዝቀዝ ብለው ይሆናል:: እንደምንመለከተው በሕዝቡ ዘንድ የተደበላለቀ ዐይነት ስሜት ነበር (ዮሐ 8÷30-31):: ሆኖም ጥያቄያቸው በሚገባ አለማድመጣቸውን አጋልጧል:: እርሱ ስለ መሆኑ ግን ላለፉት ሁለት ቀኖች በመቅደስ ሲያስተምር ነበር:: አሁን ወደዚያ አይመለስም:: ምንም እንኳ ሥልጣኑም



ተፈላጊውም ነገር ቢኖረውም፣ ፍርድ እንደሚያመጣ ሙግት ውስጥ መግባት አልፈለገም:: ያን ለአባቱና ትምህርቶቹ ላቀረቡት ምክንያታዊ እውነት ትቷል:: እነዚያ አይሁድን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ለመኰነን በቂ ናቸው (ቍ 26)::

ዮሐ 8÷27-30

27እነርሱም ስለ አብ እየነገራቸው እንደ ነበር
አላስተዋሉም:: 28ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «የሰው
ልጅን ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ፣ ያ ያልሁት እርሱ እኔ
እንደ ሆንሁና ለብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣ በራሴም ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ
ታውቃላችሁ፤ 29የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው፤ ምንጊዜም የሚያስደስተውን ስለማደርግ
ብቻዬን አልተወኝም::» 30ይህንንም እንደ ተናገረ ብዙዎች በእርሱ አመኑ::

ኢየሱስ የተናገረው ለማያምኑት ሰዎች እንደ ገና እንቈቅልሽ ሆነባቸው:: ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ከመስጠት ይልቅ ግራ የሚያጋባ ነገር ጨመረባቸው:: ኢየሱስ የሚያስተምረው ለደቀ መዛሙርት እንጂ ነገርን ለማብራራት እንዳልሆነ እንደ ገና እንመለከታለን (ከማቴ 13÷10-17 ጋር ያነ):: ኢየሱስ ተማሪዎቹ ላለማመን ራሳቸውን እስካመቻቹ ድረስ፣ ይበልጥ ግራ እንዲጋቡ ከማድረግ የሚመልሰው አንዳችም የሕሊና ወቀሳ አልነበረም:: ወደ ማመን ያዘነበሉ ግን ወደ እርሱ ይጠጋሉ::

እንደ 3÷14 ሁሉ፣ «ከፍ ከፍ ማለቱ» የሚጀምረው ከመስቀሉ ነው (ከ12÷32 ጋር ያነ):: እነዚያ አይሁድ ኢየሱስ ማን መሆኑን እንዴት በፍጥነት ማወቅ ይችላሉ? መቼም፣ በጐልጐታ ብዙዎች የሚያምኑበት ሁኔታ አይኖርም:: ስቅለቱ አብዛኞቹን አይሁዶች ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አያሳምናቸውም:: ይሁን እንጂ፣ «ከፍ ከፍ» የማለቱ አካል በሆኑት በትንሣኤውና በዕርገቱ ግን የተቀሩት እስራኤላውያን ይድናሉ:: በበዓለ ሃምሳ ቀን ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት

ሲሰብክ፣ «ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?» የሚል ጥያቄ ያቀረቡትን ማሰባችንም አይቀርም።

በተጨማሪም፣ ኢየሱስ መስቀል ላይ ለመሞት ራሱን መስጠቱ የኋላ ኋላ ለእግዚአብሔር መታዘዙንና ከእርሱም ጋር ያለውን ኅብረት ያረጋግጣል። ይህ ማረጋገጫ ወደ ፊት ፍሬ ማፍራት ብቻ ሳይሆን፣ ብዙዎች በእርሱ እንዲታመኑ ያደርጋል። ይህ፣ «እምነት» - «የሚያድን» እምነት (ከዮሐ 2፥23፤ 12፥42 ጋር ያነ) ባይሆን እንኳ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የሚያመራ እርምጃ ይሆናል።

**99ለ**
**አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ**
**(ዮሐ 8፥31-59)**

[31]ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ እንዲህ
አላቸው፤ «በትምህርቴ ብትጸኑ እናንተ በእውነት ደቀ
መዛሙርቴ ናችሁ፤ [32]እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም
ነጻ ያወጣችኋል።
[33]እነርሱም መለሰው፣ «እኛ የአብርሃም ልጆች
ነን፤ ለማንም ባሪያዎች ሆነን አናውቅም፤ ታዲያ፣ 'ነጻ
ትወጣላችሁ' እንዴት ትለናለህ?» አሉት። [34]ኢየሱስም
እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት የሚያደርግ የኀጢአት ባሪያ
ነው፤ [35]ባሪያ ለዘለቄታ በቤተ ሰቡ ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን ምንጊዜም በቤት
ይኖራል። [36]እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ።

ኢየሱስ ይህን ሲል በሁለቱ መካከል ጥቂት ወይም ምንም ልዩነት ሳያደርግ ለሚያምኑትና ለማያምኑት ጭምር ነበር። ምክንያቱም አድማጮቹ በመከፋፈላቸው ነበር። አንዳንዶቹ ሊገድሉት ወስነዋል፤ ሌሎች ደግሞ በእርሱ ማመን ጀምረዋል። ይሁን እንጂ «ያምናሉ» የተባሉት እንኳ በእምነትና በጥርጥር መሓል እየዋዠቁ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በእምነት ገና «ሕፃናት» ነበሩ፤ ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረውም በጣም ከባድ ነበር።



ኢየሱስ ጨቅላ እምነታቸውን እየመገበ እያለ የእርሱ ደቀ መዝሙር መሆን የሚያስከትለውን ኀላፊነትና መብት አስቀመጠላቸው። ኀላፊነታቸው ትምህርቱን አጥብቀው መያዛቸው (መታዘዛቸው) ነው። በአንደበት ብቻ ማውራት ሳይሆን፣ በቅርብ በሚነሣው ተቃውሞ ውስጥ እንኳ እርሱን በማመን መመላለስ አለባቸው። መብታቸው ደግሞ ነጻነታቸው ነው። ይህ ማድረግ ያለባቸውን ለማድረግ የሚስችላቸው ኀይልና ፈቃድ እንጂ የሚወዱትን የማድረግ ነጻነት አይደለም።

ሕዝቡ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድም እንኳ ቢሆን ባሪያ መባላቸውን ተቃውመዋል። ሙሉ መብት ያለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸው። የአብርሃም ልጆች ናቸው! እንደ እውነቱ ከሆነ የግብፅ፣ የባቢሎን፣ የሶሪያ፣ አሁን ደግሞ የሮም ባሪያዎች መሆናቸውን መዘንጋት አልነበረባቸውም። ብዙ አይሁዶችም ማኅበረ ሰባዊ ባርያዎች መሆናቸውንም መካድ አይችሉም። እርግጥ ነው የሙሴ ሕግ አይሁዳዊ አይሁዳዊን ለጊዜው በባርነት እንዲያሳድረው ደንግጎአል። እነርሱ መናገር የፈለጉት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የማንም ባሪያዎች እንዳልሆኑና ሆነውም እንደማያውቁ ነበር። በዙሪያቸው ያሉ አረማውያን ለሚያመልኳቸው ብዙ አማልክት ተገዝተው አያውቁም። በጣዖት አምልኮ ውስጥ ላለው ጽልመታዊ የአጋንንት አስተምህሮ እስረኞች ሆነው አያውቁም። አንዱን አምላክ ያሕዌን ብቻ ነበር የሚያመልኩት። ስለዚህም የቱንም ያህል መንፈሳዊ ነጻነት እንደማያስፈልጋቸው ያስባሉ።

ቤት ውስጥ መኖር ልጅ እንደማያደርግ ሁሉ፣ ትክክለኛ ሃይማኖትንም መያዝ ነጻ እንደማያደርግ ኢየሱስ ግልጽ አደረገላቸው። እርግጥ ነው፤ ትክክለኛውን ሃይማኖት ይዘዋል፤ ትክክለኛ ሕይወት ግን አልነበራቸውም። ኀጢአተኞች ናቸው (በአሁን ጊዜ መጠቀሙ በኀጢአት ሕይወት እየቀጠሉ መሆናቸውን ያመለክታል፤ ከ1ዮሐ 3፥4 ጋር ያነ)። ኀጢአት የሚያደርግ ሁሉ ባርያ ነው (ሮሜ 6፥16፤ 11፥32፤ 2ጴጥ 2፥19)። ቍጥር 36 «የነጻነት ዐዋጃችን» ነው (2ቆሮ 3፥17፤ ገላ 4፥6-

7):: እንደ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ባሪያዎቹን ነጻ የማውጣትና በቤተ ሰቡ ውስጥ እንደ ልጆች የመቀበል ሕጋዊ መብት አለው:: በክርስቶስ ያለን ነጻነት፤ ከኀጢአት ነጻ መሆናችን ነው:: (1) ከሚያስከትለው ቅጣት - ዕዳችን ተደምስሶአል (ኢሳ 53÷5)፤ (2) ከተግባሩ - ኀጢአት የማድረግን ልማድ እናሸንፋለን፤ (3) ከኀይሉ - እናደርጋቸው የነበሩ ነገሮችን እንዳንፈልግ አዲስ ልብ ተሰጥቶናል::

በተጨማሪም፣ በክርስቶስ ከሰዎችም ፍርድ ነጻ ሆነናል (ሮሜ 14÷4):: ከበደለኛነት ስሜት (ሮሜ 8÷1-2)፣ እንዲሁም ከዚህ ዓለም ፍልስፍናና ተፅዕኖ (ዮሐ 3÷8):: ስለ ቁሳዊ ነገሮች ከመጨነቅ ነጻ ነን (ማቴ 6÷25-34)፤ ከፍርድ ፍርሃት ነጻ ነን (1ዮሐ 4÷18)፤ ከራሳችንና ከከንቱ ምኞታችን ነጻ ነን (ገላ 2÷20)፤ ከሞት ነጻ ነን (ሮሜ 6÷5-6):: ኢየሱስ ነጻ ካወጣን፣ በእርግጥም ነጻ ነን!

**ዮሐ 8÷37-41**

37የአብርሃም ልጆች መሆናችሁን ዐውቃለሁ፤
ነገር ግን ቃሌን ስለማትቀበሉ ልትገድሉኝ ቈርጣችሁ
ተነሥታችኋል:: 38እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤
እናንተም ከአባታችሁ የሰማችሁትን ታደርጋላችሁ::
39እነርሱም፣ «አባታችንስ አብርሃም ነው» ብለው መለሱለት:: ኢየሱስም
እንዲህ አላቸው፤ «የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ አብርሃም የሠራውን ትሠሩ ነበር::
40ከእግዚአብሔር ሰምቼ እውነቱን የነገርኋችሁን እኔን ለመግደል ቈርጣችሁ
ተነሥታችኋል፤ አብርሃም ግን እንዲህ አላደረገም:: 41እናንተ የምታደርጉት አባታችሁ
የሚያደርገውን ነው::»

እነርሱም፣ «እኛስ በዝሙት የተወለድን አይደለንም፤ አባታችንም አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው» ሲሉ መለሱለት::

በአይሁድ ነገረ መለኮት መሠረት የአብርሃም ልጅ መሆን አያሌ በረከቶችን ያስገኛል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳናዊ ግንኙነት፣ በመሲሐዊ ግብዣ መሳተፍ፣ እንዲሁም ለእውነተኛው የእግዚአብሔር ሥርዐት



መታመን (ከሮሜ 3÷1-2፤ 9÷4-5 እና ሌሎችም ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ፣ የአብርሃም ዘሮች በመሆንና (ቍ 37) የእርሱ ልጆች (ቍ 39) በመሆን መካከል ልዩነት አለ:: የአብርሃም ዘር መሆን በውልደት ከእርሱ መወለድን ያሳያል:: የእርሱ ልጅ መሆን እንደ እርሱ መኖርን ያመለክታል (ሮሜ 2÷28-29፤ 4÷12-13፣16፣18፤ 9÷7-8፤ ገላ 3÷6-9፣14፣29፤ 4÷22-28፤ ራእ 2÷9፤ 3÷9):: ኢየሱስ፣ አይሁድነታቸውን እንጂ የዘር ሐረጋቸውን አልካደም:: እንደ አይሁድ እየኖሩ አይደለም ማለት ደግሞ ከባድ ነቀፋ ነው:: ኢየሱስ እንደ አይሁድ ማንነታቸውን አዋርዶታል:: ሙሴን (7÷19-23)፣ ኤልያስን ወይም ሒላልን እንኳን አላደመጣችሁም ቢል ኖሮ ይህን ያህል ከባድ አይሆንባቸውም ነበር:: ይሁን እንጂ እንደ የአይሁድ ሕዝብ አባት አብርሃም መሪዎቻቸውን፣ ተስፋዎቻቸውንና ተግባሮቻቸውን ሁሉ ይወክላል::

የኢየሱስ ክስ ጠንካራ ቢሆንም፣ የተረጋገጠ ነበር:: ኢየሱስን ለመግደል በመፈለጋቸው አብርሃም ሲናፍቀው የነበረውን ሁሉ ለማጥፋት መሞከራቸው ነበር (ዘፍ 12÷1-3፤ ገላ 3÷16-29):: የአብርሃም ሕይወትና መጠራት መሠረት የሆነውን - የመሲሑን መምጣት ተስፋ እያወደሙ ነበር:: ስለሆነም የአብርሃም ዘሮች ነን የማለት መብት የላቸውም:: ከዚያም በላይ፣ እምነት የአብርሃም ሁነኛ ባሕርይ ነበር:: እግዚአብሔር የነገረውን በመስማትና የሰማውን ተግባር ላይ በማዋል የመጣ እምነት ነበር (ከዘፍ 18÷1-8 ጋር ያነ):: የወቅቱ የኢየሱስ ታዳሚዎች የእግዚአብሔርን መልእክተኛ እየሰሙ አይደለም:: ስለሆነም የአብርሃም ዐይነተኛ ምልክት የሆነው እምነት አልነበራቸውም::

ተግባራቸው አባታቸው ሌላ መሆኑን ነበር የሚናገረው:: ነፍሰ ገዳዮች ናቸው:: የእግዚአብሔርን መልእክትና መልእክተኛ ንቀዋል:: ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔርን ሥልጣን እስከ መጋፋት እንኳ

ደፍረዋል:: እነዚህ ደግሞ ሰይጣናዊ ባሕርያት ናቸው:: ተግባራቸው ከአብርሃም ይልቅ፣ የዲያብሎስ ወገኖች መሆናቸውን ነበር የሚገልጠው:: እንዲህ ላለው ነቀፋ የሚመልሱት በቍጣ ነበር:: «እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን» በማለት ይከራከራሉ:: ይህን የሚሉት ከልባቸው ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ተሳስተዋል::

የጠፉ ኀጢአተኞች ሲሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት አለን በማለት የሚያስቡ ሁሉ እንዲሁ ናቸው (ከማቴ 7÷21-23፤ 25÷41-46 ጋር ያነ):: እንዲህ ሲባል ግን ድነታችንን በተመለከተ እርግጠኞች መሆን አንችልም ማለት አይደለም (1ዮሐ 5÷13 ጋር ያነ):: ይሁን እንጂ እርግጠኝነታችን የእግዚአብሔር መልእክተኛ በሆነው ኢየሱስ በኩል መምጣት ይኖርበታል::

መንፈሳዊ ዲቃላዎች ተብለው መጠራታቸው በጣም አስቆጥቷቸዋል:: ከዚህም የተነሣ የራሱ የኢየሱስ ልደትን በተመለከተ በረቀቀ ሁኔታ ነቀፋ ሰንዝረዋል:: ማርያምና ዮሴፍን በተመለከተ እንዲህ ያለው ክስ አዲስ አልነበረም:: ኢየሱስ አይሁድን መንፈሳዊ ዲቃላዎች በማለት የሰነዘረው ነቀፋ በሥጋዊ ሁኔታ እርሱን ራሱን ይመለከታል የሚል ወሬ እንዲስፋፋ አድርጎ ነበር::

**ዮሐ 8÷42-47**

[42]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር:: እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም:: [43]የምናገረውን ለምን አታስተውሉም? ምክንያቱም ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው:: [44]እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ:: እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት አልጸናም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት በመሆኑ ሐሰትን ሲናገር፣ የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው፤ [45]እኔ ግን እውነት ስለምናገር አታምኑኝም:: [46]ከእናንተ ስለ ኀጢአት በማስረጃ ሊከሰኝ የሚችል አለን? እውነት የምናገር ከሆነ፣ ለምን አታምኑኝም? [47]ከእግዚአብሔር የሆነ እግዚአብሔር የሚለውን ይሰማል፤ እናንተ ግን ከእግዚአብሔር ስላልሆናችሁ አትሰሙም::»



አይሁድ ሁለት የሚጋጩ ድምፆችን እየሰሙ ነበር፤ አንዱ ከእግዚአብሔር ሲሆን (በኢየሱስ በኩል) ሌላው ከሰይጣን ነው:: የሚያደምጡት በጣም የለመዱትን ድምፅ ነው:: አባታቸው የነገራቸውን ሁሉ እንደሚያደምጡ ልጆች እነዚያ አይሁድ አባታቸው ዲያብሎስን እያደመጡ ነበር:: ማድመጥ የእውነትና የምክንያታዊነት ጉዳይ ብቻ አይደለም:: የመውደድም ጉዳይ ነው (ቍ 42፤ ከ1ዮሐ 3÷10፤ 5÷1-2 ጋር ያነ):: ኢየሱስ የሚነግራቸውን ለመቀበል ፈዛዛ የሆኑት፣ የማይገባቸው ወይም የኢየሱስ ቃል ግራ የሚያጋባ ስለሆነባቸው አልነበረም:: መስማት ያልፈለጉት (ከዮሐ 8÷19፣22፣25፣27፣33 ጋር ያነ) ኢየሱስን ባለመውደዳቸው ነበር:: ኢየሱስን ያልወደዱት እግዚአብሔርን ባለመውደዳቸው ነው::

ወላጆቻቸውን መምረጥ እንደማይችሉ በተፈጥሮ እንደ ተወለዱ ልጆች ሳይሆን በተቃራኒው፣ አይሁድ እርሱ የሚያደርገውን በማድረግ የዲያብሎስ ልጆች ሆነዋል (ማቴ 13÷38፤ 23÷15፤ 1ዮሐ 3÷8፤ ራእ 12÷9):: መሠረታዊው ሐሳብ የምንሰማውን መምረጥ መቻላችን፣ አባት የሚሆነንን መምረጥ መቻላችን ነው:: ሐሰትን ለብዙ ዘመን ከመስማታችን የተነሳ እውነትን ማመን የማንችልበት ሁኔታ ላይ የምንገኝበት ጊዜ ይመጣል (ቍ 43)::

ሰይጣን ሐሰተኛ ነው (ዘፍ 3÷1፣4፤ ኢዩ 1÷9፣10፣11፤ ማቴ 4÷6፣9፤ ሐሥ 5÷3፤ 2ተሰ 2÷9፣10፣11):: ከዚያም በላይ ከፊል እውነት በመናገርና (ዘፍ 3÷4) ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጣመም የታወቀ ነው (ማቴ 4÷6):: ዓላማውን የሚያሳካው ሐሰት በመናገር ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ሐሳብ በ«ሰው» ሐሳብ በመተካት ጭምር ነው (ኢሳ 55÷6-9):: በምዕራቡ ዓለም እውነት ታሽንቆለች፤ በሚቀርበው ማስረጃ

መሠረት የኋላ ኋላ ምክንያታዊነት አሸንፎ ይወጣል በማለት እናስባለን:: ይሁን እንጂ «ሐቅ» ወይም «እውነት» የምንለው ነገር በአመዛኙ ቀደም ሲል ራሳችንን በሰጠነው ነገር ይወሰናል:: በአጭር ቋንቋ ሰይጣን የግድ መረጃ እንዳይኖረን አያደርግም:: መረጃዎችን (እውነቶችን) በዓለም ዓይን የምናይበት ሁኔታ ላይ ካስቀመጠን ሌላው ቀርቶ መስቀሉ እንኳ ሞኝነት መስሎ ሊታየን ይችላል (1ቆሮ 1፥18-25):: እነዚያ ኢየሱስን በተመለከተ ሐቁን የሚያውቁ አይሁድ እርሱን ያልተቀበሉት በዚህ ምክንያት ነበር:: ኢየሱስ ከፍልስፍናቸው ጋር ሊጣጣምላቸው አልቻለም፤ ስለሆነም፣ «ድምፅን» መቀበል አልፈለጉም::

የተሳሳተ ፍልስፍና አንዳንድ እውነቶችን መረዳት የማይችልበት ጊዜ ላይ ይመጣል:: እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርስ ማንኛውም ቅን ሰው፣ «የአስተሳሰብ መንገዱን» ይተውና ከሐቆቹ ጋር መገናዘብ የሚችል መንገድ ይይዛል:: ቁጥር 46 ከኢየሱስ ኀጢአትን ፈልገው እንዲያገኙ በመጋበዝ የተሳሳተ ፍልስፍናቸውን እንዳልነበረ ለማድረግ የታለመ ነው::[15] ይህ አደገኛ ግብዣ ነው! የፖለቲካ ቅስቀሳዎች ያስተማሩን ነገር ቢኖር፣ ማንኛውም ሰው ፍጹም አለመሆኑን ነው:: ሆኖም የኢየሱስ ከሳሾች መንቀሳቀስ አልቻሉም:: መናገር የሚችሉት አልነበራቸውም:: ምናልባትም ይህ ኢየሱስ ምንም ኀጢአት የሌለበት ለመሆኑ አሳማኝ ፍንጭ ሊሆነን ይችላል (ከ2ቆሮ 5፥21፤ ዕብ 4፥15 ጋር ያነ)::

**ዮሐ 8፥48-53**

48አይሁድም መለሰው፣ «አንተ ሳምራዊ ነህ፤ ደግሞም ጋኔን አድሮብሃል ማለታችን ትክክል አይደለምን?» አሉት::
49ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እኔስ አባቴን አከብረዋለሁ እንጂ ጋኔን አላደረብኝም፤ እናንተ ግን ታዋርዱኛላችሁ:: 50እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም፤

---

[15] «ማስረጃ» የሚለው ቃል [*elenchei*] (ቁ 46) በቂ ምክንያት በማቅረብ ማረጋገጥና ማሳመን ማለት ነው:: ክስ በማቅረብ ብቻ የማይወሰን መሆን አለበት::



የሚፈልግ ግን አለ፤ ፈራጁም እርሱ ነው:: 51እውነት እላችኋለሁ፤ ማንም ቃሌን ቢጠብቅ፣ ሞትን ፈጽሞ አያይም::»
52አይሁድም እንዲህ አሉት፤ «ጋኔን እንዳለብህ አሁን ዐወቅን፤ አብርሃም ሞተ፤ ነቢያትም እንዲሁ፤ አንተ ግን ማንም ቃልህን ቢጠብቅ ሞትን ፈጽሞ እንደማይቀምስ ትናገራለህ:: 53አንተ ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? እርሱ ሞተ፤ ነቢያቱም እንዲሁ፤ ለመሆኑ አንተ ማን ነኝ ልትል ነው?»

ሕዝቡ ለኢየሱስ ነቀፋ አጸፋውን መለሱ:: በአስተምህሮ ደረጃ ስታችኋል አላቸው:: እነርሱም የተሳሳተው የሳምራውያንን ትምህርት የተከተለው እርሱ እንደ ሆነ ተናገሩ (ዮሐ 4፥9 ይመ):: የዲያብሎስ ልጆች መሆናቸውን ተናገረ:: እነርሱም ጋኔን አድሮብሃል አሉት (ዮሐ 7፥20 ይመ):: ከዚህ የበለጠ ስድብ መለዋወጥ ሊኖር አይችልም:: ለራሱ ከመከራር ወይም መልስ ከመስጠት ይልቅ (ያን የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው፣ ቁ 50) ሕይወትን አቀረበላቸው (ቁ 51):: የመጣውም ለዚሁ ነው (ዮሐ 10፥10)::

ሕይወት እሰጣለሁ ማለት የድፍረት አነጋገር ነው:: ለመሆኑ ኢየሱስ፣ ማን ነኝ ብሎ ያስባል? ... ይህን ብቻ ማወቅ ፈልገዋል! ለእነዚያ አይሁድ በፍጹም የማይታሰብ መስሎ ቢታያቸውም፣ ኢየሱስ ከአብርሃም ይበልጣል (ከዮሐ 5፥18፤ 10፥33፤ 19፥7 ጋር ያነ):: መሲሑ ዓለምን ሁሉ የሚባርክ እንዲሆን ከተፈለገ የግድ እንደዚያ መሆን አለበት (ዘፍ 12፥3):: ምንም እንኳ ሦስቱ ታዋቂ የዓለም ሃይማኖቶች (ይሁዲ፣ ክርስትናና እስልምና) አብርሃምን መሠረት ያደረጉ ቢሆንም፣ ኢየሱስ ከአብርሃም የበለጠ በምድራችን ላይ ለውጥ እንዳመጣ ታሪክ አረጋግጧል:: የታሪክ የማኅበረሰብ ጥናት፣ የፍልስፍናና ነገረ መለኮት የማይታበል ትምህርት ኢየሱስ ከአብርሃም የበለጠ መሆኑ ማስረገጣቸው ነው:: ያ ግን እንደ እግዚአብሔር ልጅና እንደ ሥላሴ ሁለተኛ አካል ስለ ማንነቱ የሚያመለክተው የለም::

ኢየሱስን ሰምተውት ቢሆን ኖሮ፣ መሲሑ እነርሱ ከሚያስቡት የበለጠ መሆኑን ይገነዘቡ ነበር:: ከታናሹ የሰው ልጅ መንግሥት ሳይሆን ከሞት ነጻ ያወጣል (1ቆሮ 15÷54-57):: ቃሉን ለሚሰሙና ለሚታዘዙት እርሱ የሕይወትና የዘላለም ኀይል ነው (ማቴ 7÷24-27)::

ዮሐ 8÷54-59

[54]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «እኔ ራሴን ባከብር፣ ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያከብረኝ ግን እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው:: [55]እናንተ ባታውቁትም፣ እኔ ዐውቀዋለሁ፤ አላውቀውም ብል፣ እኔም እንደ እናንተው ሐሰተኛ እሆናለሁ:: እኔ ግን ዐውቀዋለሁ፤ ቃሉንም እጠብቃለሁ:: [56]አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ለማየት ተስፋ በማድረግ ተደሰተ፤ አየም፤ ሐሴትም አደረገ::

[57]አይሁድም፣ «ገና አምሳ ዓመት ያልሞላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃል!» አሉት::

[58]ኢየሱስም፣ «እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ» አላቸው:: [59]በዚህን ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው፤ ከቤተ መቅደስም ወጥቶ ሄደ::

የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጥ በድፍረት መናገር ከተራ መኩራራት ያለፈ ነው:: ኢየሱስ ያን አባባል ከመደገፍ በላይ እየሆነው ነው:: ይህን ጊዜ ብቻ ያረጋግጣል:: ለኢየሱስ መከላከል ያለበት እግዚአብሔር ብቻ ነው:: የተቀረው የአዲስ ኪዳን ክፍል ስለ ኢየሱስ ሕይወት ሰጪ ኀይልና እግዚአብሔርን ልጁን ስለ ማክበሩ የሚናገር ነው:: ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ክርክር ሳይሆን ሐቁ መነገሩን ነው የምንመለከተው::

አብርሃም የኢየሱስን ቀን በማየት ተደሰተ፤ የኢየሱስን ቀን ያየው ግን መቼ ነበር? ይህ ከሰማይ መጥቶ በሥጋ መገለጡን በማየት ደስ ተሰኘ ማለት ነውን? ወይስ ኢየሱስ የይስሐቅን መወለድ ከተናገሩት ሦስቱ ጐብኚዎች አንዱ ነበር (ዘፍ 18÷1-2)? ምናልባት ልጁ ይስሐቅ



በተወለደ ጊዜ ስለ መሲሑ የተነገረው ተስፋ መጀመሪያ ሲፈጸም በማየቱ አብርሃም ደስ ተሰኘ ማለት ሊሆን ይችላል (ዘፍ 12÷1-3):: በመጀመሪያ ደረጃ፣ የስሙ ትርጒም ራሱ፣ «ሣቅ» ማለት ነው (ዘፍ 21÷3-6):: ይህ የእግዚአብሔር ተስፋ የመጀመሪያ ፍሬ ሲሆን ከ2000 ዓመት በኋላ በዐይናቸው ፊት ገሃድ እየወጣ ነበር::

ኢየሱስን በትክክል አለመረዳታቸው ግልጽ ነው:: ለእነርሱ የመሰላቸው ኢየሱስ በአብርሃም ዘመን እንደነበረ መናገሩ ነው:: ኢየሱስ ግን 2000 ዓመቱ አልነበረም:: በሥጋ ከመጣ ገና ሃምሳ ዓመት እንኳ አልሆነውም:: የነገሩ ጭብጥ ኢየሱስ አብርሃም ሲወለድ፣ እንዲያውም ከዚያ ረጅም ጊዜ በፊት ነበር የሚለው ነው:: ኢየሱስ ከአብ ጋር ነበር፤ ከአብ ጋር ዘላለማዊ ነው (ዮሐ 1÷1-2፤ ቈላ 1÷15-17)::

ኢየሱስ ያስቀመጠውን የጊዜ ተዋረድ በትክክል ባይረዱም፣ የንግግሩን ጭብጥ ሐሳብ ግን አልሳቱም:: «ከአብርሃም በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ» ሲላቸው ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እያደረገ መሆኑን ዐውቀዋል:: ኢየሱስ ይህን ያለው በግሪክ ወይም በአረማይክ ቢሆን እንኳ ምን እያለ እንደ ነበር ትርጒሙ ግልጽ ነው:: ይህን፣ «ያሕዌ» የተሰኘ በቃላት ሊገለጥ የማይቻል የእግዚአብሔር ስም ኢየሱስ ለራሱ ተጠቅሞበታል:: እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በዚህ መጠሪያ ነበር:: «ያለና የሚኖር» መሆኑን ለሙሴ ነግሮታል (ዘፀ 3÷14):: ምናልባትም ይህ ኢየሱስ አምላክ ስለ መሆኑ በግልጽ የተናገረበት ይሆናል:: አይሁድም በትክክል ተረድተውታል:: ምን እያለ እንደ ነበር በትክክል በመረዳታቸው እግዚአብሔርን ተሳድበሃል በማለት ሊገድሉት ተዘጋጅተዋል:: ኢየሱስ የተናገረው ሐሰት ከሆነ፣ በሙሴ ሕግ መሠረት መገደል ነበረበት (ዘሌ 24÷16):: የተናገረው እውነት ከሆነ ግን በሥጋ የተገለጠ ሕይወት ምንጭ የሆነውን ሊገድሉ ነው ማለት ነው

(ሐሥ 2÷36፤ 3÷15)። እየተሠራ ከነበረው መቅደስ የወዳደቁ ድንጋዮች አነሡ (ከዮሐ 2÷20 ጋር ያነ)። በጊዜው በሰው ልጆች ታሪክ ተሰምቶ የማይታወቅ ታላቅ ድፍረትን ለመበቀል ተዘጋጅተዋል።

**§ 100ሀ**
**ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን ፈወሰ**
**(ዮሐ 9÷1-7)**

ይህ ተአምር ምዕራፍ 5 ላይ ካለው ሽባ ሰው መፈወስ ጋር ይመሳሰላል። ሁለቱም የተፈጸሙት በሰንበት ነበር፤ ሁለቱም ከውሃ ምንጭ ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ሁለቱም ከሃይማኖት መሪዎቹ ጋር ለከፍተኛ ክርክር ምክንያት ሆነዋል። በጴጥሮስና ዮሐንስ በኩል ከተፈወሰው አንካሳ ሰውም ጋር በጣም ይመሳሰላል (ሐሥ 3)። ያም ቢሆን መጠነኛ ክርክር በማስነሣት ለወንጌል መስፋፋት ታላቅ ዕድል አስገኝቷል።

**ዮሐ 9÷1-3**

1በመንገድ ሲያልፍም ከተወለደ ጀምሮ ዐይነ
ስውር የሆነ ሰው አየ። 2ደቀ መዛሙርቱም፣ «ረቢ፤ ይህ
ሰው ዐይነ ስውር ሆኖ እንዲወለድ ኀጢአት የሠራ ማን
ነው? እርሱ ራሱ ወይስ ወላጆቹ?» ብለው ጠየቁት።
3ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «እርሱ ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም፤
ይህ የሆነው ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ሕይወት እንዲገለጥ ነው።»

ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ መሰወሩን ስለሚያመለክት ይህ ፈውስ የተፈጸመው ኢየሱስን በድንጋይ ለመውገር በሞከሩበት ቀን ነበር ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ፣ ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ፣ ምናልባት በማግሥቱ ነበር ማለቱ የበለጠ ትክክል ይሆናል። ሰውየው የት እንደ ነበር ምንባቡ አይነግረንም፤ ይሁን እንጂ ዐይነ ስውር (ዮሐ 9÷8) በቤተ መቅደስ በር ተቀምጦ ምጽዋት መለመኑ የተለመደ ነበር (ከሐሥ 3÷2 ጋር ያነ)። በሦስተኛ ዓለም በጣም በተስፋፋና በውልደት ጊዜ ከጥንቃቄ



ጉድለትና ሕፃናት ተገቢውን ቪታሚን ባለማግኘታቸው በሚመጣ ዐይነ ስውርነት ተጠቅቶ ነበር።

በዘመኑ የነበሩ አይሁድም ሆኑ (ከኢዮ 4÷7፤ 8÷20 ጋር ያነ፤ ሉቃ 13÷2-5ን ይመ) አሕዛብ (ከሐሥ 28÷4 ጋር ያነ) ኀጢአት ላይ የሚወርድ መለኮታዊ ቅጣት በአካላዊ ሕመም አማካይነት ሊገለጥ እንደሚችል ያምኑ ነበር፤ ስለሆነም ያንን ዐይነ ስውር ሲያዩ፣ «ኀጢአት ያደረገው ማነው?» በማለት ለመጠየቅ ገፋፋቸው። እነርሱ ግን ሁለት አማራጮችን ብቻ ነበር የሚያስቡት።

በመጀመሪያ፣ የዚህ ሰው ዐይነ ስውርነት በራሱ ኀጢአት ምክንያት የመጣ የእግዚአብሔር ቅጣት ነው ወይ በማለት ጠየቁ። ዐይነ ስውርነቱ ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ፣ ምናልባት ኀጢአቱ በማሕፀን ውስጥ እያለ የተፈጸመ ይሆናል። በጣም በሚገርም ሁኔታ በዘመኑ እንዲህ ያለው እምነት ያልተለመደ አልነበረም። ዘፍጥረት 25÷22-26 ላይ ያለውን መሠረት በማድረግ የአይሁድ መምህራን በማሕፀን ውስጥ እያለ ኤሳው ያዕቆብን ለመግደል ሞክሮአል በማለት ያስተምሩ ነበር ከ(መዝ 51÷5፤ 58÷3 ጋር ያነ)።

ሁለተኛው አማራጭ፣ የዚህ ሰው ወላጆች ኀጢአት አድርገዋል፤ የወላጆቹን ኀጢአት እግዚአብሔር በቀጣዩ ትውልድ ላይ እያመጣ ነው የሚል ነው (ዘፀ 20÷5፤ ሆኖም ከኤር 31÷29-30፤ ሕዝ 18÷1-4 ጋር ያነ)። እግዚአብሔር እንዲህ ያደረገው በአሮጌው ኪዳን ድነት የሚገኘው በካህናቱና በአባቶች በኩል ስለ ነበር ነው። የቤተ ሰብ ድነት አባትን መሠረት ያደርጋል፤ ስለሆነም የተግባሩ ውጤት ግለ ሰባዊ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ሰቡ ጭምር የሚተርፍ ነበር። አዲሱ ኪዳን ግን ይህን ሁሉ ለውጧል (ኤር 31÷29-34)። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመንም ቢሆን የአባቶች ኀጢአት አካላዊም ሆነ ማኅበራዊ በሆነ መልኩ በልጆች ላይ ቅጣትን ያስከትላል። ለምሳሌ አካላዊውን የወሰድን እንደ ሆነ አባትየው

የሚወስልት ከሆነ ልጆቹ በተላላፊ በሽታና በኤድስ ሊጠቁ ይችላሉ:: ማኅበራዊውን የወሰድን እንደ ሆነ ደግሞ የሚደበደቡና የወሲብ ጥቃት የሚፈጸምባቸው ልጆች እነርሱም በገዛ ልጆቻቸው ላይ ያንኑ ይፈጽማሉ:: የምንወርሰው የወላጆቻችንን መልክና ቁመና ብቻ ሳይሆን፣ ኀጢአታቸውንም ጭምር እንዲሁ ይተላለፋል::

ሦስተኛ፣ (ደቀ መዛሙርቱ ያላቀረቡት አማራጭ) ይህ ኀጢአት ከአዳም የተላለፈ ይሆናል (ከሮሜ 5÷12-21 ጋር ያነ):: በአዳም ኀጢአት ይህ ዓለም በአብዛኛው መለወጡን ለመረዳት አንድ ሰው የግድ በመጀመሪያው ኀጢአት ማመን የለበትም:: ወንዶችና ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ (ዘፍ 3÷16-19) ምድር ራሷም ከመርገም በታች ናት (ዘፍ 3÷18፤ ሮሜ 8÷19-22):: ምድር ላይ የተላለፈው መርገም፣ ከሰዎች ኀጢአት ጋር በአንድነት ለበሽታ፣ ለሕመምና እግዚአብሔር ላላቀደው ጉስቊልና ሁሉ ምክንያት ሆኗል::[16]

አራተኛ፣ ኢየሱስ ይህ ሕመም ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ነበር አመለከተ:: እርሱን በመፈወስ ክብር እንዲያገኝ አንድ ሰው ለዘመናት ዐይነ ስውር እንዲሆን እግዚአብሔር መፍቀዱ ምናልባት ጭካኔ መስሎ ሊታየን ይችላል:: ሆኖም በሮሜ 9÷20-23 መሠረት ሁሉም ነገር በሉዓላዊ ማንነቱ ሥር ነው:: ያም ሆኖ ግን፣ «ይህ የሆነው» የሚለው ሐረግ (ቊ 3) ይህን ሕመም ያመጣ እግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም::[17] ምናልባት ኢየሱስ ለዚህ ሕመም ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የሚቀርበውን ማንኛውንም የግምት አስተሳሰብ ችላ በማለት ቀና ስለሆነ ገጽታው ብቻ እየተናገረ ይሆናል:: አነጋገሩ፣ «ይህ ሕመም እንዴት ሊመጣ እንደ ቻለ አይገደኝም፤ ሆኖም እርሱን በመፈወስ

[16] ይህ ኤድስን፣ ቂጥኝን፣ ጨብጥን፣ የተለያዩ ካንሰሮችን፣ የጨጓራና የአእምሮ ሕመምን፣ የምግብ እጥረት የሚመጡ በሽታዎችን፣ ሳምባ ጉት ልብ ወዘተ በሽታዎችን ሁሉ ይጨምራል::

[17] *hina* ብዙውን ጊዜ የሚመለክተው ዓላማን ቢሆንም ውጤትንም ያመለክታል::



እግዚአብሔር የሚከብር መሆኑ ግን ደስ ይለኛል» የማለት ያህል ነበር:: ይህ አባባል ምክንያታዊ ይመስላል:: በዚያ ቤተ መቅደስ ውበት ተመስጠው እያለ የመምህራኑን ነገረ መለኮታዊ ግምት ማውጠንጠን ያዙ:: ኢየሱስ ግን በተግባር ወደሚገለጥ ሩኅሩኅነት መራቸው:: እነርሱ፣ «ይህ እንዴት ሊደርስበት ቻለ?» በማለት ጠየቁ:: ኢየሱስ ደግሞ፣ «ምን ልናደርግለት እንችላለን?» በማለት ጠየቀ::

4ቀን ሳለ፣ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ፤ ዮሐ 9÷4-7
ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣል፤ 5በዓለም
ሳለሁ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ::
6ይህን ካለ በኋላ፣ በምድር ላይ እንትፍ ብሎ በምራቁ ጭቃ አበጀ፤
የሰውዬውንም ዐይን ቀባና፣ 7«ሄደህ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ» አለው፤ ሰሊሆም
ማለት 'የተላከ' ማለት ነው:: ሰውዬውም ሄዶ ታጠበ፤ እያየም ተመልሶ መጣ::

ቊጥር 4 እና 5 በአንድነት መነበብ ይኖርባቸዋል:: «ቀን» «እኔ በዓለም እያለሁ» የማለት አቻ ነው:: ኢየሱስ ስለ መጪው ሕማማቱ እያሰበ ነበር:: ወደዚያ በቀረበ መጠን፣ ትኵረቱን ዐሥራ ሁለቱን ማሰልጠን ላይ እንዳደረገ ሁሉ፣ በበለጠ ሁኔታ የራሱ አገልግሎትም ላይ አደረገ:: ኢየሱስ ሲሄድና ሥራው ሲያበቃ ሌሊት ይመጣል:: ለዐሥራ ሁለቱ ግን ያኔም ቢሆን ቀን ይሆናል:: ሥራቸው ይቀጥላል:: ይህ ሽግግር፣ ይህ የመጐናጸፊያ ቅብብል አንገብጋቢ ሁኔታ ነው:: ስለሆነም እዚህ ላይ ኢየሱስ፣ «እኛ» የሚል ተውላጠ ስም በመጠቀም፣ ወደ አገልግሎቱ ማዕከል ሲያመጣቸው እንመለከታለን:: ኢየሱስ፣ «መሥራት አለብን» አለ::

ከዮሐንስ 7÷3 ወዲህ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሲናገር ይህ የመጀመሪያው ነው:: ይሁን እንጂ፣ ሁሌም ከእርሱ ጋር ነበሩ:: ቀደም ሲል ሲደረግ የነበረውን ጠንከር ያለ ምልልስ ድምፃቸውን አጥፍተው

ሲታዘቡ ነበር:: ኢየሱስ ቀደም ሲል እንዳደረገው መሲሕነቱን እያወጀ ነበር:: «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» የሚለውን ቃል በቃል ነበር የደገመው፤ አባባሉ፣ «የተከበራችሁ ወገኖቼ፣ ተቃውሞው የቱንም ያህል ቢበረታም፣ መሲሕ ነኝ:: ከእውነቱ ወደ ኋላ ማለት አልፈልግም፣ ደግሞም አልችልም፤ እናንተም እንደዚያ ማድረግ አለባችሁ!» የማለት ያህል ነው::

የዓለም ብርሃን እንደሆነ መናገሩ የደቀ መዛሙርቱን ልብ ብቻ ሳይሆን፣ የዐይነ ስውሩንም ልብ ሳያሞቀው አልቀረም:: የኢየሩሳሌም ነዋሪ እንደ መሆኑ መጠን፣ ቤተ መቅደሱን ሞልቶ የነበረው ሕዝብ በቊጣ ሲገነፍል ሰምቶ ይሆናል:: በቤተ መቅደስ ደጃፍ የሚቀመጥ ለማኝ በመሆኑ ምናልባት የኢየሱስን ድምፅ ደጋግሞ በመስማት መለየት ሳይችል አልቀረም:: ማየት ባይችል እንኳ፣ መስማት ይችላል:: ከዐውዱ እንደምንመለከተውም፣ ብሩህ አእምሮ ነበረው:: «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» በማለት ኢየሱስ ሲናገር፣ እፊቱ ያለው ማን እንደ ነበር ብቻም ሳይሆን (ከቊ 11 ጋር ያነ) ይህ ሰው ስላስነሣው ጭቅጭቅም አያውቅም::

ምራቅና ጭቃ ለእኛ እንግዳ መድኀኒት ሊሆን ይችላል:: ለዐይነ ስውሩ ግን ጉልህ ምልክት ነበር:: ኤደርሼይም እንደሚያመለክተው (11:48) አይሁድ ምራቅ መድኀኒትነት እንዳለው ያምኑ ነበር:: ሊፈውሰው እንደሆነ ኢየሱስ ለሰውየው መንገር አልነበረበትም:: ዐይኑ ላይ የተደረገው ጭቃና ኢየሱስ እንደ ፈዋሽ የነበረው ታዋቂነት ለራሳቸው መናገር ይችላሉ (ዮሐ 7÷31፤ ዮሐ 5:1-9 እና 7÷23):: ስለዚህም ኢየሱስ ወደ ሰሊሆም (የተላከ ማለት ነው) ሲልከው ያለ ማመንታት ነበር የሄደው::

እዚህ ላይ አንዳንድ ትእምርታዊ ነገሮች አሉ:: የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ (ዮሐ 8÷12፤ 9÷5) ለዚህ ዐይነ ስውር ብርሃን



ይሰጣል::[18] ከእግዚአብሔር የተላከው ኢየሱስ (ዮሐ 7÷16፣ 18፣28-29፣33፤ 8÷14፣16፣18፣26፣29፣42) እንዲታጠብ ዐይነ ስውሩን ወደ ሰሊሆም ምንጭ «ላከው»:: ሰሊሆም ለመቅደሱ የዳስ በዓል ውሃ የሚቀዳበት ቦታ ነው:: «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» (ዮሐ 7÷37) በማለት ኢየሱስ የተናገረው እዚህ ነበር:: ይህ ፈውስ የበዓሉ የመጨረሻ ጥቂት ቀኖችና የኢየሱስ ልብ ሙሉ አነጋገር ጉልህ መገለጫ ሆነ:: የኢየሱስን ንግግሩ ይከዱ ይሆናል፤ ሥራዎቹን እንዴት እንደሚያደርጉ ግን እንመለከታለን:: ሁለቱም አንደ ነገር ነው የሚናገሩት::

**§ 100ለ**
**ጐረቤቶቹ ዐይነ ስውሩን መረመሩት**
**(ዮሐ 9÷8-12)**

8 ጐረቤቶቹና ከዚህ ቀደም ብሎ ሲለምን ያዩት ሰዎች፣ «ይህ ሰው ተቀምጦ ሲለምን የነበረው አይደለምን?» አሉ:: 9 አንዳንዶቹም፣ «በእርግጥ እርሱ ነው» አሉ:: ሌሎችም፣ «ይመስለዋል እንጂ እርሱ አይደለም» አሉ:: እርሱ ግን፣ «እኔው ነኝ» አለ::

10 እነርሱም፣ «ታዲያ ዐይኖችህ እንዴት ተከፈቱ?» ሲሉ ጠየቁት::

11 እርሱም፣ «ኢየሱስ የሚሉት ሰው ጭቃ አድርጎ ዐይኔን ቀባኝ፤ ወደ ሰሊሆም ሄጄ እንድታጠብም ነገረኝ፤ ሄጄ ታጠብሁ፣ ማየትም ቻልሁ» ሲል መለሰ::

12 እነርሱም፣ «ታዲያ፣ ያ ሰው የት አለ?» አሉት:: እርሱም፣ «እኔ አላውቅም» አለ::

ማንም እንደሚጠብቀው ከተፈወሰ በኋላ ሰውየው ወደ ቤቱ ሄደ (ቊ 7):: ጎረቤቶቹ ዐይናቸውን ማመን አቃታቸው:: መልኩ እርሱን ይመስላል፤ ድምፁም የእርሱ ነው:: ከዚህ በፊት ግን እንዲህ ሆኖ

---

[18] በዮሐንስ ጽሑፎች መሠረት ዐይነ ስውርነት ያለ ማመን ምሳሌ ነው (ዮሐ 9÷39-41፤ 12÷40፤ 1ዮሐ 2÷11):: ስለሆነም የዚህ ዐይነ ስውር ታሪክ የእስራኤልን መንፈሳዊ ሁኔታ ያመለክታል፡፡ J.M. Lieu, "Blindness in Johannine Tradition." *NTS* 34 (1988): 83-95.

አያውቅም (ቊ 32):: ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደ ሰው እንዴት ሊፈወስ ይችላል? በቤተ መቅደሱ እንደ ነበረው ሕዝብ ሁሉ፣ ጎረቤቶቹም በሁለት የተለያዩ አስተሳሰቦች መካከል ተከፋፈሉ:: አንዳንዶች እርሱ ራሱ መሆኑን ርግጠኞች ነበሩ:: አንዳንዶች ደግሞ እርሱን የሚመስል ሌላ ሰው ነው አሉ:: ዐይነ ስውር የነበረው ሰው ግን በአጭር ቃል፣ «እኔው ነኝ!» አላቸው::

ሕዝቡ ምርመራቸውን ጀመሩ:: 1ኛ ጥያቄ፣ ምን ተፈጠረ? የሆነውን ነገር ሰውየው በአጭርና ግልጽ ቋንቋ ነግሮአቸዋል:: በንግግሩ መሐል የኢየሩሳሌም ሰዎችን የሚያቆም ቃል ተናገረ:: «ኢየሱስ የሚሉት ሰው ...» አለ:: መቼም ይህ ሰው ቤተ መቅደሱ ውስጥ ኹከት የፈጠረ ገሊላዊ እንደ ነበር ነው የሚታሰበው:: እነዚያ የኢየሩሳሌም ሰዎች ለበዓሉ ከመጡ ተራ ሰዎች ይልቅ ለኢየሱስ አነጋገር ይህን ያህል ደንታ አልነበራቸውም:: የአይሁድ ሸንጎ መማክርት ኢየሱስን በተመለከተ እንዲህ ያለ አመለካከት እንደነበራቸው ገና ከበዓሉ በፊት ይታወቅ ነበር (ዮሐ 7÷25):: በዓሉ እየተከበረ እያለ እንኳ ኢየሱስን ለመያዝ ጥቂት ሙከራዎች ሲያደርጉ (ዮሐ 7÷30፣32፣44) እንዲያውም አንድ ጊዜ በድንጋይ ሊወግሩት እንኳ ፈልገው ነበር (ዮሐ 8÷59):: ለኢየሱስ ቀና አመለካከት ያላቸው ሁሉ ከቤተ መቀደሱ እንደሚወገዱም ያውቃሉ (ዮሐ 9÷22):: ባለ ሥልጣናቱ ማወቅ የፈለጉት ይህን ነበር:: ስለዚህ 2ኛ ጥያቄ አቀረቡ፤ ኢየሱስ የት ነው? ዐይነ ስውሩ እንዴት ዐወቀ? ከኢየሱስ ተለይቶ ከሄደ በኋላ እርሱን የሚያገኝበት መንገድ አልነበረም:: በምንጩ እስኪታጠብ ድረስ ዐይነ ስውር ነበር:: ከሰሊሆም ምንጭ በቀጥታ ወደ ቤቱ ነበር የመጣው::



**§ 100ሐ**
***ፈሪሳውያን ዐይነ ስውሩን መረመሩት***
**(ዮሐ 9÷13-34)**

[13]እነርሱም ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው ወደ
ፈሪሳውያን ወሰዱት:: [14]ኢየሱስ ጭቃ የሠራበት፣
የሰውዬውንም ዐይን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበር::
[15]ስለዚህ ፈሪሳውያንም እንዴት ማየት እንደ
ቻለ ጠየቁት:: ሰውየውም፣ «እርሱ ዐይኔን ጭቃ ቀባኝ፤
እኔም ታጠብሁ፤ ይኸው አያለሁ» አላቸው:: [16]ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ፣ «ይህ ሰው
ሰንበትን ስለማያከብር፣ ከእግዚአብሔር አይደለም» አሉ:: ሌሎች ግን፣ «ኀጢአተኛ
እንዲህ ያሉትን ታምራዊ ምልክቶች እንዴት ሊያደርግ ይችላል?» አሉ::
በመካከላቸውም አለመስማማት ተፈጠረ::
[17]ስለዚህ፣ ዐይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው ተመልሰው፣ «ዐይንህን ስለ
ከፈተው፣ እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ?» አሉት:: ሰውየውም፣ «እርሱ ነቢይ ነው»
አለ::

ቀኑ ሰንበት ስለ ነበር የፈሪሳውያኑ መሰብሰብ፣ መደበኛ የአይሁድ ሸንጎ መማክርት ስብሰባ አልነበረም:: በሌላ አባባል፣ ኢየሱስን ይዘው ለመመርመር ወይም ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው ከቤተ መቅደስ የማግለል ሕጋዊ ሥልጣን አልነበራቸውም ማለት ነው (ቊ 34):: ይሁን እንጂ፣ እነዚያ ፈሪሳውያን የፈለጉትን ለማድረግ ዐቅም እንደ ነበራቸው ግልጽ ነው:: ፈሪሳዊነት በሕዝቡ የተወደደ ስለ ነበር ሳይሆን፣ ኢየሱስን ወደሚመለከት ጉዳይ ሲመጡ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን መጥፎ ሰው መሆኑን ስለሚስማሙ ብቻ የሚያሳልፉትን ውሳኔ ሁሉ መማክርቱም እንደሚደግፉአቸው እርግጠኞች ነበሩ::

ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን አመጡት:: ምናልባት ጎረቤቶቹ አብረውት ይሆናሉ፣ ወይም ስለ ሁኔታው የሰሙ ፈሪሳውያን አስጠርተውት ይሆናል:: እዚያ ሲደርሱ ፈሪሳውያን የሰውየው ጎረቤቶች እንዳደረጉት ሁሉ እነርሱም፣ «እንዴት ማየት ቻልህ?» በሚል ጥያቄ ነበር ምርመራቸውን የጀመሩት:: የሰውየው

መልስ እጥር ያለ ቢሆንም እንደ መጀመሪያው ሁሉ ጥርት ያለ ነበር፤ «ዐይኔን ጭቃ ቀባኝ፤ እኔም ታጠብሁ፤ ይኸው አያለሁ» አለ። አንዴ ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜ ኢየሱስ ሰንበትን በመሻሩ ፈሪሳውያን በጣም ተናድደዋል! በመጀመሪያ ጭቃ ሠርቶ ሰውየው ዐይን ላይ በማድረጉ፤ ሁለተኛው፣ በሰንበት ቀን በመፈወሱ። በባሕላቸው መሠረት ሁለቱም በጥብቅ የተከለከሉ ነበሩ።

በሰንበት ፈውስሃል ተብሎ የሚነሣው ክርክር ለኢየሱስ የተለመደ ነበር። ከዐሥራ ስምንት ወሮች በፊት በኢየሩሳሌም፣ (ዮሐ 5÷10-18) እንዲሁም በገሊላ (ማቴ 12÷1-14) ሰንበትን አስመልክቶ የነበራቸውን ወግ ከንቱነት ገልጦባቸው ነበር (§ 49ለ፣ 50፣51 ጋር ያነ)። ኢየሱስ አንድን ክርክር ከረታ በኋላ፣ ድጋሚ እንደማያነሣው ቀደም ሲል ተመልክተናል (ለምሳሌ 7÷49)። ይህ እንዲከበር የሚፈልጉት ሥርዐት ነበር። ዘወትር የሚሹት ሃይማኖታዊ ምክንያት ነበር። እንደምንመለከተው ግን ይህን ቢተዉት ይሻላቸው ነበር።

ሰንበትን በተመለከተ የተነሣው ክርክር፣ ታላቅ ተአምር መደረጉን ይጨምራል። (ቍጥር 16 ላይ፣ «ምልክቶች» በሚል ብዙ ቍጥር መጠቀሙ፣ ስለ ሌሎች የኢየሱስ ተአምራትም ሳያውቁ እንደማይቀር ሊያመለክት ይችላል)። ዐይነ ስውርን መፈወስ በእርግጥ የሚገርም ነው። ከዚያ በፊት ተሰምቶ አይታወቅም። ይህ ሐቅ «ኀጢአተኛ እንዴት ተአምር ማድረግ ይችላል?» የሚል ጥያቄ ያነሡ ፈሪሳውያንን እንኳ አላለፋቸውም። በወቅቱ የነበረው የፈሪሳውያን ነገረ መለኮተ እግዚአብሔር ኀጢአተኛን እንደማይሰማ ይገልጻል (ከመዝ 34÷15፤ 66÷18፤ ምሳ 15÷29፤ 28÷9፤ ኢሳ 1÷15፤ 59÷2፤ ሚክ 3÷4፤ ያዕ 5÷16 ጋር ያነ)።[19] ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ፣ ኀጢአተኛ እንዲህ ያለ ተአምር ማድረግ አይችልም።[20] ግራ የሚያጋባውም ይኸው ነው። በአንድ በኩል ኢየሱስ በግልጽ የሚታወቅ ሥርዐተ ተውፊት ተላልፏል። ይህ ሥርዐት የቅዱሳት መጻሕፍቱ ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ይታሰብ ነበር። ከዚህም የተነሳ እንግዲህ ኀጢአተኛ መሆኑ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ ያለው ተአምር የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያመለክታል። ይህም ኀጢአተኛ አይደለም ማለት ነው። ስለሆነም ከሁለት አንዱ እውነት መሆን አለበት፤ ይህ ተአምር በፍጹም አልተደረገም፤ (ይህን ለማረጋገጥ ብዙ መድከም አለባቸው) ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር ነቢይ ኢየሱስ በሰዎች ሥርዓት አይገደብም። እነርሱ ደግሞ ይህን መቀበል አይፈልጉም። ያም ሆኖ ሐቁን ፊት ለፊት ለመጋፈጥ ፈቃደኛ በሆኑ ፈሪሳውያን መካከል አንዳንድ አስተዋዮችም ነበሩ። እንደ ገና የፈሪሳውያንን ኅብረት እንኳ ሳይቀር ኢየሱስ ሲከፋፍል እንመለከታለን።

ከተአምሩ ወደ ኢየሱስ ተመልሰው፣ (ዋናው ጉዳይ ይኸው ነው) ዐይነ ስውሩን፣ «ለመሆኑ፣ አንተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ?» በማለት ጠየቁት። የሰጠው መልስ ምናልባት ፈሪሳውያን ረጋ ብለው እንዲያስቡ ማድረግ ይችላል። ይህ ተአምር ስላስከተለው ውጤት ቆም ብለው እንዲያጤኑ ያደርጋቸው ይሆናል። ግን፣ ምን መልስ እንዲሰጣቸው ነበር የጠበቁት? ኢየሱስ ለዐይነ ስውሩ ማየትን ሰጠ። ይህ ዐይነ ስውር ለማኝ ለፀጉር ስንጠቃ ደንታ አልነበረውም። ዐይነ ስውር ነበር፤ አሁን ግን ያያል። ይህ ፈዋሽ ነቢይ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም!

---

[19] ፈሪሳውያን የኢየሱስ አጋንንትን የማስወጣት ኀይል ከቡዔል ዜቡል ጋር የተያያዘ ነበር ማለታቸው እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን አይሰማም የሚል እምነታቸውን አይጻረርም። ሰይጣን በአጋንንት ላይ ሥልጣን አለው፤ ስለዚህም ሊቈጣጠራቸው ይችላል ቢባል አግባብ ነው። ስለሆነም የኢየሱስ አጋንንት የማስወጣት ሥልጣን መለኮታዊ ሳይሆን ሰይጣናዊ ነበር ማለት ነው። የሰይጣን ዐይነ ስውርነትን መፈወስ ግን የግድ ምክንያታዊ ሊሆን አይችልም። ይህ በዐይነቱ የተለየ ተአምር ነው።

[20] ይሁን እንጂ ይህ አጠያያቂ ድምዳሜ ነውና ተአምር የማድረግ ኀይል የእግዚአብሔር ብቻ አይደለም (ማቴ 7÷22፤ 2ቆሮ 11÷14፤ 2ተሰ 2÷9)።

ዮሐ 9÷18-23

18አይሁድ ወደ ወላጆቹ ልከው እስኪያስጠሯቸው
ድረስ፣ ሰውየው ዐይነ ስውር እንደ ነበረና እንዳየ
አላመኑም ነበር። 19እነርሱም፣ «ዐይነ ስውር ሆኖ
ተወልዷል የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታዲያ፣ አሁን
እንዴት ሊያይ ቻለ?» አሏቸው።
20ወላጆቹም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ «ልጃችን መሆኑንና ዐይነ ስውር ሆኖ
መወለዱን እናውቃለን፤ 21አሁን ግን እንዴት ማየት እንደቻለና ዐይኖቹን ማን እንደ
ከፈተለት እኛ አናውቅም። ሙሉ ሰው ስለሆነ፣ ስለ ራሱ መናገር ይችላልና እርሱን
ጠይቁት።» 22ኢየሱስን፣ ክርስቶስ ነው ብሎ የመሰከረ ሁሉ ከምኵራብ እንዲባረር
አይሁድ አስቀድመው ወስነው ስለ ነበር፣ ወላጆቹ ይህን ያሉት አይሁድን ፈርተው
ነው። 23ስለዚህ ወላጆቹ፣ «ሙሉ ሰው ስለሆነ እርሱን ጠይቁት» አሉ።

የመጀመሪያው ምርመራ ውጤት አላስገኘም። ኢየሱስን ለማውገዝ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ይልቅ፣ አንዳንድ ፈሪሳውያንን ለእርሱ ያላቸውን አመለካከት እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል። ስለዚህ ሌላ መንገድ ፈለጉ። ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው ወላጆች አስጠሩ። ሁለተኛው ምርመራም ቢሆን የበለጠ ውድቀት ነበር ያመጣባቸው። ወላጆቹ፣ «አዎን፣ ልጃችን ነው፤ ዐይነ ስውር ሆኖ መወለዱም እውነት ነው» በማለት መስማት ያልፈለጉትን ነገሯቸው። መናገር የፈለጉት ይህን ብቻ ነበር። ከቤተ መቅደስ እንዲባረሩ አይፈልጉም። ሐቁ ግን ልጃቸው እንዴት እንደ ተፈወሰ መዋሸታቸው ነበር። የፈወሰው ኢየሱስ እንደ ነበር ያውቃሉ (ቊ 22)። ከዚህም በላይ፣ ጎረቤቶቹ ሁሉ የሚያውቁትን ወላጆቹ አያውቁም ማለት በፍጹም የማይታሰብ ነው።

እነዚህን ሰዎች በጣም መጫን የለብንም። ከቤተ መቅደስ መባረር በጣም አስፈሪ ነገር ነው (ከሉቃ 6÷22፤ ዮሐ 12÷42፤ 16÷2 ጋር ያነ)። የአይሁድ ማኅበረ ሰብ ሁለገብ ስለ ነበር አንድ ሰው ከምኵራብ ከተባረረ ሃይማኖታዊ፣ ቤተ ሰባዊ፣ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ትስስሩን ሁሉ ያጣ ነበር። እጅግ አስፈሪ ነገር ነው። በተጨማሪ ዐይነ ስውሩ ሰው ለማኝ ነወ (ቊ 8)። ይህ የሚያሳየው የዚያ ቤተ ሰብ ኤኮኖሚ ምን ያህል ዝቅ ያለ መሆኑን ነው። ከማኅበረ ሰቡ ተቆራርጠው መኖር አይችሉም። ከዚህም በተረፈ እንደምንመለከተው የልጁ አነጋገር ለዛና አስተዋይነት የላቀ ነበር። ከእርሱ በላይ ሊከራከሩ አይችሉም። ምንም እንኳ ልጃቸውን አጋልጠው መስጠት ቢሆንም፣ ቤተ ሰቡ ማድረግ የሚችለው የብልኀነት መንገድ ይኸው ነው።

ዮሐ 9÷24-27

24ዐይነ ስውር የነበረውንም ሰው ዳግመኛ
ጠርተው፣ «አንተ ሰው፤ እግዚአብሔርን አክብር፤ ይህ
ሰው ኀጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን» አሉት።
25እርሱም፣ «ኀጢአተኛ መሆኑን እኔ አላውቅም፤ ነገር ግን ዐይነ ስውር እንደ
ነበርሁ፤ አሁን ግን እንደማይ ይህን አንድ ነገር ዐውቃለሁ» አለ።
26እነርሱም፣ «ምን አደረገልህ? እንዴትስ ዐይንህን ከፈተ?» ብለው ጠየቁት።
27እርሱም፣ «አስቀድሜ ነገርኋችሁ፤ አላዳመጣችሁኝም፤ ለምን እንደ ገና መስማት
ፈለጋችሁ? እናንተም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትሻላችሁ?» አለ።

ፈሪሳውያን መጥፎ ቀን ገጥሟቸዋል! በእርግጥ ተአምር መፈጸሙ አሁን ግልጽ ሆኗል። ተአምሩን ከኢየሱስ ጋር ካያያዙት፣ የእግዚአብሔርን ነቢይ በመቃወማቸው ስሕተት መፈጸማቸውን ማመን ሊኖርባቸው ነው። ያላቸው አማራጭ ተአምር መደረጉንና ከኢየሱስ ጋር የተያያዘ አለመሆኑን መቀበል ነው። ይህ ደግሞ፣ «አዎን፣ ከዐይነ ስውርነት ተፈውሶሃል፤ ሆኖም የኢየሱስ ድርሻ ከአጋጣሚነት ያለፈ አይደለም፤ የፈወሰህ እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ብቻ ነው!» የማለት ያህል ነው። ለዚህም ነበር፣ «እግዚአብሔርን አክብር» ያሉት። ለአንድ አይሁድ ይህ አባባል ምስጋና ብቻ ሳይሆን፣ ኑዛዜም ጭምር ነው (ከኢያ 7÷19 ጋር ያነ)። ይህን ተአምር ከኢየሱስ ጋር በማያያዝ በደል

ፈጽመሃል፤ ስለዚህ መናዘዝ ይኖርብሃል በማለት ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው በብዙ መንገድ እየጠየቁ ነው።

የተፈወሰው ሰው ግን ሞኝ አልነበረም። ቁርጥ ያለ መልስ ነበር የሰጠው። «እናንተ ፈሪሳውያን ስለ ኢየሱስ ሁሉንም እንደምታውቁ ትናገራላችሁ። ለእኔ ግን ይህ አይገባኝም። ስለ ነገረ መለኮታዊ ክርክራችሁ ግድ የለኝም። እኔ የማውቀው፣ ዐይነ ስውር እንደ ነበርሁና አሁን ግን ማየቴን ነው! ይህ ይበቃኛል» አላቸው።

ፈሪሳውያን፣ «ለመሆኑ ምን አደረገልህ?» በማለት ጠየቁት። የፈወሰው በእርግጥ ኢየሱስ መሆኑን የሚያረጋግጥ መልስ በመጠበቅ የጠየቁ ይመስላል። በዚህም ጊዜ ቢሆን የተፈወሰው ሰው በወጥመዳቸው አልተያዘም። ያንኑ ጥያቄ መልሰው መላልሰው እየጠየቁ እንደ ነበር ነገራቸው። ዙሪያ ጥምጥም መሄድ ወይም፣ አንዱን ነገር መደጋገም አልፈለገም። እነርሱም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሆን ይፈልጉ እንደ ነበር ፈሪሳውያንን በመጠየቅ ነበር ዙሪያ ጥምጥም ከሆነ አካሄድ ያወጣቸው።

ይህ ሰው ዐይነ ስውር እንጂ ደንቆሮ አልነበረም። በቤተ መቅደስ የነበረውን ክርክር ያለ ጥርጥር ሰምቷል። እንዲህ ያለው የሰላቅ አነጋገር ከፈሪሳውያን እንደሚለያየው ያለ ጥርጥር ይረዳል። ይህ ግን ለእርሱ ምኑም አልነበረም። አሁንም ቢሆን ለማኝና ከማኅበረ ሰቡ የተጣለ ነው። በማኅበረ ሰቡ፣ «መታቀፍ» ምን እንደሆነም አያውቅም። ስለሆነም መባረር ለእርሱ ይህን ያህል ጉዳት የሚያመጣ አልነበረም። በተጨማሪም፣ አስተዋይ አእምሮ ያለው ዐይነ ስውር ለማኝ ቤተ መቅደሱ ደጃፍ ተቀምጦ ለማሰላሰል በቂ ጊዜ ይኖረዋል። የፈሪሳውያንን ንግግርና ዓላማ ሲገነዘብ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ አለመሆኑ እርግጥ ነው። የፈረሳውያንን ስውር ማንነት ዐይቷል። ኢየሱስ እንዳየው ሁሉ አጉል ክርክራቸውን፣ ጋጠ ወጥነታቸውን፣ ከንቱ መንጠራራታቸውን ዐይቶአል። በሕይወት ውስጥ በእርግጥ አስፈላጊና ውበት ያለውን ነገር



ሲያሰላስል ኖሮአል። ሆኖም እዚህ አላገኘውም። መሠረታዊ ሐሳቡ ይህ ነው፤ ኢየሱስ ሊታመን በማይቻል ሁኔታ ማየትን ሰጥቶታል። ይህን በማድረጉም ሰብዓዊ ፍጡር ብቻ እንዳልነበር አረጋግጧል። ስለዚህም ፊቱን ከኢየሱስ ማዞር ውለታ ቢስነት ብቻ ሳይሆን ቁልቁል መውረድ ጭምር ይሆናል። እርሱ የእስራኤል ተስፋ የሆነው መሲሑ ነው!

28ከዚህ በኋላ በእርሱ ላይ የስድብ ናዳ
በማውረድ እንዲህ አሉት፤ «የዚህ ሰው ደቀ መዝሙር ዮሐ 9፥28-34
አንተ ነህ፤ እኛስ የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን!
29እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እናውቃለን፤ ይህ
ሰው ግን ከየት እንደ መጣ እንኳ አናውቅም።»
30ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እናንተ ከየት እንደ መጣ
አለማወቃችሁ የሚያስደንቅ ነው፤ ይሁን እንጂ እርሱ ዐይኖቼን ከፈተልኝ።
31እግዚአብሔር የሚሰማው፣ የሚፈራውንና ፈቃዱን የሚያደርገውን እንጂ፣
ኀጢአተኞችን እንደማይሰማ እናውቃለን፤ 32ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደን ሰው ዐይን
የከፈተ አለ ሲባል፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ማንም ሰምቶ አያውቅም። 33ይህ ሰው
ከእግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ይህን ማድረግ ባልቻለ ነበር።
34እነርሱም፣ «ሁለንተናህ በኀጢአት ተነክሮ የተወለድህ አንተ እኛን
ለማስተማር እንዴት ትደፍራለህ?» ሲሉ መለሱለት፤ አባረሩትም።

ፈሪሳዊ ደቀ መዝሙር ይሆናል ብሎ ማሰቡ ራሱ የማይመስል ነው! ሆኗልስ ወይ (ከዮሐ 3፥1-2፤ 7፥50-52፤ 8፥30፤ 19፥39፤ ማቴ 27፥57፤ ሐሥ 15፥5)? ወይስ ሸኪስፒር በሐምሌት አማካይነት እንደሚለው፣ «ወይዘሮዋ፣ ይሆናል ብሎ ማሰብን ትቃወማለች» እንዳለው መሆኑ ነው። ስድባቸው እርግጠኝነት የማጣታቸው ምልክት ይመስላል። ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሙሴ ደጋፊዎች መሆናቸውን ይናገራሉ። ሆኖም፣ «ይህ ኢየሱስ የሚባለው ግን፣ አጭበርባሪ ነው» አሉ።

በዐይነ ስውሩ ድፍረት ከመደነቅ ሌላ የምንለው የለም:: በአቋሙ መጽናቱ፣ ከአነጋገሩ ምክንያታዊነት ጋር ተዳምሮ እነዚህ ፈሪሳውያን ከሚችሉት በላይ ሆኖባቸዋል:: የፈሪሳውያኑን ውስጠ ወይራ አነጋገር (ቊ 16) በመጠቀም መልስ መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ማስረጃ አቅርቦላቸዋል:: ፈሪሳውያን፣ ምክንያት ማቅረብ ካልቻልህ፣ ሰውየውን አጥቃ የሚለውን የቈየ አባባል እንዲይዙ ተገደዋል:: ሲወለድ ጀምሮ ኀጢአተኛ መሆኑን ነገሩት:: ቀደም ሲል ያንን ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሰምቶ ነበር (ዮሐ 9፥2):: ይሁን እንጂ፣ «የዓለም ብርሃን» እና «ብርሃን ሰጪ» የሆነው ኢየሱስ፣ «እርሱ ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም፤ ይህ የሆነው ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ሕይወት እንዲገለጥ ነው» በማለት ትክክለኛውን መልስ ሰጥቶ ነበር:: ያቀረቡት ክስ «ተፍረከረከ»:: የተፈወሰው ሰው እውነት አለመሆኑን ዐውቋል::

ፈሪሳውያን በዚህ ተራ ሰው መማር አልፈለጉም:: እፊታቸው መገኘቱ ራሱ ግን ይፈርድባቸዋል:: ሕያው የኢየሱስ ምስክር ነበር:: ስለዚህም ከፊታቸው አባረሩት:: ምንም እንኳ ቃሉ [*exebalon*] ቊጥር 22 ላይ ካለው የተለየ ቢሆንም «ከምኵራብ የታገደ» ይመስላል:: ለእርሱ ይህን ያህል ጉዳት የለውም:: ከምንም በተለይ ደግሞ፣ የዐይኑን ብርሃን ሊወስዱበት አይችሉም::

**§ 100መ**
**ኢየሱስ ዐይነ ስውሩን ወደ ማመን አመጣው**
**(ዮሐ 9፥35-38)**

35ኢየሱስም ሰውየውን እንዳባረሩት ሰማ፤ ባገኘ
ውም ጊዜ፣ «በሰው ልጅ ታምናለህን?» አለው::
36ሰውየውም፣ «ጌታዬ፤ አምንበት ዘንድ እርሱ
ማን ነው?» ሲል ጠየቀው::
37ኢየሱስም፣ «አይተኸዋል፤ አሁንም ከአንተ ጋር
የሚነጋገረው እርሱ ነው» አለው::
38ሰውየውም፣ «ጌታ ሆይ፣ አምናለሁ» አለ፤
ሰገደለትም::



በንጽጽሩ ኢየሱስ፣ ይህን «ውግዘት» ያገናዝባል:: ጣልቃ የሚገቡ ፈሪሳውያን (ቊ 40) ምናልባትም ብዛት ያላቸው ደቀ መዛሙርት ተከትለውታል:: ዐይነ ስውር የነበረው ሰው ኢየሱስን ሲያይ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነው:: ይሁን እንጂ ድምፁና ማበረታታቱ አጽንቶታል::

አንዳንድ ቅጂዎች፣ «የሰው ልጅ» በሚለው ምትክ፣ «የእግዚአብሔር ልጅ» (ቊ 35) የሚል ተክተዋል:: ዮሐንስ ስለ መሲሑ ሲናገር በሁለቱም ስለሚጠቀም ልዩነቱ ይህን ያህል ነው:: ስለሆነም ለዐይነ ስውሩ የቀረበውን ጥያቄ፣ «በመሲሑ ታምናለህን?» በሚል መልኩ ማስቀመጥ እንችላለን:: ዐይነ ስውሩ የሰጠውንም መልስ፣ «ማን እንደሆነ ከነገርኸኝ በእርሱ አምናለሁ» በሚል መልኩ ማስቀመጥ ይቻላል:: አደገኛ ውጤት ማስከተል በሚችል ከባድ ተቃውሞ ፊት ሰውየው ከኢየሱስ ጐን ቆሟል:: ቆራጥ ውሳኔውን ለደቀ መዛሙርቱ አሳይቷል (ቊ 28):: አሁን የሚያስፈልገው በቂ መመሪያ ነው::

ሰውዬው፣ «መሲሑ ማን ነው?» በማለት ጠየቀ:: ኢየሱስ፣ «እኔ ነኝ» አለው:: ስለሆነም፣ ምን ዐይነት ውሳኔ ላይ እንደሚደርስ ይታወቃል፤ «ጌታ ሆይ፣ አምናለሁ!» በማለት ለኢየሱስ ሰገደ:: ኢየሱስን ምን ያህል ዐውቆታል:: ቊጥር 11 ላይ፣ «ኢየሱስ የሚሉት ሰው» ብሏል:: ቊጥር 17 ላይ፣ «ነቢይ» መሆኑን ተቀበለ:: ቊጥር 33 ላይ ግን፣ «ከእግዚአብሔር» መሆኑን ተገነዘበ:: በመጨረሻም፣ ቊጥር 38 ላይ፣ «ጌታ» አለው:: ብዙ የሚማረው፤ ብዙ የሚያደርገው ይኖራል:: ይሁን እንጂ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጋር መሆን የሚያበቃውን ትምህርት አግኝቷል:: ሁሉንም ስለ መተው ኢየሱስ የሰጠውን መመሪያ በሚያስገርም ሁኔታ አሟልቶ ተገኘ (ማቴ 10፥34-39፤ ሉቃ 14፥26-33)::

**§ 100ሠ**
**ኢየሱስ**
**የፈሪሳውያንን**
**ዕውርነት ተናገረ**
**(ዮሐ 9÷39-41)**

[39]ኢየሱስም፣ «ዕውሮች እንዲያዩ፣ የሚያዩም እንዲታወሩ፣ ለፍርድ ወደዚህ ዓለም መጥቻለሁ» አለ:: [40]ከእርሱ ጋር ከነበሩት ፈሪሳውያን አንዳንዶቹ ይህን ሰምተው፣ «ምን ማለትህ ነው? ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን ነው?» አሉት:: [41]ኢየሱስም፣ «ዕውሮችስ ብትሆኑ ኀጢአት ባልሆነባችሁ ነበር፤ አሁን ግን እናያለን ስለምትሉ፣ ኀጢአታችሁ እንዳለ ይኖራል» አላቸው::

ኢየሱስ ለፍርድ እንዳልመጣ አንዳንዴ ሲናገር (ዮሐ 8÷15)፣ አንዳንዴ ግን ለፍርድ እንደ መጣ ይናገራል (ዮሐ 5÷27):: ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር አብ ፍርድን ሁሉ ለወልድ መስጠቱ እውነት ነው (ዮሐ 5÷22):: ወደ ዓለም የመጣበት ዓላማ ግን ዓለምን ለማዳን እንጂ ለመፍረድ አይደለም (ዮሐ 3÷17):: ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን የኢየሱስ ቃል፣ (ዮሐ 8÷26) ባልተቀበሉት ላይ ፍርድ ያመጣል (ዮሐ 12÷31):: ዮሐንስ 12÷47-48 ይህን በሚገባ ይገልጸዋል፤ *«ቃሌን ሰምቶ በማይፈጽመው ላይ የምፈርደው እኔ አይደለሁም፤ ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመጣሁምና:: በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያቃልል ላይ የሚፈርድበት አለ፤ የተናገርሁት ቃል ራሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል::»*

ኢየሱስ ትሑታንን ከፍ ሲያደርግ፣ ብርቱዎችን ግን ዝቅ የሚያደርግበትን መንገድ አስገራሚ ነው (ማቴ 11÷25):: ከማቴዎስ 13÷13-17 እንደምንመለከተው ኢየሱስ ምሳሌውን አስመልክቶ ብዙዎች ጆሮ ቢኖራቸውም መስማት እንደማይችሉ ተናግሮ ነበር:: እዚህ ላይ ግን ዐይን እንዳላቸውና ማየት እንዳልቻሉ ይናገራል:: የዐይነ ስውሩን አካላዊ ፈውስ ምሳሌ በማድረግ ስለ መንፈሳዊ ዕውርነት ተናገረ::

ፈሪሳውያን ወዲያውኑ፣ «ምን ማለትህ ነው? ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን ነው?» በማለት አሉታዊ መልስ የሚጠብቅ ዐይነት ጥያቄ አቀረቡ:: ኢየሱስም፣ «አይደለም፣ ዕውሮች አይደላችሁም:: በሚገባ ታያላችሁ:: ኀጢአት የሆነባችሁም ይኸው ነው» በማለት መለሰላቸው:: የማያውቁ ቢሆኑ፣ በሙሴ በኩል የእግዚአብሔር ቃል ባይሰጣቸው እና ትክክለኛውን ነገረ መለኮታዊ መልስ ባያውቁ ኖሮ፣ ኢየሱስን ችላ ማለታቸው ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር:: እንዲህ በመሆኑ ግን የተሻለ አውቀዋል (ዮሐ 15÷24)::

በእግዚአብሔር አሠራር መሠረት የመጀመሪያው መጨረሻ ይሆናል፤ የመጨረሻው መጀመሪያ ይሆናል:: ታላቁ ታናሽ፣ ታናሹም ታላቅ ይሆናል:: ያለማወቅ ጨለማ ውስጥ መሆናቸውን የተቀበሉ ወደ ኢየሱስ በመምጣት መንፈሳዊ ማየትን ያገኛሉ:: በትምህርታቸው የሚደገፉትን ግን እውነትን እንዳያዩ እግዚአብሔር ያሳውራቸዋል::

**§ 101ሀ**
**የመልካሙ እረኛና**
**የሌባው ምሳሌ**
**(ዮሐ 10÷1-18)**



እዚህ ላይ የኢየሱስ ትምህርት የአቀራረብ ለውጥ አድርጓል:: ከምዕራፍ 7-9 ባሉት ክፍሎች ቀጥተኛ በሆነ አቀራረብ ነበር የተጠቀመው:: በድንገት ምሳሌያዊ አነጋገር መጠቀም ጀመረ:: በዳስ በዓል ላይ በሦስት ወሮች ውስጥ (ዮሐ 10÷27-29)፣ ስለ እረኛውና በጎቹ መናገሩን ይቀጥላል:: ይህም አንዳንዶቹን፣ ዮሐንስ 10÷1-18 ከቀጣዩ የዳስ በዓል ጋር የተያያዘ እንጂ (ዮሐ 10÷22) ከዚያ በፊት ከነበረው የዳስ በዓል በኋላ የሚቀጥል አይደለም ወደ ማለት አድርሷቸዋል:: ዐውዱ ግን ከዳስ በዓል በኋላ እንጂ ከዳስ በዓል በፊት የቀረበ አያስመስለውም:: (1) ስለ መሪዎቹ ተቃውሞ ማውሳቱን ቀጥሏል (ዮሐ 10÷19-21)፤ (2) ኢየሱስን በተመለከተ ተፍጥሮ ስለ ነበረው የሐሳብ መከፋፈልም ይናገራል (ዮሐ 10÷19)፤ (3) ኢየሱስ ጋኔን ያደረበት ተብሏል (ዮሐ 10÷20)፤ (4) ስለ ዐይነ ስውሩ መፈወስም ይናገራል (ዮሐ 10÷21):: በሦስት ሠር ጊዜ የዳስ በዓል ላይ ኢየሱስ

ባለፈው ጊዜ ትምህርቱን ከቆመበት እንደ ገና ይቀጥላል:: የዳ በዓል ሲከበር ያደረገውም ይህንኑ ነው (ከዮሐ 7፥21-24 እና 5፥18 ጋር ያነ)::

**ዮሐ 10፥1-6**

1እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች ጉረኖ በበሩ
ሳይሆን፣ በሌላ በኩል ዘሎ የሚገባ ሌባና ነጣቂ ነው፤
2በበሩ የሚገባ ግን እርሱ የበጎቹ እረኛ ነው፤ 3በር
ጠባቂው በሩን ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰማሉ:: የራሱንም በጎች
በየስማቸው እየጠራ ያወጣቸዋል:: 4የራሱ የሆኑትንም ሁሉ ካወጣ በኋላ ፊት ፊታቸው
ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል:: 5እንግዳ የሆነውን ግን ድምፁን
ስለሚያውቁ ከእርሱ ይሸሻሉ እንጂ ፈጽሞ አይከተሉትም:: 6ኢየሱስ ይህን ምሳሌ
ነገራቸው፤ እነርሱ ግን ምን እንደ ነገራቸው አላስተዋሉም::

የኢየሱስ ምሳሌ ከዓሣ ማጥመድና ከእርሻ ጋር ሦስተኛ ዋነኛ ሥራ ስለ ሆነው እረኝነት ይናገራል:: እረኝነት ከመካከለኛው ምሥራቅ ባሕል ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው:: በብሉይ ኪዳንም በምሳሌነት በተደጋጋሚ ተነሥቷል:: ሁለቱም ሐቆች የኢየሱስን አነጋገር በተለየ ሁኔታ ጎምዛዛ አድርገውታል:: በትንሽ ቃላት ብዙ ይናገራል:: የኢየሱስን ምሳሌ በሚገባ ለመረዳት ስለ መካከለኛው ምሥራቅ እረኝነትና ስለ በጎቹ ራሳቸው መመልከት ይኖርብናል::

በጎቹ ቀኑን በሙሉ ተሰማርተው ከዋሉ በኋላ አንድ በር ብቻ ባለው ዋሻ ውስጥ እንዲያድሩ ይደረጋል:: አንዳንዴ እውነተኛ በር (ቍ 3) ቢደረግለትም፣ ብዙውን ጊዜ ግን በር የሚሆነው የዐለቱ ቀዳዳ ሲሆን፣ እረኛውም እዚያ አካባቢ ይተኛል:: በአንድ ጉረኖ ውስጥ ጥቂት በጎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ጠዋት ላይ እረኛ ሲጠራቸው እያንዳንዱ በግ ድምፁን በመለየት ይከተለዋል (ቍ 3):: በምሥራቃውያን ዘንድ በእረኛውና በበጎቹ መካከል ያለው መቀራረብ ግላዊ ነው:: በጎቹን ሁሉ በየስማቸው ያውቃቸዋል፤ እነርሱም ድምፁን ያውቃሉ (ቍ 5):: አንድ ሌላ ሰው እንደ እረኛው በመልበስ፣ ድምፁንም የእርሱን በማስመሰል



ቢቀርባቸው በጎቹ አይታለሉም (ቍ 5):: ጉረኖው ውስጥ ከነበሩ እዚያው ይቆያሉ:: ሜዳ ላይ ከነበሩ ግን በፍርሃት ይበታተናሉ::

እረኛው ረዳት መቅጠር ከቻለ፣ ሌሊት የሚጠብቅለት መሆን አለበት:: ሥራው ሌቦችና የዱር አውሬዎች እንዳይገቡ እንዲሁም የባዘነ በግ ወጥቶ እንዳይሄድ ጉረኖው በር ላይ ሆኖ መጠበቅ ብቻ ነው:: በበር ጠባቂው በኩል መግባት የሚችል ዋናው እረኛ ብቻ ነው (ቍ 3):: በጎች በጣም ተፈላጊና በቀላሉ ሊሰረቁ የሚችሉ በመሆናቸው እንዲህ መሆኑ ተገቢ ነው:: ፓለስቲና ለመሥረቅ በሚያደቡ ሌቦችና (*kleptes*) ከመስረቅ ይልቅ (ቍ 1) በኀይል መንጠቅ በሚፈልጉ ሽፍቶች (*testes*) የተሞላች ነበረች:: የምሥራቅ እረኞችን የተለዩ የሚያደርጋቸው ሌላው ነገር ፊት ፊት እየሄዱ በጎቹን መምራታቸው ነው (ቍ 4):: በሌላው አገር ግን በጎች ይነዳሉ:: ይህ የፓለስቲና እረኞች ለበጎቻቸው ስለሚያደርጉት ጥንቃቄ ሌላው አመልካች ነው::

ይህን ምሳሌ (ቃል በቃል *paroimia* - የላቀ እውነትን የሚሰውር የአነጋገር ዘዬ ቍ 6) ለመተርጐም እንዲረዳን ባሕላዊ ትዕምርቶችንና ከእነዚህ ትዕምርቶች በስተጀርባ ያለውን የብሉይ ኪዳን ነገረ መለኮት በአንድነት በማቀናጀት መመልከት ይኖርብናል:: ኢየሱስ መልካም እረኛ መሆኑ ግልጽ ነው:: በብሉይ ኪዳን ግን ይህ የእግዚአብሔር ተግባር ነበር (መዝ 23፤ 79፥13፤ 95፥7):: እንደ የእግዚአብሔር ተወካይ ለመሲሑ የተገባለት ተስፋም ነው (ሕዝ 34፥23):: ይህ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሌላ ጠንካራ ንግግር ነው:: በእኛም መካከል ቢሆን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በጎችን የሚያግዱ ቀማኞችና ሌቦች አሉን:: ኢየሱስ ይህን ሲናገር ከአድማጮቹ ወገን የነበሩ የአይሁድ መሪዎችን እያሰበ እንደ ነበር ግልጽ ነው (ዮሐ 9፥40፤ 10፥19):: በግትርነት ኢየሱስን ችላ በማለታቸው በበሩ በኩል ወደ ጉረኖው ለመግባት ፈቃደኛ አልሆኑም:: ያም ሆኖ ወደ በጎቹ መግባት

**ይፈልጋሉ**:: ለበጎቹ ደኅንነት ባለ ማሰብ በጭካኔ ይዘርፏቸዋል (ለምሳሌ ማቴ 23÷14-15፤ ሕዝ 34÷1-6)::

በዚህ *paroimia* ውስጥ፣ በተለይም ብሉይ ኪዳን ስለ እረኞች ከሚጠቀምበት ምስል አንጻር ከተመለከትነው ለመረዳት የሚደብድ ነገር የለም (ኤር 23÷3፤ አሞ 3÷12፤ ሚክ 2÷12፤ 5÷7-8):: ይህ፣ ቍጥር ስድስትን አስገራሚ ያደርገዋል:: ለመረዳት ያልቻሉት በከፊልም ቢሆን እግዚአብሔር ስላደነደናቸው እንደ ሆነ ማሰብ ይቻላል (ማቴ 13÷13-16፤ ሮሜ 11÷25)::

**ዮሐ 10÷7-13**

[7]ስለዚህ ኢየሱስ ዳግም እንዲህ አላቸው፤
«እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ ነኝ:: [8]ከእኔ በፊት
የመጡት ሁሉ ሌቦችና ቀማኞች ነበሩ፤ በጎቹ ግን
አልሰሟቸውም:: [9]በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል፤ ይገባል፤
ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል:: [10]ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ይመጣል፤
እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ::»
[11]መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ
ይሰጣል፤ [12]ተቀጣሪው እረኛ ግን በጎቹ የእርሱ ስላልሆኑ፣ ተኵላ ሲመጣ ጥሎአቸው
ይሸሻል፤ ተኵላውም በጎቹን ይነጥቃል፤ ይበትናቸዋልም:: [13]የሚሸሸውም ተቀጣሪ
ስለሆነና ለበጎቹ ደንታ ስለሌለው ነው::

ኢየሱስ ስለ እረኛ እየተናገረ የነበረበትን ዘይቤ ስለ በር ወደሚያመለክት ምሳሌ ለውጦታል:: ሐቁ፣ ብዙ ጊዜ እረኞች እንደ በር ማገልገላቸው ነው:: ምሽት ላይ በጎቹ ወደ ጉረኖው ሲመጡ አንድ በአንድ እረኛውን ተሻግረው ነበር የሚልፉት:: ቍስልና ስብራት ደርሶባቸው እንደ ሆነ ይመረምራል:: አስፈላጊ ከሆነም ቍስላቸው እንዳያመረቅዝ በዘይት ያክማቸዋል:: ከዚያም በጎቹ ሁሉ ከገቡ በኋላ ወደ ጉረኖው መግቢያ ፊት ለፊት ይተኛል::



ኢየሱስ መልካም እረኛ ነው (አጋቶስ ሳይሆን ካሎስ) (ከዕብ 13÷20፤ 1ጴጥ 2÷25፤ 5÷4 ጋር ያነ):: ይህም ውብ፣ በጐና ደግ ነው ማለት ነው:: ኢየሱስን የሚያውቅና በእርሱ የሚታወቅ ሁሉ በጉረኖው ውስጥ ነው:: በጉረኖው ውስጥ መኖርም የሚስገኛቸው ጥቅሞች አሉ:-

- ❖ ድነት፣ ቍ 9 - ሉቃ 19÷10፤ ዮሐ 3÷17፤ ሐሥ 4÷12፤ ሮሜ 5÷9፤ 10÷9-10፤ ኤፌ 2÷5-8፤ 2ተሰ 2÷13፤ ቲቶ 3÷5፤ 2ጴጥ 1÷11::
- ❖ መግቦት፣ «ይገባል፤ ይወጣል፤ መሰማሪያም ያገኛል» ቍ 9 - ማቴ 5÷6፤ ሮሜ 5÷5፤ 12÷6፤ 1ቆሮ 2÷12፤ 2ቆሮ 5÷5፤ 2ጴጥ 1÷3-4::
- ❖ ሕይወት፣ «የተትረፈረፈ» ቍ 10 - ዮሐ 1÷16፤ ሮሜ 6÷4፣23፤ 8÷2፣6፣11፤ 1ቆሮ 15÷45፤ ገላ 2÷20፤ ኤፌ 1÷7-8፤ 2ጢሞ 1÷10፤ 1ዮሐ 3÷14፤ 5÷11-13፤ ራእ 22÷1-2፣14፣17::
- ❖ ቤዛነት፣ «ሕይወቱን ስለ በጐቹ አሳልፎ ይሰጣል» ቍ 11 - ኢሳ 53÷3-6፤ ማቴ 20÷28፤ ሐሥ 20÷28፤ 2ቆሮ 5÷14-15፣21፤ ገላ 3÷13-14፤ ኤፌ 5÷25-27፤ 1ዮሐ 2÷2፤ 1ጴጥ 1÷18-19::
- ❖ ጥበቃ፣ ቍ 12-13 (በንጽጽር) - ሮሜ 8÷31-39፤ ዕብ 13÷5::

እዚህ ላይ በአጭሩ የተጠቀሱ ነገሮች ሊገመት የማይቻል ዋጋ ያላቸው ናቸው፤ ለመንፈሳዊ ሕይወታችንም ጠቃሚ ናቸው::

ኢየሱስ ስለ ራሱ ለመናገር ሁለት ምሳሌዎችን አቅርቧል፤ እነርሱም እረኛና በር ናቸው:: የአይሁድ መሪዎችን ለመግለጥ አራት ምሳሌዎችን አቅርቧል - ሌባ፣ ነጣቂ፣ እንግዳና ተቀጣሪ:: እነዚህ አራት

የአይሁድ ዐይነቶችን የሚወክሉ አይደለም:: ይልቁንም እያንዳንዱ የአንድን ባሕርይ የተለያዩ ገጽታዎች ነው የሚያመለክቱት:: እነዚህ አራት ነገሮች ሁሉንም ፈሪሳዊና ሰዱቃዊ የሚመለከቱ አይደለም:: ሆኖም፣ ከሞላ ጐደል የአንዳንዶቹ ዐይነተኛ መገለጫዎች ናቸው::

ኢየሱስ፣ «ከእኔ በፊት የመጡት» ሌቦችና ነጣቂዎች ነበሩ ብሏል:: ብዙ ቃላት በመጠቀም፣ «ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መጥፎዎች ናቸው» አላለም:: ያነጣጠረው ሌላ ማን ላይ ሊሆን ይችላል? መቼም፣ መጥምቁ ዮሐንስና አስቀድመው የነበሩ ነቢያት ሐሰተኛ እረኞች ነበሩ ማለቱ አይሆንም:: አሁን ያሉትና ያለፉት የአይሁድ መሪዎች ለአባባሉ ይመቻሉ:: በዚህ በዓል አይሁድ ኢየሱስን ለመግደል መፈለጋቸውን በግልጽ አሳይተዋል (7÷19፣25፤ 8÷59):: እርሱን ስለሚጠሉ ለራሱ መከላከል በማይችል በግ ላይ ጨካኞች ናቸው:: ምዕራፍ 5 ላይ ለአንካሳው ደንታ እንደሌላቸው ታይቷል፤ ምዕራፍ 9 ላይ ለዐይነ ስውሩ ደንታ እንደሌላቸው ታይቷል:: ሰንበት በመሻሩ አጉረመረሙ እንጂ፣ በመፈወሳቸው አልተደሰቱም:: በምንዝር ተያዘች የተባለችውን ሴት በተመለከተም ለሴትዮዋ ክብርና በጐነት ባለማሰብ ኢየሱስን ለማጥመድ ፈልገው ነበር:: ጥላቻ የሞላበት ሤራቸው ላይ ጥያቄ ለማቅረብ ድፍረት በነበራቸው የራሳቸው ሰዎች ላይ እንኳ ቍጣቸውን ገልጸዋል (ዮሐ 7÷46-52)::

የአይሁድ መሪዎችን በተመለከተ እነዚህ ባሕርያት አዲስ አልነበሩም:: የቀደሙ ነቢያትም በመጥፎ እረኝነታቸው መሪዎቻቸውን ነቅፈዋል (ኤር 23÷1-2፤ ሕዝ 34÷1-10):: በወቅቱ የነበሩትም ሆኑ ያለፉት መሪዎች፣ (ሀ) የእግዚአብሔርን ሰዎች በመናቅ፣ (ለ) አጉል ጥቅምን በመፈለግ፣ (ሐ) የፈለጉትን ለማግኘት ኹከት በመፍጠር፣ እና (መ) የተራቡትን ባለመመገብና የታመሙትን ባለመንከባከብ የታወቁ ነበሩ:: ስለዚህም ያኔ እንደ ነበረው ሁሉ አሁንም የፈራና የተበተነ መንጋ ተገኝቷል::



ሐሰተኛ እረኞች ለበጐቹ የማይጠነቀቁት ለምድንነው? የእነርሱ ባለመሆናቸውና ዋጋ የከፈሉባቸው ስላለሆኑ ነው:: ከመንጐቹ ጥቅም ለማግኘት በበጐቹ መሐል እንዳሉ ቅጥረኞች ናቸው:: ስለዚህ፣ አንድ ዐይነት ችግር ሲመጣ ጥለው ይሸሻሉ:: ዋጋ ያወጡባቸው ስላልሆኑም ራሳቸውን አይሰጡም:: ይህ በየዘመናቱ ሥር ሰዶ የኖረ ችግር ነው:: እነዚህ የሰቡትን በጐች የሚበሉ ቅጥረኛ ካህናት ናቸው፤ ችግርና ተቃውሞ ሲመጣ ትተው ወደ ሌላ የተሻለ ቦታ ይሄዳሉ:: ሕይወቱን ስለ በጐቹ ከሚሰጥና እኛም እንደዚያ እንድናደርግ ከሚጠራን መልካም እረኛ ጋር በፍጹም አይስተካከሉም (1ዮሐ 3÷16፤ 1ጴጥ 5÷2-3)::

ምስኪኖቹ በጎች የሚጠቁት በቅጥረኞች ብቻ ሳይሆን፣ በሚያደቡ ነጣቂዎች ጭምር ነው:: እነዚህ ከውጭ የሚመጡ ጠላቶች የሰይጣንና የሠራዊቱ ምሳሌዎች ናቸው:: ይሰርቃሉ፣ ይገድላሉ፣ ያጠፋሉ:: ሰይጣን በእነዚህ ነገሮች የሚወዳደረው የለም፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ በውስጥ በብልሹ መሪዎች፣ በውጭ ደግሞ በሰይጣናዊ ኀይላት ይጠቃሉ:: የሚገርመው ቅጥረኞች የተኩላዎችና የነጣቂዎችን ያህል ጉዳት ማድረሳቸው ነው:: ምናልባትም ወደ ኋላ ተመልሰን ዮሐንስ 8÷44ን ማየት ይኖርብናል:: ቅጥረኞች ከነጣቂዎቹ ጋር የተያያዙ ናቸው::

ዮሐ 10÷14-18

14መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጐቼን ዐውቃሁ፤
እነርሱም ያውቁኛል፤ 15ይህም አብ እኔን እንደሚያውቀኝ
እኔም አብን እንደማውቀው ነው:: ሕይወቴንም ስለ
በጐቼ አሳልፌ እሰጣለሁ:: 16ከዚህ ጉረኖ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱንም
ማምጣት አለብኝ:: እነርሱም ድምፄን ይሰማሉ፤ አንድ መንጋም ይሆናሉ፤ እረኛውም
አንድ:: 17መልሼ ለማንሣት ሕይወቴን አሳልፌ ስለምሰጥ አባቴ ይወደኛል:: 18ሕይወቴን
በራሴ ፈቃድ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፤ አሳልፌ ለመስጠትም
ሆነ ለማንሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህን ትእዛዝ የተቀበልሁትም ከአባቴ ነው::»

ምሳሌው ወደ መቋጨቱ ሲቃረብ ኢየሱስ በጣም በተለመዱ ርእሰ ጉዳዮች ላይ አጽንዖት ይሰጣል፤ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» (ከቍ. 11 ጋር ያነ)፣ «በጐቼን ዐውቃሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል» (ከቍ. 3 ጋር ያነ)፣ «ሕይወቴንም ስለ በጐቼ አሳልፌ እሰጣለሁ» (ከቍ. 11 ጋር ያነ):: ሆኖም፣ አዳዲስ ነገሮችም ተጨምረዋል:: በመጀመሪያ፣ በጐቹን ማወቁ ከአብ ጋር በተገናኘ እንደ ሆነ ኢየሱስ ይናገራል:: እርሱ፣ የአባቱ መንጋዎች ዋናው አለቃ ነው::

ሁለተኛ፣ መንጋዎቹ በወቅቱ እያደመጡት ከነበሩት ይበዛሉ:: ከዚያ ጉረኖ (አይሁድ) ኢየሱስ ያገኘው ትሩፋኑን - እውነተኛ በጐችን ብቻ ነበር (ኤር 23÷3፤ ሕዝ 34÷11-13):: በሌላ አነጋገር፣ አይሁድ ሁሉ የእግዚአብሔር መንጋዎች አይደሉም:: ከዚያ በኋላ ኢየሱስ በእምነት የእግዚአብሔር መንጋዎች ወደሚሆኑትና (ዘፍ 12÷3፤ መዝ 87÷4-6፤ ኢሳ 54÷2-3፤ 60÷3፤ ኢዮ 2÷28፤ ሚክ 4÷1-2፤ ሚል 1÷11፤ ኤፌ 1÷9-10፤ 3÷6) ከተለያዩ ሕዝቦች ወደሚመጡ በሌላ፣ «ጉረኖ» ወዳሉት ሊሄድ አለው (ለምሳሌ አሕዛብ፤ ከዮሐ 17÷20 እና ማቴ 28÷19 ጋር ያነ)::

በመጨረሻም፣ ኢየሱስ ስለ በጐቹ ሕይወቱን የሚሰጠው በፈቃደኝነትና ለጊዜው እንደሆነ እናነባለን:: ሌላ እረኛ መንጋውን ለማዳን እርሱ ራሱ በሕይወት መኖር አለበት:: እረኛው ከሞተ በጐቹ ይበተናሉ፤ ይጠፋሉ:: ኢየሱስ ሲሞት በደቀ መዛሙርቱ የሆነውም ይኸው ነበር:: እርሱ ግን ሕይወቱን እንደ ገና «ማንሣት» ስለቻለ መንጋው እንደ ገና ተሰብስቦአል::

**§ 101ለ**
**ኢየሱስን አስመልክቶ መለያታቸው**
**(ዮሐ 10÷19-21)**

19ከዚህም ቃል የተነሣ በአይሁድ መካከል እንደ ገና መለያየት ተፈጠረ:: 20ብዙዎቹም፣ «ጋኔን ያደረበት እብድ ነው ለምን ትሰሙታችሁ?» አሉ::



21ሌሎች ግን፣ «ይህ ጋኔን ያደረበት ሰው ንግግር አይደለም፤ ጋኔን የዐይነ ስውርን ዐይን መክፈት ይችላልን?» አሉ::

ኢየሱስን በተመለከተ እንደ ገና ተለያዩ (ዮሐ 6÷52፤ 7÷12፣30-31፣43፤ 8÷30፤ 9÷16):: ብዙዎች፣ «እብድ» (ጋኔን ያደረበት) ነው አሉ:: ዮሐንስ 7÷20 ላይ እንዲህ ካሉ ጀምሮ ሐሳባቸውን አልለወጡም (ከዮሐ 8÷48 ጋር ያነ):: ሌሎች ግን እብድ ሊሆን አይችልም አሉ:: ንግግሩ የእብድ አይደለም:: የተለመደ አይደለም፤ ሆኖም ከንቱ ንግግርም አይደለም:: የገዛ ራሳቸውን ጉልበት፣ ሥልጣንና አመክንዮ አዝለዋል:: ተግባሮቹም ቢሆኑ አጋንንት ያደሩበት ሰው አይደለም:: መሬት ላይ ወድቆ ሲንደባለልና ራሱን ሲያቆሽሽ አልታየም:: በምራቁ አፈሩን በመለወስ የዐይነ ስውሩን ዐይኖች ፈውሶአል:: ይህ ደግሞ የተለመደ ወይም አጋንንታዊ አይደለም:: ሌላው ቢቀር ይህን ሰው መስማት አለብን::

**§ 93**
**ሁሉም መከተል አይችሉም**
**(ማቴ 8÷19-22፤ ሉቃ 9÷57-62)[21]**

ማቴዎስ ይህን ኹነት የሚያስቀምጠው በመጀመሪያው የኢየሱስ አገልግሎት ዓመት፣ እንዲያውም ሐዋርያቱን ከመምረጡ በፊት ነው:: ሉቃስ ግን፣ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመራ፣ በሦስተኛው የአገልግሎት ዓመት መፈጸሙን ነው የሚያመለክተው:: በግልጽ የተቀመጠ ታሪክ በመሆኑ፣ ሁሌ የተፈጸመ ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ መምረጥ ይኖርብናል:: የምንከተለው የማቴዎስን አቀራረብ ነው? ወይስ የሉቃስን? ወይስ ሁለቱንም አንከተልም?[22]

---

[21] የቶማስና ገንድሪ ክፍል ቍጥር ብንከተልም፣ ኹነቶቹን ያስፈርነው የሉቃስን አቀራረብ በመከተል ነው::

[22] ይህ መጽሐፍ የሚከተለው የሉቃስን ነው:: አር.ሲ.ፎስተር የሚከተለው የማቴዎስን ነው:: ቶማስና ገንድሪ ሁለቱንም አይከተሉም::

የምንከተለው የማቴዎስን ከሆነ ሁለቱ ሰዎች ወደ ኢየሱስ የመጡት ከሕዝቡ መሸሽ በሞከረበት ጊዜ ነበር:: ባሕሩን ተሻግሮ ወደ ጌርጌሴኖን አካባቢ ሊሄድ ነው:: ሊከተሉት ፈልገው ነበር፤ እርሱ ግን፣ «አይሆንም» አላቸው:: የማቴዎስ ሁኔታዎች አቀማመጥ ከዐውዱ ጋር በሚገባ ይጣጣማል:: ለምን አብረውት እንዲሆኑ እንዳልፈለገም ያመለክታል:: ሌሎች ጀልባዎች ሊከተሉት ሰለ ሞከሩበት ሁኔታ ማርቆስ የጨመረውን ያብራራል (4÷36):: ይሁን እንጂ ማቴዎስ 8 እና 9 ወቅታዊውን ጉዳይ እንጂ ቅደም ተከተላዊ ነገሩን የተከተሉ አይደለም:: በተጨማሪም፣ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ቤት እንደሌለው እንዴት ይናገራል? ገና ከጴጥሮስ ቤት መውጣቱ ነበር (ማቴ 8÷14)፤ የራሱ ቤተ ሰቦችም ወደዚያ ከተማ ሳይዛወሩ አልቀረም (ዮሐ 2÷12)::

የሉቃስ ቅደም ተከተላዊ አቀማመጥ ይበልጥ ያመቻል:: የኢየሱስ አገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም ተሸጋግሮአል (ሉቃ 9÷51):: መንገድ ላይ በሰማርያ ተቃውሞ ገጥሞታል (ሉቃ 9÷52-56):: እዚያም በደረሰ ጊዜ አይሁድ ተቃውመውታል (ዮሐ 7-9):: እንዲያውም ሊገድሉት ፈልገው ነበር:: ያ ለዚህ ሁናቴ መድረኩን ያመቻቻል:: ኢየሱስን መከተል የሚፈልግ ሁሉ መወላወል የለበትም:: በአሁኑ ጊዜ ኀይለኛ ተቃውሞ ባለበት በይሁዳ ከስፍራ ስፍራ እየተንቀሳቀሰ እየሰበከ ነበር:: በእንዲህ ዐይነቱ ተቃውሞ በበዛበት አካባቢ አንድ ጸሐፊ ሊከተለው ፈለገ ማለቱ እንግዳ ነገር ይሆናል:: ሆኖም፣ ይህን አስገራሚ መምህር በተመለከተ የሐሳብ መከፋፈል ተፈጥሯል (ዮሐ 10÷21):: የዚህ ጸሐፊ ወላዋይ እምነት ውስጥ የነበረውን ትግል አጋልጧል::

**ሉቃ 9÷57-62**
**ማቴ 8÷19-22 ጋር**

57በመንገድ ሲሄዱም አንድ ሰው [የአይሁድ
ሃይማኖት መምህር[ማተ]] ቀርቦ፣ «[መምህር ሆይ[ማተ]]
ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ» አለው::



58ኢየሱስም፣ «ቀበሮዎች ጉድጓድ፣ የሰማይ
ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን እንኳ
የሚያስገባበት የለውም» አለው::
59ሌላውን ሰው ግን፣ [ደቀ መዝሙር[ማተ]] «ተከተለኝ» አለው:: ሰውዬውም፣
«ጌታ ሆይ፣ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን ልቀብር» አለው::
60ኢየሱስም፣ «[ተከተለኝ[ማተ]] ሙታን ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ተዋቸው፤
አንተ ግን ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ» አለው::
61ሌላ ሰው ደግሞ፣ «ጌታ ሆይ፣ መከተሉስ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን ሊመለስና
መጀመሪያ የቤቴን ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ» አለ::
62ኢየሱስ ግን፣ «ዕርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር
መንግሥት የተገባ አይደለም» አለው::

ከኢየሱስ የተነሳ የዳስ በዓል በተከበረበት ቦታ ከፍተኛ ኹከት ተነስቷል (ዮሐ 7-9):: አንዳንድ ሰዎች ወደውታል፤ ሌሎች ጠልተውታል (ዮሐ 10÷20):: በይሁዳ ለማገልገል ከተማውን ለቅቆ ሲወጣ ጥቂት ሰዎች ተከትለውት ነበር:: በተለይ ደግሞ ሦስት ግለሰቦች ኢየሱስን መከተል ፈልገዋል፤ ይሁንና ግን ቅድመ ሁኔታ በሚያስቀምጥ መልክ ነበር:: ኢየሱስ ግን የሦስቱንም ምክንያት ባለ መቀበል እነዚያ ደቀ መዛሙርት መሆን የፈለጉ ሰዎች ሁሉን ትተው እንዲከተሉ ጠየቃቸው::

መጀመሪያ የመጣው የሕግ መምህር፣ ምናልባትም ፈሪሳዊ ነበር:: ወደ ውስጥ መግባት የሚፈልግ የውጭ ሰው ነበር:: ከኢየሱስ ጋር የትም እንደሚሄድ ተናገረ:: ኢየሱስ ግን ደቀ መዝሙርነት እርሱ የለመደውን ምቾት እንደማያረጋግጥለት አሳሰበው:: ኢየሱስ እንዲህ ሲል ፍጹም ምስኪን ነበር ማለት ሳይሆን ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውር አገልግሎቱ ዋስትና ያለው ሕይወት ሊሰጠው እንደማይችል ማመልከቱ ነበር:: የሕግ መምህሩ ኢየሱስን ስለ መከተል አለመከተሉ የሚነግረን

የለም፤ ይሁን እንጂ እንዳልተከተለው ነው ጠንከር ባለ መልኩ የሚያመለክተው:: በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስን፣ «መምህር» በማለት ከጠሩት መካከል አንዱ እንኳ ሙሉ በሙሉ አልተከተለውም (ከ12÷38፤ 19÷16፣24፣36 ጋር ያነ)::[23] ሌላ ቦታም ቢሆን ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ኢየሱስን በተመለከተ ቅንነት እንዳልነበራቸው ነው የምናየው::

ሁለተኛው፣ ደቀ መዝሙሩ ነው:: የውስጥ ሰው ቢሆንም፣ ለጊዜው ወደ ውጭ መውጣት ፈልጓል:: ቀጠሮውን እስከ አባቱ ቀብር ቀን ድረስ ማዘግየት ይፈልጋል:: ምናልባትም ለሦስት ወሮች ያህል በሚቆየው የአባቱ ለቅሶ ወቅት እንዲገኝ እንዲፈቅድለት ኢየሱስን እየጠየቀ ይሆናል:: በጣም የሚገርመው ግን፣ አባቱ ገና ያልሞተ መሆኑ ነው:: የፓለስቲና የለቅሶ ወግ የሚፈጸመው በተሞተበት ቀን በመሆኑ፣ የዚህ ሰው አባት በእርግጥ ሞቶ ቢሆን ኖሮ ከኢየሱስ ጋር አይቆይም ነበር:: መፈጸም ያለባቸው የቀብር ሥርዐቶች ይኖሩ ነበር::[24] ስለዚህ የዚህ ሰው አባት ሞት አፋፍ ላይ ነበር፤ እርሱ ከሞተ በኋላ ግን ልጁ ኢየሱስን መከተል ይጀምራል:: «ሙታን ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ተዋቸው» የሚለው ሰወር ያለ የኢየሱስ ንግግር፣ ጨካኝ ስላቅ ሊመስል ይችላል፤ ይሁን እንጂ፣ «መንፈሳዊ ሙታን የለመዱትን እንዲያደርጉ ተዋቸው፤ አንተ ግን ልታደርገው የሚገባ የበለጠ ሥራ አለህ» ማለቱ ነበር ቢባል ይበልጥ ያስኬዳል::

---

[23] በማቴዎስ ወንጌል እውነተኛ አማኞች ኢየሱስን ጌታ በማለት ነበር የጠሩት (ማቴ 8÷2፣6፣8፣21፣25፤ 9÷28፤ 14÷28፣30፤ 15÷22፣25፣27፤ 16÷22፤ 17÷4፣15፤ 18÷21፤ 20÷30-31፣33፤ 26÷22):: ከዚህም በላይ ስለ መጪ ነገሮች እየተናገረ ካልሆነ በቀር በውጭ ካሉ ሰዎች ጋር ሲነጋገር ራሱን፣ «የሰው ልጅ» በማለት ነበር የሚጠራው (ማቴ 9÷6፤ 11÷19፤ 12÷8፣32፤ 16÷13):: J.D. Kingsbury, "On Following Jesus: The 'Eager' Scribe and the 'Reluctant' Disciple (Mt 8:18-22); *NTS* 34 (1988):45-59.

[24] አንዳንዶች እንደ ናዝራውያን ካህናት ሁሉ፣ ደቀ መዛሙርቱ የቀብር ሥርዓት ላይ እንዳይገኙ ኢየሱስ ተናግሮአል የሚል የተሳሳተ አመለካት አቅርበዋል (ዘሌ 21÷1-12፤ ዘኍ 6÷7)::



ቢ.አር.መኬን ለዚህ የተሰወረ የኢየሱስ አነጋገር ሌላ አሳማኝ መፍትሔ አቅርቧል::[25] ከቀብሩ አንድ ዓመት በኋላ አጥንቶ ብቻ እንጂ ሌላ ምንም በማይገኝበት ጊዜ የአይሁድ ቤተ ሰብ ወደ መቃብሩ ይገቡና አጥንቱን በመሰብሰብ የድንጋይ ሳጥን ውስጥ ያስቀምጡታል:: ስለሆነም ቤተ ሰቡ በሙሉ አንድ ላይ መቀበር ይችላል ማለት ነው:: ይህ ሁኔታ የለቅሶው ወራት ማብቂያ ሲሆን ከሥርግና ግርዘት ሥርዓት እስኪወዳደር ድረስ በጣም የተቀደሰ ነው (*Semahot* 12.5):: ስለሆነም፣ «ሙታን ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ተዋቸው» ማለት፣ «የድንጋዩ ሳጥን ውስጥ ያሉ አጥንቶች አጥንቶቹን ይሰብስቡ» ማለት ነው:: ያም ሆነ ይህ የኢየሱስ አነጋገር ጥልቅና ቀጥተኛ በመሆኑ አድማጮቹን ፈገግ አሰኝቶ፣ ሳያስገርም አልቀረም::

እዚህ ላይ ሦስተኛ ደቀ መዝሙር ይመጣል:: ቤተ ሰቦቹን ተሰናብቶ እንዲመለስ ፈቃድ እየጠየቀ ነው:: ሆኖም ኢየሱስ ቤተ ሰብን የሚያልፍ ሙሉ መሰጠት ሊኖር እንደሚገባ ተናግሮአል (ከማቴ 10÷37፤ ሉቃ 14÷26 ጋር ያነ):: ዕርፍ የያዘ ሰው ወደ ኋላ ዘወር ቢል ትልሙ ፈሩን እንደሚስት ማንኛውም ገበሬ ይገነዘባል:: ለሁለት ነገሮች መሰጠት ጉጂና የእግዚአብሔርን መንግሥት ፍሬያማነት እንደሚያሳጣው ማንኛውም መልካም ደቀ መዝሙር ይረዳል (ማቴ 6÷24)::

ዋስትና ከመፈለግም ይሁን ወይም በዓለማዊ ሥራ ወይም በቤተ ሰብ ትስስር ምክንያት እርሱን ላለመከተል የሚቀርብ ሰበብን ኢየሱስ አይቀበልም:: ኢየሱስ ቁጥር አንድ እንዲሆን አይፈልግም፤ እርሱ የሚፈልገው አንድ እርሱ ብቻ መሆንን ነው!

---

[25] B.R McCane, "'Let the Dead Bury Their Own Dead': Secondary Burial and Matt 8:21-22," *HTR* 83/1 (1990): 31-43.

**§ 102ሀ**
**«ሰባዎቹ» መሾም**
**(ሉቃ 10፥1-16)**

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን እንደ ላከ ሁሉ (ሉቃ 9፥1-6፤ ማቴ 10) አሁን ደግሞ ሰባ ሁለቱን ሊልክ ነው። እዚህ የምንመለከተው ሁሉ በማቴዎስ 10-11 ካለው ላይ ቃል በቃል የተወሰደ ነው። መቼታቸው ተመሳሳይ በመሆኑ፣ ሁለቱንም ሁኔታዎች ለመግለጽ አንድ ዓይነት ቃላት ተጠቅመዋል። ይሁን እንጂ ኤደርሼይም እንደሚለው (11፥38) ከዐሥራ ሁለቱ ዕድሜ ልክ አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር፣ የሰባዎቹ አገልግሎት ጊዜያዊ ነበር። ለዐሥራ ሁለቱ ከሰጠው ጋር ሲነጻጸር (ማቴ 10) ለሰባ ሁለቱ በሰጠው ተልዕኮ (ሉቃ 10) ላይ የጐደለ ነገር መኖሩን ስናስተውል ይህ ግልጽ ይሆንልናል።

የዳስ በዓል በሚከበርበት ወቅት፣ ኢየሱስ ላለፉት ስድስት ወሮች በመገለል ባሳለፈው ጊዜ ያጣውን ታዋቂነት መልሶ አግኝቷል (ዮሐ 7፥31፣40-41፣45-51፤ 9፥16፣38፤ 10፥21)። ይህም እነዚያ ዝግጁ የሰባኪዎች ሰራዊት፣ ከዓመት በፊት ዐሥራ ሁለቱ በገሊላ ያደረጉትን፣ እነርሱም በይሁዳ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ኢየሱስ በይሁዳ አካባቢ ሊያገለግል ነው። እነዚህ ሰዎች ቀድመው በመሄድ ለእርሱ መምጣት በየመንደሩና በየከተሞቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነበረባቸው።

**ሉቃ 10፥1-4**

1 ከዚህ በኋላ ጌታ ሌሎች ሰባ ሁለት ሰዎችን
መርጦ ሾመ፤ ወደሚሄድበትም ከተማና ቦታ ሁሉ
እንዲቀድሙት፣ ሁለት ሁለት አድርጎ ላካቸው፤ 2 እንዲህም
አላቸው፤ «መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው፤ ስለዚህ የመከሩ ጌታ
ሠራተኞችን ወደ መከሩ ቦታ እንዲልክ ለምኑት። 3 እንግዲህ ሂዱ፤ እንደ በጎች
በተኲላዎች መካከል እልካችኋለሁ። 4 ኮረጆ ወይም ከረጢት፣ ወይም ጫማ አትያዙ፤
በመንገድ ላይም ለማንም ሰላምታ አትስጡ።



ኢየሱስ እርሱን መከተል የሚችሉ ሦስት ሰዎችን አሰናብቶ ነበር (ሉቃ 9፥57-62)። የየራሳቸው ሰበብ ስለ ነበራቸው ለደቀ መዝሙርነት ተገቢ ሆነው አልተገኙም። ኢየሱስን መከተል አዳጋች ነው ብለን ስናስብ ተግዳሮትን ሁሉ ለመቋቋም የተዘጋጁ ሰባ ሁለት ሰዎች አገኘን። ያልተከፋፈለ ታማኝነታቸውን ሊሰጡት ተዘጋጅተዋል።

ሰባ ወይም ሰባ ሁለት ብንል ሁለቱንም የሚደግፍ አሳማኝ ቅጂ አለ። በጣም የሚገርመው ደግሞ የአይሁድ ሸንጎ አባላት ቍጥር ስንት እንደ ነበረም ግራ የሚያጋባ መሆኑ ነው። አንዳንዶች ሰባ ሲሉ ሌሎች ሰባ ሁለት ይላሉ። ምናልባትም እነዚያ የሰባኪዎች ቡድን በተለያየ መልኩ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥልጣንና ሕግ መወሰኛ አካል የሚወክሉ እንደ ነበር ያመለክታል (ከዘኍ 11፥16 ጋር ያነ)። እንዲህ ማለት ግን የተላኩት ሰባኪዎች ቍጥር በትክክል ይህ አይደለም ማለት አይደለም። ይልቁንም፣ ቀደም ሲል ዐሥራ ሁለቱ እንደ ነበሩት ሁሉ እነዚያ በየቦታቸው የሚዘዋወሩ ሰባኪዎች መደበኛ የኢየሱስ ተወካዮች ነበሩ ማለት ነው።[26]

እንደ ዐሥራ ሁለቱ ሁሉ ሰባዎቹም የተላኩት፣ (1) ሁለት ሁለት ሆነው ነበር (ከማር 6፥7፤ ሉቃ 7፥18-19፤ ሐሥ 13፥2፤ 15፥27፣39-40፤ 17፥14፤ 19፥22 ጋር ያነ)፤ (2) ከኢየሱስ ወደ ቦታው መምጣት በፊት ነበር የተላኩት፤ (3) በተኩላዎች መሐል እንደ በጐች[27] ነበር፤ (4) ምንም ትርፍ ነገር መያዝ አልነበረባቸውም፤ (5) ከቤት ወደ

[26] ሊፌልድ ዘፍጥረት 10 ላይ የቅጂ ልዩነት መኖሩን አስተውሏል። የማስሬቱ ቅጂ (MT) ሰባ ሕዝቦች ሲል የሰብዓ ሊቃናት ግን ሰባ ሁለት ይላል። ስለሆነም ይህ የወንጌላውያኑ ቍጥር ከሕዝቦቹ ቍጥር ጋር የተያያዘ መሆኑን ያመለክት ይሆናል። ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት እያንዳንዱን የአይሁድ ነገድ እንደሚወክሉ ሁሉ ሰባ ሁለቱም በወቅቱ ይታወቁ የነበሩ እያንዳንዱን ሕዝብ ይወክላሉ። እርግጥ ነው፣ ይህ ከቍጥሩ ጋር ቢጣጣምም፣ ለዚህ ዐውድ ግን እንግዳ ነው። ድነት ለአሕዛብ እየደረሰ ነው ብሎ ለመናገር ትንሽ መቸኰል ይመስላል።

[27] ማቴ 10፥16፣ «በጐች» ይላል። ከማቴዎስ ይልቅ ሉቃስ ያልተመጣጠነ ምስል ያቀርባል።

ቤት በመዘዋወር ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን፣ የሚደረግላቸውን መስተንግዶ ለመቀበል ነበር፤ (6) ቤቶችን በሰላም መባረክ ወይም የእግራቸውን ትቢያ በማራገፍ መራገም ነበረባቸው፤ (7) ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኀይል ተሰጥቷቸው ነበር (ከሉቃ 10÷17-19፤ ማቴ 10÷1፣8 ጋር ያነ)። የእግዚአብሔር መንግሥት/መንግሥተ ሰማይ መቅረቧን ማወጅ ነበረባቸው። እነዚህ ተጨማሪ ተመሳሳይነቶች እንደ ዐሥራዎቹ ሁሉ ሰባ ሁለቱም ሥልጣን እንደ ነበራቸው ያመለክታሉ። እነዚህን ሰዎች በበዓሉ መጨረሻ ኢየሱስ ፊት ለፊት ከተጋፈጣቸውና የሚናገሩትን ካሳጣቸው የአየሁድ መማክርት ጋር አለማወዳደር ለይሁዳ ነዋሪዎች ቀላል አልነበረም።

ጒዞዋቸው ጓዝ ያላበዛና ፈጣን መሆን ነበረበት። ኢየሱስ ትርፍ ነገር እንዳይዙ፣ ሌላው ቀርቶ መንገድ ላይ ለሰዎች ሰላምታ እንዳይሰጡ እንኳ አዞአቸዋል (ከ2ነገ 4÷29 ጋር ያነ)። የምሥራቃውያን ሰላምታ ራሱን የቻለ ወግ ያለውና ጊዜ አባካኝ ነበር። መንገድ ላይ የሚያገኟቸውን ሰዎች ዝም ብለው መሄዳቸው ጨዋነት የጐደለው ሊመስል ይችላል። ይሁን እንጂ በአጭር አነጋገር በየመንገዱና በየአደባባዩ የሚያባክኑት ጊዜ አልነበራቸውም። በዳስ በዓልና በመቅደስ ምረቃ በዓል መካከል ያሉት ሁለት ወሮች ብቻ ነበሩ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ኢየሱስ ሰፊውን የይሁዳ አውራጃ ማዳረስ ነበረበት። ስለሆነም፣ ኢየሱስና ዐሥራ ሁለቱ በገሊላ የፈጸሙትን፣ ሰባ ሁለቱ በይሁዳ ለመፈጸም መጣደፍ ነበረባቸው።

[ቍጥር 2 = ማቴ 9÷37-38፣ የ§ 70ሀ ማብ ይመ]

[ቍጥር 3 = ማቴ 10÷16፣ የ§ 70ለ ማብ ይመ]

[ቍጥር 4 = ማቴ 10÷9-10፣ የ§ 70ለ ማብ ይመ]



5ወደ ማንኛውም ቤት ስትገቡ አስቀድማችሁ፣
ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ፤ 6የሰላም ሰው በዚያ ካለ፣ ሉቃ 10÷5-8
ሰላማችሁ ያርፍበታል፤ አለዚያም ሰላማችሁ ለእናንተው
ይመለሳል። 7ያቀረቡላችሁን ሁሉ እየበላችሁና እየጠጣችሁ በዚያ ቤት ተቀመጡ፤
የሚሠራ ይመጠዝ ማግኘት ይገባዋልና። ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት አትዘዋወሩ።
8ወደ ማንኛውም ከተማ ስትገቡ ሰዎቹ ከተቀበሏችሁ፣ ያቀረቡላችሁን ብሉ።»

ይህ «የሰላም» ቡራኬ [ዕብ፣ ሻሎም] የተለመደ የአይሁድ ሰላምታ ነበር፤ ሆኖም፣ «ታዲያስ፣ እንደምነህ?» ከማለት የጠለቀ ትርጒም አለው። ስለ ሰውየው ሁለንተና አስመልክቶ ጸሎት የማቅረብ ያህል ነበር። ከማቴዎስ 10÷12-13 እንደ ተመለከትነው ሐዋርያቱ የመስበክ፣ የመፈወስና ይህ የመባረክ ውክልና ከኢየሱስ ተሰጥቷቸው ነበር። በተመሳሳይ መልኩ ሰባቱ ሁለቱም እንደ የኢየሱስ ተወካዮች የእርሱ ወደ አብ የመቅረብ መብት ነበራቸው። አንድን ቤት በ«ሰላም» መባረክ፣ ለዚያ ቤት መልካም እንዲሆን የመጸለይ ያህል ነበር። በተመሳሳይ መንገድ ቀጥሎ እንደምንመለከተው የእግራቸውን ትቢያ በማራገፍ አንድን ከተማ ከረገሙ፣ ሁናቴው እንዲሁ ምልክት ብቻ አይደለም። ያንን ከተማ መርገማቸው ነበር።

ቍጥር 7-8 ያለው መመሪያ ወላጆች ልጆቻቸውን የቀረበላቸውን ሁሉ እንዲመገቡ የሚሰጡት ትእዛዝ ዐይነት አልነበረም። ይልቁንም፣ እነዚህ ለተልዕኮ የወጡ ሰባኪዎች ከሌላው ሰው ገበታ ለመመገብ ዕፍረት ሊሶማቸው አይገባም ማለት ነው። ለሰበኩት ስበከት የሚገባ ዋጋ ነው (ከ1ቆሮ 9÷3-18፤ 3ዮሐ 5-8 ጋር ያነ)።

[ቍጥር 5-8 = ማቴ 10-13 የ§ 70ለ ማብ ይመ]

**ሉቃ 10፥9-12**

[9]በዚያ የሚገኙትን በሽተኞች እየፈወሳችሁ፤
'የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች'
በሏቸው። [10]ነገር ግን ወደ አንድ ከተማ ገብታችሁ
ካልተቀበሏችሁ፣ ወደ አደባባዩ ውጡና እንዲህ በሉ፤
[11]በእግራችን ላይ ያለውን የከተማችሁን ትቢያ እንኳ እናራግፍላችኋለን፤ ነገር ግን
የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ቀረበች ይህን ዕወቁ። [12]እላችኋለሁ፤ በዚያን ዕለት
ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ቀላል ይሆንላታል።

«የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች» የሚለውን ለሚቀበሉም ሆነ ለማይቀበሉ መልእክቱ አንድ ነው። አንድ ሰባኪ የሚደረግለት አቀባበል መልእክቱን ሊለውጥ አይገባም። በተጨማሪም «ቀርባለች» የሚለው ግሥ በአሁን ጊዜ ነው የተቀመጠው። ያ ማለት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት አሁኑኑ ቀርባለች ማለት ነው! ይህም ቁጥር 12ን የበለጠ አስፈሪ ያደርገዋል። ክርስቶስን ችላ የምትሉ ከሆነ ገሃነም ይጠብቃችኋል (ከሮሜ 9፥29፤ 2ጴጥ 2፥6፤ ይሁዳ 7 ጋር ያነ)።

[ቁጥር 9 = ማቴ 10፥7-8፣ የ§ 70ለ ማብ ይመ]

[ቁጥር 10-12 = ማቴ 10፥14-15፣ የ§ 70ለ ማብ ይመ]

**ሉቃ 10፥13-16**

[13]«ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ!
በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጉ
ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብሰው ዐመድ ነስንሰው
ንስሐ በገቡ ነበር። [14]ነገር ግን በፍርድ ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና
ይቀልላቸዋል። [15]አንቺም ቅፍርናሆም፣ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ልትዪን? ወደ ሲኦል
ትወርጃለሽ።
[16]እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤ እናንተን የማይቀበል እኔን አይቀበልም፤
እኔንም የማይቀበል የላከኝን አይቀበልም።»



በይሁዳ በነበረ ጊዜ ኮራዚን፣ ቤተ ሳይዳንና ቅፍርናሆምን ማንሳቱ ያለቦታው ይመስላል። ይህን የኢየሱስ አነጋገር ሉቃስ እዚህ ላይ ያስገባው ቁጥር 12 ላይ ሰዶም ከተነሳችበት ሁኔታ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም። ያም ሆኖ ግን ምን ማለት እንደ ነበር ማንም አያስተውልም። ኢየሱስ ታላላቅ ተአምራቱን በእነዚህ የእስራኤል ጠላቶች መሐል አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ንስሐ ይገቡ ነበር። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ የእግዚአብሔርን መልእክተኛ መቃወማቸውን ቀጥለዋል።

[ቁጥር 13-15 = ማቴ 11፥21-23፣ የ§ 58 ማብ ይመ]

[ቁጥር 16 = ማቴ 10፥40፣ የ§ 70ለ ማብ ይመ]

**§ 102ለ**
**የ«ሰባዎቹ» መመለስ**
**(ሉቃ 10፥17-24)**

[17]ሰባ ሁለቱም ደስ እያላቸው ተመልሰው፣ «ጌታ
ሆይ፤ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዙልን» አሉት።
[18]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ሰይጣን እንደ
መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። [19]እንግዲህ እባቡንና
ጊንጡን እንድትረግጡ፣ በጠላትም ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤
የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም። [20]ይሁን እንጂ መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚያ
ደስ አይበላችሁ፤ ስማችሁ ግን በሰማይ ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።»

ለ«ሰባዎቹ» ጉዞው አስደሳች ነበር። ሕዝቡን ለመርዳት የኢየሱስ ኀይል በእነርሱ በኩል ማለፉ እንዳስደሰታቸው ግልጽ ነበር። ኢየሱስም ቢሆን በዚህ ደስ ተሰኝቷል። ኢየሱስ የተደረገውን ፈውስና፣ የተገለጠውን ኀይል እየተቀባበሉ ሲነግሩት ከሰባ ሁለቱ ጋር አብሮ ሳይስቅ አልቀረም። ኢየሱስ ይህን ሁሉ የሚያየው ከተለየ አቅጣጫ

ነበር::[28] መንፈሳዊ ዐይኑ የሰይጣንን መውደቅ ማየት ችሏል (ከኢሳ 14÷4-11፤ ራእ 12÷9 ጋር ያነ):: እንደ መብረቅ ነበር:: ይህ ሰይጣን በከፍተኛ ፍጥነት እንደ ወደቀ የሚያመለክት ይሆን? ወይስ አወዳደቁ እንደ ነበልባል ነበር ማለት ነው? ይበልጥ ግን የሰይጣን ውድቀት በሁሉም ቦታ ታይቷል ማለት ሊሆን ይችላል:: «ዐየሁ» የሚለው ግሥ ቁርጥ ያለ ጊዜን የሚያመለክት አይደለም:: ኢየሱስ የሰይጣንን መውደቅ «እያየ» እንደ ነበር ነው የሚያመለክተው:: ኢየሱስ ሰይጣን በስፍራ ሁሉ ሲወድቅ አየ:: የኢየሱስ መመለስ ከመብረቅ ጋር የተመሳሰለው በዚህ መልኩ ነበር (ማቴ 24÷27፤ ሉቃ 17÷24)::

እንደ ማርቆስ 16÷18 (ጭቅጭቅ የበዛበት) ቍጥር 19 ልዩ ስለሆኑ ኀይላት ይጠቅሳል:: እባብና ጊንጡን የመርገጥ ችሎታ ለገጠር መንገደኞች እንጂ በከተማ ለሚመላለሱ ሰባኪዎች ይህን ያህል ጠቃሚ አይመስልም:: ይህን ችሎታ በምሳሌያዊ መልኩ መረዳት ይበልጥ ምክንያታዊ ይሆናል:: እባብና ጊንጥ እነዚህ ሰዎች ያስወጧቸውን አጋንንት ይወክላሉ (ከዘፍ 3÷15 ጋር ያነ):: በመሠረቱ፣ ዐውዱ የሚናገረው አጋንንታዊ ኀይላት ላይ ድል ስለ መቀዳጀት እንጂ ስለ ተፈጥሮአዊ ኀይላት አይደለም:: ያም ሆኖ ግን ኢየሱስ ታላላቅ በረከቶቻቸውን እንዲያደንቁ ነበር የነገራቸው:: ከድነት አንጻር ስናያቸው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኀይላት ያላቸው ፋይዳ ይደበዝዛል::

ሉቃ 10÷21-22

[21]በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት
አድርጎ እንዲህ አለ፤ «የሰማይና የምድር ጌታ፤ አባት

---

[28] J.V. Hills, "Luke 10:18 - Who Saw Satan Fall?" *JSNT* 46 (1992): 25-40, እንደሚያመለክተው *etheoroun* የሚለው፣ «አየሁ» ሳይሆን፣ «አዩ» ተብሎ መተርጐም አለበት:: ስለዚህም ሰይጣን ሲወድቅ ያየው ኢየሱስ ሳይሆን፣ ቍ 17 ላይ የተጠቀሱት አጋንንት መሪያቸው ሲወድቅ አዩ ማለት ይሆናል:: ስለሆነም፣ አጋንንት በማስወጣት ረገድ ስላገኙት ውጤት ሲነግሩት ኢየሱስ የሰጠው መልስ፣ መሪያቸው ሰይጣን ሲወድቅ ስላዩ አጋንንት ለደቀ መዛሙርት መገዛታቸውን የሚያመለክት ይሆናል ማለት ነው::



ሆይ፣ ይህን ሁሉ ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው
አመሰግንሃለሁ፤ አዎን፣ አባት ሆይ፤ ይህ የአንተ በጎ ፈቃድ ሆኖአልና::
[22]ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ደግሞም ወልድ ማን እንደ ሆነ ከአብ
በቀር የሚያውቅ የለም፤ አብ ማን እንደ ሆነም ከወልድ በቀር፣ ወልድም ሊገልጥለት
ከሚፈቅደው በቀር የሚያውቅ የለም::»

ይህ መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ ሐሤት እንደ ሰጠው የሚያመለክት የተለየ ዐረፍተ ነገር ነው:: ማቴዎስ ይህን አላሰፈረም:: በይበልጥ ግራ የሚያጋባው ደግሞ፣ ይህን ሉቃስ ላይ ያለውን፣ «ቅዱስ» የሚለውን ቃል የሚገድፉ ቅጂዎች መኖራቸው ነው:: ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ሉቃስ ውስጥ በተደጋጋሚ የምንመለከተው ዐቢይ ሐሳብ ነው:: ማቴዎስ ያላሰፈረውን ይህን አባባል ሉቃስ መጨመሩ በጣም የሚያስገርም ሊሆን አይችልም:: ኢየሱስ ይኖር የነበረው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተሟላ ኅብረት በማድረግ ነበር (ሉቃ 4÷14፤ ዮሐ 3÷34)::

[ቍጥር 21-22 = ማቴ 11÷25-27፣ የ§ 58 ማብ ይመ]

ሉቃ 10÷23-24

[23]ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ ለብቻቸው
እንዲህ አላቸው፤ «እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዐይኖች
ብፁዓን ናቸው፤ [24]እላችኋለሁና፤ ብዙ ነቢያትና ነገሥታት
እናንተ የምታዩትን ለማየት ፈልገው አላዩም፤
የምትሰሙትንም ለመስማት ፈልገው አልሰሙም::»

እነዚህ ጥቅሶች በምሳሌ ከተሰጠው ስብከት የተወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ:: ማቴዎስ በግል ዐሥራ ሁለቱን ማስልጠን ላይ በነበረ ጊዜ የተናገረው መሆኑን ነው የሚነግረን (ማቴ 13÷10፤ ማር 4÷10):: በሌላ በኩል ደግሞ ሉቃስ ሰባ ሁለቱን እያሰለጠነ በነበረ ጊዜ የተናገረው መሆኑን ይናገራል:: እንደ ገና ኢየሱስ ለእነዚህ ሰዎች የሰጠውን የተለየ መብት እንመለከታለን::

ሉቃስ እነዚህን አባባሎች ከሌላው ወስዷል ማለት የተረጋገጡ አይደለም ማለት አይደለም:: የዐይን ምስክሮችን መሠረት በማድረግ ይጽፍ የነበረው ሉቃስ አጠር ባለ መልክ ሲያስቀምጠው ማቴዎስ በሌላ ኹነት የተጠቀመበትንም ጥቅስ ወስዷል::

[ቊጥር 23-24 = ማቴ 13÷16-17፣ የ§ 64ለ ማብ ይመ]

**§ 103**
**ደጉ ሳምራዊ**
**(ሉቃ 10÷25-37)**

ይህ ከተነገሩ ታላላቅ ታሪኮች መካከል አንዱ ነው::[29] አንድ የሕግ መምህር የዘላለም ሕይወትን በተመለከተ ነገረ መለኮታዊ ይዘት ያለው የተወሳሰበ ጥያቄ በማቅረብ ኢየሱስን ፈተነው:: ኢየሱስ ግን እዚህና አሁን ስላለው ሕይወት ቀላል ታሪክ በማቅረብ የሰውየውን አቋም የሚንድ መልስ ሰጠ:: ከዚህ ታሪክ፣ ሦስት የሕይወት ፍልስፍናዎችን እንመለከታለን:: ሌቦች ከራስ ወዳድነት በመነሣት፣«ያንተ የሆነው፣ የእኔ ነው» ይላሉ:: የሃይማኖት መሪዎቹ፣ «የእኔ የሆነው፣ የእኔ ነው» ይላሉ:: ይህ ሳምራዊ ግን፣ «የእኔ የሆነው፣ የአንተም ነው» አለ:: የዘላለምን ሕይወት መውረስ የሚገባው እርሱ ብቻ ነው:: ያደረገውን ሳይሆን፣ ሆኖ መገኘትን ግምት ውስጥ ያስገባ ጉዳይ ነበር::

**ሉቃ 10÷25-29**

25እነሆም አንድ ቀን፣ አንድ ሕግ ዐዋቂ ኢየሱስን ሊፈትነው ተነሥቶ፣ «መምህር ሆይ፣ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?» አለው::

26ኢየሱስም፣ «በሕግ የተጻፈው ምንድን ነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?» ሲል መለሰለት::

27ሰውየውም መልሶ፣ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህና በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ ይላል» አለው::

28ኢየሱስም፣ «በትክክል መልሰሃል፤ አንተም እንደዚሁ አድርግ፤ በሕይወት ትኖራለህ» አለው::

29ሰውየውም፣ ራሱን ጻድቅ ለማድረግ ፈልጎ፣ «ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?» አለው::

[29] F.S. Spencer, "2Chronicles 28:5-15 and the Parable of the Good Samaritan," *WTJ* 46 (1984): 317-349 ላይ ይህ ታሪክ በ2ዜና 28÷5-15 ያለውን መሠረት ያደረገ ነው የሚል አሳማኝ ምክንያት አቅርቧል::



በገሊላ ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ከመጡ ሕግ ዐዋቂዎች ጋር ተከራክሯል:: እዚህ በይሁዳ ደግሞ እያንዳንዱ እንቅስቃሴውን በዐይነ ቁራኛ ይከታተሉ ነበር:: ይህ ሰው ሰላይ መሆን አለመሆኑን አናውቅም፤ ሆኖም በጣም ተጠራጣሪ ይመስላል:: የመጣው ለኢየሱስ ጥያቄ ለማቅረብ ነበር:: ከጥያቄነቱ ይልቅ ለማጥመጃነት የታሰበ ፈተና ይመስላል (*ekpeirazo*):: ጥያቄው ምክንያታዊና ጠቃሚ ቢሆንም ቀላል አልነበረም:: በመቶዎች የሚቈጠሩ የብሉይ ኪዳን ሕጐች፣ በሺዎች የሚቈጠሩ ወጐችና ሥርዐቶች በነበሩበት ሁኔታ አንድ ሰው የዘላለም ሕይወት ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑትን እንዴት ማወቅ ይችላል? አረሙን ከስንዴው መሓል ነቅሎ ማውጣት ሁልጊዜ ቀላል አይደለም::

ኢየሱስ ሰዎችን የሚረዳበት ሁኔታ እንዴት ግሩም ነው! ይህ ሕግ ዐዋቂ ከመስማት ይልቅ ለመናገር መምጣቱን ዐውቆአል:: ስለዚህም በሙያው መሠረት ሕጉን እንዲተረጉም ጠየቀው: በመሠረቱ፣ ይህ የኖረበት ሙያ መስክ ነበር:: መልሱ እጅግ በጣም ጥሩ ነበር! ኢየሱስም ቢሆን የሚለው ይህንኑ ነበር (ከማቴ 22÷37-40፤ ማር 12÷29-31 ጋር ያነ):: የእግዚአብሔር ልጅ መሆን በዚህ ይጠቃለላል:- እግዚአብሔርን መውደድ ልጆቹንም መውደድ ነው::

የመጀመሪያውና ታላቁ ትእዛዝ አይሁድ ሼማ (Shema) የሚሉት ነው:: ይህ የሚገኘው ዘዳግም 6÷5 ላይ ሲሆን፣ እግዚአብሔርን በሦስት

ነገሮች መውደድ እንደሚገባ ያመለክታል፤ ልብ፣ ነፍስና፣ «ሁሉም ነገር»:: ሆኖም፣ ዕብራይስጡ፣ «ሁሉም ነገር» [moed]፣ ለሚለው ግሪኩ አቻ ትርጒም ስለሌለው ከአንድ ቃል ይልቅ፣ ኀይልና ሐሳብ በተሰኙ ሁለት ቃላት ተጠቅሟል:: ስለሆነም፣ በልባችን፣ በነፍሳችን፣ በኀይላችንና በሐሳባችን ሁሉ እግዚአብሔርን መውደድ ይኖርብናል::

ሁለተኛው ትእዛዝ ከዘሌዋውያን 19÷18 ላይ ያረፈው ሲሆን፣ የመጀመሪያውን ለመረዳትም በጣም አስፈላጊ ነው:: ፍቅራችንን ለእግዚአብሔር የምናሳየው እንዴት ነው? እርግጥ ነው፣ አንዳንድ የምንፈጽማቸው ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ይኖራሉ:: ሆኖም፣ በባዶነት ስሜት ልናደርጋቸው እንችላለን:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን ሳንወድ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፣ ስጦታ ማቅረብ፣ ወዘተ እንችላለን:: እግዚአብሔርን እንደምንወድ የምናሳይበት ብቸኛው ተግባራዊ መንገድ ባልንጀራችንን በመውደድ ነው (ከ1ዮሐ 4÷20-21 ጋር ያነ)::[30]

ኢየሱስ በጥሩ ሁኔታ መልስ በመስጠቱ ሕግ ዐዋቂውን አደነቀ:: ሆኖም፣ «ትክክል የሆነውን ዐውቀሃል፤ አሁን ግን ሥራ ላይ አውለው» በማለት በጨዋነት ነገረው:: ይህ ሕግ ዐዋቂ ፈጣን አእምሮ ነበረው:: ኢየሱስ፣ «መልስህ ትክክል ነው፤ ምግባርህ ግን መስተካከል ይኖርበታል» ማለቱ እንደ ነበር ወዲያውኑ ነበር የተረዳው:: ንስሐ ከመግባት ይልቅ ማንኛውም ግብዝ እንደሚያደርገው ራሱን ለማጽደቅ ሞከረ:: ራስን ማጽደቅ ግን ሕጉ ከሚጠይቀው ጒድሎ መገኘት ነው:: ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት መኖር ስለማይቻል፣ አሳንሰነው ለእኛ እንዲመጥን ልናደርገው ነው ማለት ነው:: ሕጉን ምክንያታዊ

30 J.Piper, "Is Self-Love Bibllical?" *CT* 21 (1977): 1150-1153 ላይ እንደሚያመለክተው፣ ይህ ክፍል በዘመናችን ተወዳጅ እየሆነ ስለ መጣውና ጤናማ ራስን ማክበር ስለ ተሰኘው ጒዳይ የሚለው የለም:: እንዲያውም፣ የቀድሞው ስሕተት ሌሎችን በጥቂቱ መውደድ ሲሆን፣ የዘመናችን ስሕተት ግን አብዝቶ ራስን መውደድ እንደ ሆነ ነው ያመለከተው::



ለማድረግ፣ ለማሻሻል፣ የራሳችንን ገለጻ ለመስጠትና ራሳችንን ለማጽደቅ የምንሞክር ከሆነ ምናልባት ዕድል ይኖረናል:: ሕጉ የሚጠይቀውን በጣም ካጠበብሁት፣ ባልንጀራዬን እወዳለሁ ማለት እችላለሁ:: «ባልንጀራዬ ማነው?» የሚለው ጥያቄ ከዚሁ አንጻር የቀረበ ነበር:: የዚህ ምሳሌ ትልቅነት፣ «የባልንጀርነትን» ትርጒም ይህ ሕግ ዐዋቂ ወይም አብዛኞቻችን ከምናስበው በላይ ያሰፋው መሆኑ ነው::

[30]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መልስ ሰጠው፤ «አንድ
ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ በወንበዴዎች ሉቃ 10÷30-35
እጅ ወደቀ፤ ልብሱንም ገፈው ደበደቡት፤ በሞት አፋፍ
ላይ ጥለውት ሄዱ:: [31]አንድ ካህን በአጋጣሚ በዚያው መንገድ ቁልቁል ሲወርድ
አየውና ገለል ብሎ አለፈ:: [32]ደግሞም አንድ ሌዋዊ እዚያ ቦታ ሲደርስ አየውና እርሱም
ገለል ብሎ አለፈ:: [33]አንድ ሳምራዊ ግን እግረ መንገዱን ሲሄድ ሰውየው ወዳለበት
ቦታ ደረሰ፤ ባየውም ጊዜ ዐዘነለት፤ [34]ቀርቦም ቍስሎቹ ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ
አፍስሶ አሰረለት፤ በራሱም አህያ ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማረፊያ ቤት
ወሰደው፤ በዚያም ተንከባከበው:: [35]በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለማረፊያ ቤቱ
ባለቤት ሰጠና፣ «ይህን ሰው ዐደራ አስታምመው፤ ከዚህ በላይ የምታወጣውንም ወጪ
እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ» አለው::

ቍጥር 30 [*hypolabon*] በሚል ዋነኛ ቃል ይጀምራል፤ አዲሱ መደበኛ ትርጒም ግን ሳይተረጒም አልፎታል:: በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ ኢየሱስ፣ ከሰውየው ጋር ክርክር፣ «አነሣ» ማለት ነው:: ሽፍንፍኑ ተነሥቶ ቀጥሎአል፤ ኢየሱስን ግን በክርክር አንሥቶታል:: ይህ ምሳሌ «ባልንጀራዬ ማነው?» በማለት ሕግ ዐዋቂው ላቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ ሳይሆን «እድን ዘንድ ምን ላድርግ?» ለሚለው የመጀመሪያው ጥያቄ የተሰጠ መልስ ነው::

ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ የሚወስደው መንገድ አደገኛ ነበር:: ለመደበቂያ የሚሆን ጠመዝማዛ ቦታ፣ ዋሻና ገደላ ገደል የሞላበት ስለ

ነበር ዘራፊዎች ይወዱታል:: አዱሚም በሚል መጠሪያም ይታወቅ የነበረ ሲሆን፣ (ኢያ 15÷7፤ 18÷17) ይህም፣ «የደም መተላለፊያ» ማለት ነው:: ስለዚህም መንገደኛው መደብደቡና በሞትና በሕይወት መካከል መጣሉን መስማት የሚገርም አልነበረም::

በዚህ መንገድ ያለፉ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች ካህናት ነበሩ:: የካህናት ተቀዳሚ ሥራ መቅደሱ ውስጥ የመሥዋዕቱን ሥርዐት መፈጸም ነው:: በሌላ በኩል ሌዋውያን መቅደሱንና በውስጡ የነበረውን አገልግሎት ያስፈጽሙ ነበር:: አገልግሎት ላይ በሚሆኑበት በዓመቱ አራት ሳምንቶች በሥርዓቱ መሠረት ንጹሕ መሆን ነበረባቸው:: ሰውየው የሞተ ይመስል ነበር:: የሞተ ሰው መንካት የተቀደሰ አገልግሎታቸውን ለመፈጸም ብቃት ያሳጣቸዋል:: አልፈውት የሄዱት በዚህ ምክንያት ይሆን? ሃይማኖታዊ ንጽሕናን ለመጠበቅ ሲባል ችግር ላይ ያለውን ሰው አልፎ መሄድ ተገቢ መሆን አለመሆኑ የሚያጠያይቅ ነው:: በተለይ ደግሞ ሰንበትን ስለማክበር ኢየሱስ ካቀረበው ትምህርት አንጻር ስናየው እውነት ይሆናል (ማቴ 12÷7፤ ማር 3÷4-5):: ያም ቢሆን ግን፣ ምክንያቱ ለሁለቱም ሰበብ ሊሆን አይችልም:: ካህኑ ወደ ታች እንጂ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ አልነበረም:: በተጨማሪም፣ ካህናትና ሌዋውያን ለአገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጡ በቡድን እንጂ እንደ እነዚህ ሁለት ሰዎች ለብቻቸው አይወጡም ነበር:: መሠረታዊው ጉዳይ፣ እነዚህ ሰዎች ያንን ሰው አልፈው ሲሄዱ ከራስ ወዳድነትና ፍርሃት ውጪ ምንም ምክንያት አልነበራቸውም::[31]

[31] የሃይማኖት ሰዎች ይህን ያህል መጨከናቸው የሚገርም ነው:: ሆኖም አዲስ አይደለም:: ዳርሊ እና ቤትሰን ይህን ምሳሌ በራሳቸው መንገድ በተግባር አይተውታል:: በትምህርት ቤታቸው ለአርባ የሰሚናሪ ተማሪዎች የሰሚናሪ ሰዎች ሙያዊ ተግባር ምን መሆን አለበት በሚል ርእስ ጉዳይ ንግግር እንዲያደርጉ ጠይቀው ነበር:: ወደሚቀጥለው ሕንፃ ሄደው የሚናገሩትን እንዲመዘግቡ ተነገራቸው:: እነዚህ ተማሪዎች የሚያደርጉትን ለመታዘብ መንገድ ላይ፣ «ጉዳተኛ» ሰው እንዲቀመጥ ተደርጎ ነበር:: ከተማሪዎቹ ሃያ አራቱ አልፈውት (60%) ሄዱ፤ አንዳንዶቹ ወደ ቦታቸው ለመድረስ በላዩ



ቀጥሎ ያለፈው ሳምራዊው ነበር:: ለዚህ አይሁዳዊ ሕግ ዐዋቂ፣ «ደጉ ሳምራዊ» በሚለው አገላለጽ መጠቀም የስድብ ያህል ነበር:: ሳምራውያን ከፊል አይሁድ ቢሆኑም በጣም የተጠሉና ጠብና ፉክክራቸው ደግሞ አደገኛና አንዳንዴም ሞትን የሚያስከትል ነበር (ዮሐ 4÷5-26፣ §35ሀ ጋር ያነ):: ይህ እንደ ርኩስ የሚቈጠር ሳምራዊ ለሰውዬው አዘነለት:: ሰውዬው ተጐድቶና በደም ተጨማልቆ ሲያየው ለዘመናት ውስጡ ታምቆ የኖረው ጥላቻ ተወገደ:: በሁለቱ መሐል ችግር እንጂ፣ ሌላ የሚያገናኛቸው ነገር አልነበረም::

ምናልባትም ከራሱ ልብስ መጠቅለያ በመሥራት ቍስሉን አሰረለት፤ ማመርቀዝን እንዲከላከልለት የራሱን ወይን ጠጅ አፈሰሰበት:: ስቃዩን እንዲያስታግስለትም የያዘውን ዘይት አፈሰሰበት:: ከዚያ በኋላ በራሱ አህያ አስቀመጠው::[32] ለሰውየው ማረፊያ ስፍራና ምግብ እንዲሆን የራሱን ገንዘብ ከፈለ:: ይህን ሁሉ ያደረገው ችግር ላይ ስለ ነበር እንጂ፣ ሰውየውን በመውደዱ አልነበረም:: በእርግጥም፣ በሥራው ወደደው::

36እንግዲህ፣ ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ሰው ባልንጀራው የሆነው የትኛው ይመስልሃል?» 37ሕግ ዐዋቂውም፣ «የራራለት ነዋ» አለ:: ኢየሱስም፣ «አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ» አለው::

ሉቃ 10÷36-37

«ባልንጀራ የሆነው» የሚለውን ሐረግ፣ ቃል በቃል፣ «ባልንጀራው ሆኖ የተገኘው» ብሎ መተርጎም ይቻላል:: «ባልንጀርነት»

ተራምደው ነበር ማለት ይቻላል:: (J.M. Darley & C.D. Bateson, "'From Jerusalem to Jerico': A Study of Situational Variables in Helping Behaviour," *JPSP* 27 (1973): 100-108).

[32] ቃሉ ለማንኛውም የጭነት እንስሳ፣ ያም ለአህያ፣ ለግመል፣ ለፈረስ ወይም ለበሬ ያገለግላል:: አህያ ተብሎ የተተረጐመው የተለመደ የጭነት እንስሳ በመሆኑ ነው::

የሚለው የግል የሆነ ነገርን ወይም ቦታን አያመለክትም:: ለምናገኘው ማንኛውም ሰው የምናሳየው ዝንባሌ ነው::

እዚህ ላይ የተገላቢጦሽ የሆነ ነገር አለ:: የሕግ ዐዋቂው ትኩረት ፍቅር ተቀባዩ ላይ ነበር (ያም እግዚአብሔር ወይም ባልንጀራው)፤ የኢየሱስ ትኩረት ግን ፍቅር ያሳየው ላይ ነበር (ለምሳሌ፣ ሕግ ዐዋቂው ወይም እኔ!):: ፍቅር ተቀባዩን አስመልክቶ በነገረ መለኮት መራቀቅ ይቻላል:: ይሁን እንጂ ፍቅር ለማሳየት፣ ፍቅር ሰጪ ለመሆን፣ ሁለንተናችንን እንድንሰጥ ይጠበቅብናል:: እንደ ሳምራዊው መሆን የምንፈልግ ከሆነ፣ ብዙ ገንዘብ ማውጣት ሊጠበቅብን ይችላል::

ለኢየሱስ በሰጠው መልስ፣ ሕግ ዐዋቂው፣ «ሳምራዊ» የሚለውን ቃል ማንሳት እንኳ አልፈለገም:: ሆኖም ገሃድ የወጣውን የምሳሌውን ዋነኛ መልእክት ማድበስበስ አይችልም:: ኢየሱስ፣ «ባልንጀራዬ ማነው?» እና፣ «የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?» ለሚሉ ሁለት ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል::

የኢየሱስ የመጨረሻዎቹ ቃላት ተግባራዊና፣ በሚያምኑት መኖርን የሚመለከቱ ናቸው:: በሚያምኑት መኖርን በተመለከተ ቀደም ሲል ኢየሱስ ትክክል የሆነውን እንዲያደርግ ነግሮት ነበር (ቍ 28):: ኢየሱስ አጽንዖት ለመስጠት ያህል እዚህም ደግሞታል:: ተግባራዊነትን በተመለከተ፣ ትክክለኛ ነገረ መለኮታዊ ዕውቀት ብቻ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ እንደማያበቃ ለሕግ ዐዋቂው (ለአንባቢውም ጭምር) አስገንዝቦታል:: ትክክለኛ መሆኑን የምናውቀውን ነገር የማናደርግ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎችን በትክክል መመለሳችን አንድ እርምጃ እንኳ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አያቀርበንም::